1. 60

የሶቪዬት ፡ አጭር ፡ ታሪኮች ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ።

በሚክሃይል፡ሾሉክሆቭ፡ተደረሰ።

# የአንድ፡ሰው፡ እጣ።

የፕሮግሬስ ፡ የመጻሕፍት ፡ ማዘጋጃና ፡
ማሳተሚያ ፡ ቤት።
ሞስኮ ።

From the Library of
ፍሥሐ አጥላው ወልደ ዮሐንስ
FESSEHA ATLAW WOLDE YOHANNES

ከአ[illegible]ማሱ : ባድማ : ተተረጐመ ።

በሶቭዬት : ኅብረት : ታተመ ።

Ш $\frac{70302-681}{014(01)-76}$ без объявления

ለየቨጌኒያ : ግሪጐርዬቭና : ሌቪጽካያ :
ከ ፲፱፻፫ ዓ : ም : እ : አ : አ :
የሶቪዬት : ኅብረት : ኮሙኒስት : ፓርቲ :
አባል : ለሆኑት : መታሰቢያ ።

ከጦርነቱ : በኋላ : በመጀመሪያው : ዓመት : በመጀመሪያው : ጸደይ : ወራት : ከዶን : ወንዝ : ክላይኛው : መድረሻ : በመኪና : ለመጓዝ : አይመችም : (እንደ : ልብ : አይገኝም :) ነበር ። በመጋቢት : ወር : መጨረሻም : ሙቀትን : የተጐናጸፈ : ንፋስ : ከአዞቭ : ባሕር : በመንፈሱ : በስተግራ : በኩል : ያለው : የወንዙ : ዳርቻ : አሻዋ : በሁለት : ቀን : ውስጥ : እራቁቱን : ቀረ ። በበረዶ : ተጐናጽፈውና : አጊጠው : ይታዩ : የነበሩት : በውኃ : የተቦረቦሩት : ቦዮችና : ሸለቆዎችም : በሜዳው : ላይ : የሚገኙትን : ወንዞች : በውኃ : ለመመገብ : ስለጀመሩ : ወንዞች : ከመጠን : በላይ : በመሙላታቸው : የተጋገረውን : በረዶ : እየሰባበሩ :

በመደንፋት ፡ ይጓዙ ፡ ጀመር ። ስለዚህ ፡ መተላለፊያ ፡ መንገዶችን ፡ ሁሉ ፡ ሰው ፡ እንዳይተላለፍባቸው ፡ ዘጉት ።

በዚህ ፡ እድለ ፡ ቢስ ፡ በሆነበት ፡ ጊዜም ፡ ቡካኖቭስካያ ፡ ወደተባለው ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ መንደር ፡ ለመሄድ ፡ ጉዞዬን ፡ ጀመርሁ ። እርቀቱ ፡ እንኳ ፡ ብዙ ፡ አልነበረም ፡ ምናልባት ፡ ስድሳ ፡ ኪሎሜትር ፡ ብቻ ፡ ቢሆን ፡ ነው ። ቢሆንም ፡ በጣም ፡ አስቸጋሪ ፡ ሆነብኝ ። ባልንጀራዬና ፡ እኔም ፡ ጸሐይ ፡ ከመውጣቷ ፡ በፊት ፡ ጉዞዋችንን ፡ ጀመርን ። በደንብ ፡ የተቀለቡ ፡ ሁለት ፡ ፈረሶችም ፡ ከባዱን ፡ ጋሪ ፡ በታላቅ ፡ ችግር ፡ ይስቡት ፡ ጀመር ። የጋሪው ፡ መንኰራኵሮችም ፡ እስከ ፡ ግማሹ ፡ ድረስ ፡ ባሸዋና ፡ በበረዶ ፡ ተቀላቅሎ ፡ በቦካው ፡ እረግረግ ፡ መንገድ ፡ በመዋጣቸው ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ብቻ ፡ እንደተጓዝን ፡ የሳሙና ፡ አረፋ ፡ የመሰለ ፡ ላብ ፡ ከፈረሶች ፡ ሰውነት ፡ ላይ ፡ ለመጉረፍ ፡ ጀመረ ። በፈረሶቹ ፡ ላብ ፡ የጋሪው ፡ መሣሪያ ፡ ጠፍር ፡ ስለበሰበሰም ፡ ንጹሑ ፡ የጥዋት ፡ አየር ፡ ሽታ ፡ እንደሚያሰክር ፡ መጠጥ ፡ ይሰነፍጥ ፡ ጀመር ።

መንገዱም ፡ ለፈረሶች ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ አስቸጋሪ ፡ ስለሆነ ፡ ከጋሪው ፡ ወርደን ፡ ጉዞ



ዋችንን ፡ በእግራችን ፡ እንሔድ ፡ ነበር ። እንደ ፡ ጭቃ ፡ የቦካውም ፡ በረዶ ፡ ከጫማችን ፡ ሥር ፡ እየተጨፈለቀ ፡ እግራችንን ፡ ስለሚውጠው ፡ ለመራመድ ፡ ችግር ፡ ሆነብን ። የመንገዱ ፡ ዳርም ፡ በሚያንጸባርቅ ፡ በረጋ ፡ በረዶ ፡ ስለተሸፈነ ፡ በሱ ፡ ለመሄድ ፡ ፍጹም ፡ አይታሰብም ። እስከ ፡ የላንካ ፡ ወንዝ ፡ ድረስ ፡ ሰላሳ ፡ ኪሎሜትር ፡ ብቻ ፡ ለመሄድ ፡ የስድስት ፡ ሰዓት ፡ ጊዜ ፡ ወሰደብን ።

በበጋ ፡ ወራት ፡ የሚደርቀው ፡ የሞክሆቭስኪይ ፡ መንደር ፡ ትንሽ ፡ ወንዝ ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ስለሞላና ፡ ውኃውም ፡ አንድ ፡ ኪሎሜትር ፡ ሙሉ ፡ በሜዳው ፡ ላይ ፡ ስለተኛበት ፡ ረግረግ ፡ ሁኗል ። ይሁን ፡ እንጅ ፡ ቢበዛ ፡ ሶስት ፡ ሰዎች ፡ ብቻ ፡ ልታሻግር ፡ በምትችል ፡ ቀዳዳ ፡ ጀልባ ፡ መሻገር ፡ ነበረብን ። ፈረሶቻችንንም ፡ መልሰን ፡ ላክናቸው ። ባሻገሩ ፡ ከሚገኘው ፡ ማኅበራዊ ፡ እርሻ ፡ ክረምቱን ፡ ሙሉ ፡ ቁማ ፡ የነበረች ፡ አንዲት ፡ አሮጌ ፡ ጂፕ ፡ አቶሞቢል ፡ ትጠብቀን ፡ ነበር ። ነጂውና ፡ እኔ ፡ በምትዋኘቀው ፡ ትንሽ ፡ ጀልባ ፡ በጥርጣሬ ፡ ወጣን ። ባልንጀራዬ ፡ ግን ፡ እቃችንን ፡ ይዞ ፡ በወዲህኛው ፡ ማዶ ፡ ቀረ ። የበሰበሰውን ፡ ሳንቃ ፡ ትንሽ ፡ ፈረሰኛ ፡ በመታውም ፡ ጊዜ ፡ በቀላሉ ፡

ተገፍተን ፡ ከመንገዳችን ፡ አቅጣጫ ፡ ወጣን ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ከወዲያኛው ፡ ዳር ፡ እስከንደርስ ፡ ድረስ ፡ በእጃችን ፡ በጨበጥነው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እንከላከል ፡ ጀመር ። ባንድ ፡ ሰዓት ፡ ጊዜም ፡ ውስጥ ፡ ከወንዙ ፡ ወዲያ ፡ ማዶ ፡ ደረስን ። ከዚህ ፡ በኋላም ፡ ነጂው ፡ ወደ ፡ መንደር ፡ ሂዶ ፡ ጂፕዋን ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ጀልባው ፡ ዘንድ ፡ መጣ ።

መቅዘፊያውን ፡ አንስቶ ፡ ይህች ፡ ልትፈራርስ ፡ የደረሰች ፡ ጀልባ ፡ ውኃው ፡ ውስጥ ፡ ያልፈራረሰች ፡ እንደሆን ፡ ምናልባት ፡ ብንችል ፡ በሁለት ፡ ሰዓት ፡ ውስጥ ፡ ከባልንጀራህ ፡ ጋር ፡ ተመልሰን ፡ እንመጣ ፡ ይሆናል ፡ አለ ።

መንደሩም ፡ ከወንዙ ፡ ራቅ ፡ ያለ ፡ ነው ። ወንዙ ፡ በሚወርድበት ፡ በኩልም ፡ ያለው ፡ ጸጥታ ፡ በበልግ ፡ ወራት ፡ መሃከል ፡ ወይም ፡ ጸደይ ፡ ሊገባ ፡ ሲል ፡ ሕዝብ ፡ ለቆት ፡ የሄደውን ፡ ቦታ ፡ ይመስላል ። ከወንዙ ፡ የሚመጣው ፡ ሽታም ፡ ከበሰበሰው ፡ ዛፍ ፡ ጋር ፡ በመቀላቀሉ ፡ ለአፍንጫ ፡ የማይስማማ ፡ ሲሆን ፤ ወይባ ፡ በመሰለ ፡ ጭጋግ ፡ የተሸሞነሞነና ፡ ቀላ ፡ ባለ ፡ አበባ ፡ ያሸበረቀ ፡ ከሚመስለው ፡ ራቅ ፡ ካለው ፡ ሜዳ ፡ ሸው ፡ ሸው ፡ የሚለው ፡ ንፋስ ፡ የሚያመጣው ፡ አዲስ ፡ ያፈር ፡ ሽታ ፡ ከበረዶው ፡



ሰንሰለት ፡ በቅርቡ ፡ ነፃነቱን ፡ ያገኘ ፡ መሆኑ ፡ ይታወቃል ።

ባቅራቢያው ፡ ከውኃው ፡ ዳርቻ ፡ ካለው ፡ አሸዋ ፡ ላይ ፡ የተሰበረ ፡ የሽምጥ ፡ አጥር ፡ ተጋድሟል ። ከተሰበረው ፡ አጥር ፡ ላይ ፡ ቁጭ ፡ ብዬ ፡ ሲጋራ ፡ ለማጤስ ፡ ወደ ፡ ኪሴ ፡ እጄን ፡ ሰደድ ፡ ባደርገው ፡ ኪሴ ፡ ውስጥ ፡ የነበረው ፡ ሲጋራ ፡ በውኃ ፡ ረጥቦ ፡ በማግኘቴ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ተስፋ ፡ መቁረጥ ፡ ጣለብኝ ። ይህም ፡ የሆነው ፡ ውኃውን ፡ ስንሻገር ፡ ፈረሰኛው ፡ ጀልባዋን ፡ በመታት ፡ ጊዜ ፡ ቦረቦር ፡ የሆነ ፡ ውኃ ፡ ሽንጤ ፡ ድረስ ፡ ያጥለቀለቀኝ ፡ ጊዜ ፡ እንደሆነ ፡ ተረዳሁት ። ትዝ ፡ እንዳለኝም ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ እንኳን ፡ ለያዝሁት ፡ ሲጋራ ፡ ላስብ ፡ ይቅርና ፡ በእጄ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ መቅዘፊያ ፡ ጥዬ ፡ በውኃው ፡ ውስጥ ፡ እንዳንሰጥም ፡ ነፍሳችንን ፡ ለማትረፍ ፡ ስታገል ፡ እንደነበረ ፡ ነው ። ቢሆንም ፡ ግድየሌሽነቴ ፡ አበሳጨኝ ። ምንም ፡ እንደማይጠቅመኝ ፡ ስላወቅሁ ፡ ቦረቦር ፡ በሆነው ፡ ውኃ ፡ ርሶ ፡ አፈርማ ፡ የሆነውን ፡ ሲጋራዬን ፡ ከኪሴ ፡ በመጠንቀቅ ፡ እያወጣሁ ፡ አጥሩ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ በአንድ ፡ አሰጣ ፡ ጀመር ።

ቀኑም ፡ እርፋድ ፡ ሆነ ። ጸሐይዋም ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ ግንቦት ፡ ጸሐይ ፡ ታቃጥል ፡ ጀመር ።

ስለዚህ ፡ ሲጋራዎቼ ፡ ቶሎ ፡ ይደርቁልኛል ፡
ብዬም ፡ ተስፋ ፡ አደረግሁ ። ከቀኑም ፡ ሞቃት
ነት ፡ የተነሣ ፡ የነበረኝን ፡ የወታደር ፡ ልብስ ፡
ለብሼ ፡ በመምጣቴ ፡ እጅግ ፡ አሳዘነኝ ። ከዓመ
ቱ ፡ ውስጥ ፡ እውነተኛው ፡ የመጀመሪያው ፡
ሙቅ ፡ ቀን ፡ ነበር ። ከባድ ፡ የሆነውን ፡ የመቅ
ዘፍ ፡ ሥራ ፡ ከሠራሁ ፡ በኋላ ፡ አሮጌውን ፡ የ
ወታደር ፡ ኩፍያዬን ፡ አውልቄ ፡ ጸጥታና ፡ ብ
ቸኝነት ፡ ከነገሠበት ፡ ሥፍራ ፡ ተቀምጬ ፡ ሰ
ማይን ፡ ለመሸፈን ፡ የሚሽቀዳደመውን ፡ ደመ
ና ፡ እንጋጥጬ ፡ እያየሁ ፡ በውኃ ፡ የራሰውን ፡
ጠጉሬን ፡ ንፋሱ ፡ እንዲያደርቀው ፡ ፈቀድሁ
ለት ።

ከመንደሩም ፡ የመጨረሻ ፡ ጐጆዎች ፡ አን
ድ ፡ ሰው ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ መንገዱ ፡ ሲገባ ፡
ታየኝ ። ያምስት ፡ ወይም ፡ የስድስት ፡ ዓ
መት ፡ የሆነ ፡ ልጅ ፡ እጅ ፡ ይዞ ፡ ይጐትታል ።
ወደ ፡ መሻገሪያው ፡ ነበር ፡ የሚያዘግሙት ፡
ጂፕዋ ፡ ዘንድ ፡ ከደረሱ ፡ በኋላ ፡ መንገዳቸው
ን ፡ ለውጠው ፡ ወደኔ ፡ አቅጣጫ ፡ መጡ ። አን
ድ ፡ እረጅም ፡ ከትክሻው ፡ ሰግደድ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡
ወደኔ ፡ ቀረብ ፡ ብሎ ፡ በ ሂያጉረመርም ፡ ድም
ጽ ፡ «እንደምን ፡ ዋለህ ፡ ወዳጄ ፡» አለኝ ።



እኔም ፡ «እንደምን ፡ ዋለህ ፡» ብዬ ፡ የዘረ
ጋልኝን ፡ ሸካራ ፡ እጅ ፡ በመጨበጥ ፡ ሰላምታ ፡
ሰጠሁ ።

ወደ ፡ ልጁም ፡ ጐንበስ ፡ ብሎ ፡ «ለሰውዬ
ው ፡ ሰላምታ ፡ ስጥ ። እንደ ፡ አባትህም ፡ መኪ
ና ፡ ነጂ ፡ ይመስላል ፡» አለው ። «አንተና ፡ እ
ኔ ፡ ብቻ ፡ ነን ፡ ካሚዎን ፡ የምንነዳ ፡ እሱ ፡ ግን ፡
እዚያ ፡ ያለችውን ፡ ጂፕ ፡ ነው ፡ የሚነዳ ፡
መሰለኝ ።»

እንደ ፡ ንጹህ ፡ ሰማይ ፡ ኮለል ፡ ባሉ ፡ ሁለ
ት ፡ ዓይኖቹ ፡ ትኩር ፡ አድርጎ ፡ ካየኝ ፡ በኋላ ፡
ፈገግ ፡ ብሎ ፡ በድፍረት ፡ ልጁ ፡ የቀዘቀዘ ፡ እ
ጁን ፡ ዘረጋልኝ ። እኔም ፡ እጁን ፡ እንደጨበ
ጥሁት ፡ «ምነው ፡ ሽማግሌ ፡ እጅህን ፡ በርዶ
ሃል? እንደዚህ ፡ ባለ ፡ ሙቅ ፡ ቀንስ ፡ ምነው ፡
እጅህ ፡ እንደዚህ ፡ የቀዘቀዘው?» ብዬ ፡ ጠየቅ
ሁት ።

በልጅነት ፡ ጠባይ ፡ በመያዝ ፡ ጉልበቶቼ
ን ፡ ደገፍ ፡ ብሎ ፡ ወርቅማ ፡ የሆኑ ፡ ቅንድቦቹ
ን ፡ በመደነቅ ፡ ብድግ ፡ አደረገ ።

«እኔ ፡ እኮ ፡ ሽማግሌ ፡ አይደለሁም ፡ አጐ
ቴ ፤ ገና ፡ ልጅ ፡ ነኝ ፡ እንጅ ፡ ደግሞም ፡ ይህ
ን ፡ ያህል ፡ በብርድ ፡ አልቀዘቀዝሁም ። እጆ
ቼም ፡ የቀዘቀዙበት ፡ ምክንያት ፡ በበረዶው ፡

እንደ ፡ ኳስ ፡ እያድቦለቦልሁ ፡ ስጫወት ፡ ስለነበረ ፡ ነው ፡» አለ ። አባቱም ፡ በጀርባው ፡ ላይ ፡ ተንጠልጥሎ ፡ የነበረውን ፡ የሸራ ፡ አኩፋዳ ፡ አውርዶ ፡ ከአጠገቤ ፡ ተቀመጠ ። «ይህ ፡ አብሮኝ ፡ የሚጓዘው ፡ ትንሽ ፡ መንገደኛ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ። እኔንም ፡ ልክ ፡ እንደራሱ ፡ ነው ፡ የሚያደክመኝ ። ረዘም ፡ ያለ ፡ እርምጃ ፡ ስትራመድ ፡ እሱ ፡ ሮጥሮጥ ፡ ይላል ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ በሱ ፡ ልክ ፡ እርምጃህን ፡ ለመለወጥ ፡ ትገደዳለህ ። አንድ ፡ ጊዜ ፡ ልራመደው ፡ የምችለውን ፡ ሶስት ፡ ጊዜ ፡ መራመድ ፡ አለብኝ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ስለዚህ ፡ የእርምጃችን ፡ ልክ ፡ እንደፈረስና ፡ ዔሊ ፡ የተለያየ ፡ ነው ። የሚያደርገውንም ፡ ለማወቅ ፡ ከኋላህ ፡ ዓይን ፡ እንዲኖርህ ፡ ያስፈልጋል ። ለቅጽበት ፡ ዓይንህን ፡ ከሱ ፡ መለስ ፡ ያደረግኸው ፡ እንደሆን ፡ ወዲያውኑ ፡ በውኃ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ሲንጨባረቅና ፡ ጭቃውን ፡ ሲያቦካ ፡ እንዲሁም ፡ በውኃው ፡ ላይ ፡ የተጋገረውን ፡ በረዶ ፡ እየሰባበረ ፡ እንደ ፡ አንኳር ፡ ስኳር ፡ ሲመጠው ፡ ታገኘዋለህ ። እንደ ፡ እሱ ፡ ካለ ፡ ጋር ፡ በእግር ፡ መሄድ ፡ የወንድ ፡ ሥራ ፡ አይደለም ።» ትንሽ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ከቆየ ፡ በኋላ ፡ «ወዳጄ ፡ አንተስ ፡ አለቃህን ፡ ነው ፡ የምትጠብቀው?» አለኝ ።



የዚህን ፡ ጊዜ ፡ መኪና ፡ ነጂ ፡ አይደለሁም ፡ ብዬ ፡ ልነግረው ፡ ስላልፈቀድሁ ፡ የ ሚከተለውን ፡ መለስሁለት ።

«እንደጠየቅኸኝ ፡ ይመስላል ፡» አልሁት ።

«ከወዲያ ፡ ማዶ ፡ ነው ፡ ወይ ፡ የሚመጣው?»

«ይመስላል ።»

«ጀልባውስ ፡ ቶሎ ፡ ከዚህ ፡ የሚደርስ ፡ ይመስልሃልን?»

«ምናልባት ፡ በሁለት ፡ ሰዓት ፡ ውስጥ ።»

«ደህና ፡ ነው ። እንግዲያውስ ፡ የሚያስቸኩለኝ ፡ ነገር ፡ የለምና ፡ አጠገብህ ፡ አረፍ ፡ ልበል ። ገና ፡ ከሩቅ ፡ እንዳየሁህ ፡ ከኛ ፡ ከሹፌሮቹ ፡ አንዱ ፡ ደህና ፡ ጸሐይ ፡ የሚሞቅበት ፡ ቦታ ፡ ይዟል ፡ ብዬ ፡ አሰብሁ ። ወዲያውኑም ፡ ሲሞቁና ፡ ለብቻ ፡ ሆኖ ፡ ሲጋራ ፡ ሲያጤሱ ፡ ምንም ፡ የሚያስቅ ፡ ነገር ፡ አይገኝም ፡ እንደሚባለው ፡ ሁሉ ፡ እስቲ ፡ ወደ ፡ እሱ ፡ ዘንድ ፡ ሂጄ ፡ አብሬው ፡ ላጤስ ፡ ብዬ ፡ መጣሁ ። ሲጋራ ፡ ነውና ፡ የምታጤሰው ፡ ስለዚህ ፡ ደህና ፡ እንደምትኖር ፡ ተረዳሁት ። አይ! እረጥበዋል ፡ ወይ? የረጠበ ፡ ትምባሆና ፡ ታሞ ፡ በመታከም ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ ፈረስ ፡ ምንም ፡ አይጠቅሙም ፡ እንደሚ

ባለው ፡ ሁሉ ፡ ስለዚህ ፡ ወንድሜ ፡ እሱን ፡ እንተወውና ፡ ከኔ ፡ ትምባሆ ፡ እናጢስ ።»

አንድ ፡ የተሸበለለ ፡ ያረጀ ፡ የትምባሆ ፡ መያዣ ፡ የሐር ፡ ጨርቅ ፡ ቦርሳ ፡ ከስሱ ፡ ካኪ ፡ ሱሪ ፡ ኪስ ፡ አውጥቶ ፡ ሲተረትረው ፡ ካንድ ፡ ጫፍ ፡ በኩል ፡ በጥልፍ ፡ የተጻፉትን ፡ ቃሎች ፡ ልብ ፡ አድርጌ ፡ ለማየት ፡ ቻልሁ ። ቃሎችም ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ የሚሉት ፡ «ለምንወዳችሁ ፡ ወታደሮች ፡ ለአንዱ ፡ ከሌቤዲያንስካያ ፡ ሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የ፮ኛ ፡ ክፍል ፡ ተማሪ ።»

አገር ፡ ውስጥ ፡ ያደገውን ፡ ጠንካራ ፡ ትምባሆ ፡ ስናጤስና ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሳንነጋገር ፡ ቆየን ። ከልጁ ፡ ጋር ፡ ወዴት ፡ እንደሚሄድና ፡ በዚህስ ፡ መጥፎ ፡ መንገድ ፡ ለምን ፡ ይዞት ፡ እንደመጣ ፡ ልጠይቀው ፡ ስል ፡ እሱ ፡ አስቀድሞ ፡ ጠየቀኝ ።

«በጦርነቱ ፡ ጊዜ ፡ ከመጀመሪያ ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ድረስ ፡ የመኪና ፡ መሪ ፡ እንደጨበጥህ ፡ ነበር ፡ ወይ?»

«ትንሽ ፡ ሲቀረኝ ፡ እንጅ ፡ አዎን ።»

«ግንባር ፡ ነበርህ?»

«አዎን ።»



«እኔም ፡ ከሚገባ ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ የሚያንገፈግፍ ፡ ችግር ፡ እስከ ፡ አንገቴ ፡ ድረስ ፡ አጥልቆኝ ፡ ነበር ።»

የጠየሙ ፡ እጆቹን ፡ ከጉልበቶቹ ፡ ላይ ፡ ጣል ፡ አድርጎ ፡ የጸወለገ ፡ እሸት ፡ ይመስል ፡ አንገቱን ፡ ደፍቶ ፡ ቁጭ ፡ አለ ። ሰረቅ ፡ አድርጌ ፡ ብመለከተውም ፡ ኃዘን ፡ ተሰማኝ ። በኃዘንና ፡ በናፍቆት ፡ በመጓጓትና ፡ በትህትና ፡ መወረር ፡ አመድ ፡ የነሰነሱባቸው ፡ የሚመስሉ ፤ ማንም ፡ ትክ ፡ ብሎ ፡ ለማየት ፡ የማይደፍራቸው ፡ ዓይኖች ፡ ለመሆኑ ፡ አይታችሁ ፡ ታውቃላችሁን? እነዚህን ፡ የመሰሉ ፡ ዓይኖች ፡ ለማየት ፡ እድል ፡ አጋጥሞኝ ፡ ላውቃቸው ፡ ችያለሁ ።

ከአጥሩ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ የተጓበጠ ፡ ጭራሮ ፡ ሰብሮ ፡ ለአንድ ፡ ደቂቃ ፡ ያህል ፡ በአሸዋው ፡ ላይ ፡ የሚያስደንቅ ፡ እንደ ፡ ስዕል ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ሲሠራ ፡ ቆይቶ ፡ ለመናገር ፡ ጀመረ ።

«አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ሌሊቱን ፡ ልተኛ ፡ አልችልም ። ዓይኖቼም ፡ በጨለማው ፡ ሳይከደኑ ፡ ነው ፡ የሚያድሩት ። በሃሳቤም ፡ «ዓለም ፡ ለምን ፡ ነው ፡ እንዲህ ፡ የምታስጨንቀኝ? ለምንስ ፡ ነው ፡ የመኖር ፡ ፍላጎቴን ፡ ልታጠፋብኝ ፡ የምትፈልገው?» የሚለውን ፡ ጥያቄ ፡ ሳወጣና ፡

ሳወርድ ፡ አድራለሁ ። ሌሊት ፡ በጨለማውም ፡
ሆነ ፡ ወይም ፡ ቀን ፡ በብርሃን ፡ የዚህን ፡ ጥያ
ቄ ፡ መልስ ፡ ላገኘው ፡ አልቻልሁም ፡... ምን
ም ፡ መልስ ፡ ገና ፡ አላገኘሁም ፡ ደግሞ ፡ ምን ፡
ጊዜም ፡ አላገኝለትም!» በድንገት ፡ ከእንቅልፉ ፡
እንደሚነቃ ፡ ሰው ፡ የተበታተነ ፡ አሳቡን ፡ ሁ
ሉ ፡ ሰበሰበና ፡ ልጁን ፡ ጐሸም ፡ አድርጐ ፡
«ከትልቅ ፡ ወንዝ ፡ አጠገብ ፡ ለልጆች ፡ መጫ
ወቻ ፡ አይጠፋምና ፡ ወደ ፡ ወንዙ ፡ ወርደህ ፡ ተ
ጫወት ፡ ግን ፡ እግርህ ፡ እንዳይረጥብ ፡ ተጠን
ቀቅ ፡» አለው ።

በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ንግግሩ ፡ ሁሉ ፡ ተቋረጠና ፡
በጸጥታ ፡ ስናጤስ ፡ በቅጽበት ፡ ዓይን ፡ አባት
ና ፡ ልጅን ፡ ብመለከት ፡ አንድ ፡ ጐደሎ ፡ ነገ
ር ፡ እንዳለ ፡ ተረዳሁ ። ልጁ ፡ ደህና ፡ ወፈር ፡
ያለ ፡ መናኛ ፡ ልብስ ፡ ለብሷል ። ከላይ ፡ በደ
ረበው ፡ ኮት ፡ አርጀት ፡ ያለ ፡ ለስላሳ ፡ ጠጉራ
ም ፡ ቆዳ ፡ ከአንገቱና ፡ ከእጅጌው ፡ ላይ ፡ሙቀ
ት ፡ እንዲሰጡት ፡ ተሰፍተዋል ፡ ካደረጋቸው
ም ፡ የሱፍ ፡ እግር ፡ ሹራቦች ፡ በላይ ፡ ቡት ፡
ጫማዎቹን ፡ ደንቅሯል ፡ የተቀደዱት ፡ የኮቱ ፡
እጅጌዎችም ፡ እውቀት ፡ (ልምድ ፡) ባለው ፡
የእናት ፡ እጅ ፡ ደህና ፡ ሁነው ፡ እንደ ፡ ተሰፉ ፡
ይታያል ። ያባትዮ ፡ ግን ፡ ፍጹም ፡ የተለየ ፡



ነበር ። ኮቱ ፡ ከብዙ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ስለተቀደደ ፡
ተጨማዶ ፡ ተሰፍቷል ፡ አርጀት ፡ ያለውም ፡
የካኪ ፡ ሱሪው ፡ ቀዳዳ ፡ አላዋቂ ፡ በሆነ ፡ በወ
ንድ ፡ እጅ ፡ አለአግበብ ፡ ስለተጻፈ ፡ ስፌቱ ፡
ያልተካከለ ፡ ነበር ። በእግሮቹም ፡ ያደረጋቸው ፡
ሱፍ ፡ የእግር ፡ ሹራቦች ፡ ብዙ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡
ተቀዳደዋል ፡ ቢሆንም ፡ አዲስ ፡ የወታደር ፡ ጫ
ማዎች ፡ አድርጓል ። የቤት ፡ እጅ ፡ እንኳን ፡
ሊነካቸው ፡ ባጠገባቸውም ፡ ያለፈባቸው ፡ አይ
መስልም ፡ ... ይህን ፡ ሁሉ ፡ ካየሁ ፡ በኋላ ፡
ሚስቱ ፡ ሙታበታለች ፡ ወይም ፡ በመሃከላቸ
ው ፡ አለመግባባት ፡ አለ ፡ የሚል ፡ ሃሳብ ፡
ተሰማኝ ።

ልጁም ፡ ወደ ፡ ውኃው ፡ እየሮጠ ፡ ሲወር
ድ ፡ እየውና ፡ ሳለ ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ እንደገ
ና ፡ ለመናገር ፡ ሲጀምር ፡ ልብ ፡ አድርጌ ፡ ላዳ
ምጠው ፡ ጀመርሁ ።

«እኔ ፡ አንድ ፡ ተራ ፡ ሰው ፡ ነኝ ። በቮርኔዥ ፡
አውራጃ ፡ በ ፲፱፻ ዓ፡ ም ፡ እ ፡ አ ፡ አ ፡ ተወለድሁ ። ባገ
ር ፡ ውስጥ ፡ ጦርነትም ፡ ጊዜ ፡ በኪክቪድዜ ፡ ዲቪዥን
በነበረው ፡ የሬድ ፡ አርሚ ፡ ውስጥ ፡ ነበርሁ ።
በ ፲፱፻፳፪ ዓ ፡ ም ፡ እ ፡ አ ፡ አ ፡ በነበረው ፡ እርሃ
ብ ፡ ወደ ፡ ኩባን ፡ ሂጄ ፡ ላንዳንድ ፡ ሃብታም ፡
ገበሬዎች ፡ እንደ ፡ በሬ ፡ ጠንክሬ ፡ ባልሠራ ፡

ኑሮ ፡ እስከዛሬ ፡ አልኖርም ፣ ነበር ። ግን ፡ ትው
ልድ ፡ አገሬ ፡ የቀሩት ፡ አባቴ ፡ እናቴና ፡ እህ
ቴ ፡ ሁሉም ፡ በረሃብ ፡ አለቁ ። ስለዚህ ፡ በዚህ ፡
ዓለም ፡ ውስጥ ፡ ብቻዬን ፡ ያለዘመድ ፡ ቀረሁ ።
በየቦታው ፡ ካሉት ፡ ዘመዶቼም ፡ አንድ ፡ የተ
ረፈኝ ፡ የለም ። ኩባን ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ከቆ
የሁ ፡ በኋላ ፡ የነበረችኝን ፡ ጐጆ ፡ ሸጬ ፡ ወደ ፡
ቮሮኔዥ ፡ ተመለስሁ ። በመጀመሪያ ፡ አናጺነ
ት ፡ ስሠራ ፡ ተቆየሁ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ፋ
ብሪካ ፡ ተዛውሬ ፡ የሜካኒክነት ፡ ሥራ ፡ ተማ
ርሁ ። ወዲያውም ፡ ሚስት ፡ አገባሁ ። ሚስቴ
ም ፡ ያደገችው ፡ ከልጆች ፡ ማሳደጊያ ፡ ቤት ፡
ነበር ። አባትና ፡ እናት ፡ የሞቱባት ፡ ነበረች ።
አዎን ፤ መልካም ፡ ጠባይ ፡ ያላት ፡ ደስተኛና ፡
ሁሉ ፡ ጊዜ ፡ ሰውን ፡ ለማስደሰት ፡ የምትጣጣ
ር ፡ ነበረች ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ ልትወዳደር ፡ የማይገ
ባት ፡ የደስ ፡ ደስ ፡ ያለባትና ፡ አስተዋይ ፡ ነበረ
ች ። ከልጅነቷ ፡ ጀምራ ፡ እውነተኛ ፡ ችግር ፡
ምን ፡ እንደሆነ ፡ ያወቀች ፡ ነች ፡ ምናልባት ፡ ይ
ህ ፡ ይሆናል ፡ ጠባይዋን ፡ ያሳመረው ። ተጐን ፡
በኩል ፡ ሁነህ ፡ ፊትዋን ፡ የተመለከትሽው ፡
እንደሆን ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ የሚያስደነግጥ ፡ አ
ይደለም ፡ ስለዚህ ፡ እኔ ፡ ሁሉ ፡ ጊዜ ፡ የምመለ



ከተው ፡ ፊትዋን ፡ በሙሉ ፡ ነበር ፡ እንጅ ፡ ከ
ጐን ፡ አልነበረም ። ቢሆንም ፡ በዓለም ፡ ውስ
ጥ ፡ እንደ ፡ እርሷ ፡ ያለ ፡ ቆንጆ ፡ ያለች ፡ ወይ
ም ፡ የምትኖር ፡ አይመስለኝም ።

ከሥራ ፡ ወደ ፡ ቤቴ ፡ ስመጣ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡
ደክሞኝ ፡ ደግሞም ፡ ጠባዬ ፡ ሁሉ ፡ ተለዋውጦ ፡
ነበር ፡ የምመጣው ። እሷ ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ቀንም ፡
ተቆጥታ ፡ ወይም ፡ ተቀይማ ፡ አታውቅም ። ሁ
ሉ ፡ ጊዜ ፡ የዋህ ፡ ደግና ፡ ዝምተኛ ፡ ከመሆ
ኗ ፡ በላይ ፡ እንኳን ፡ በቤት ፡ ኑሮ ፡ ይቅርና ፡ ባ
ይኖርም ፡ ከየትም ፡ ፈልጋ ፡ አንድ ፡ ደስ ፡ የሚ
ያሰኝ ፡ ነገር ፡ ልታደርግልህ ፡ የምትፈቅድ ፡ ባ
ደረገችልህም ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ በቂ ፡ ነው ፡
የማትል ፡ ነበረች ። ትክ ፡ ብለህ ፡ ካየሃት ፡ በ
ኋላ ፡ ግን ፡ ልብህን ፡ ከ ሚሰማው ፡ ደስታ ፡ ብ
ዛት ፡ የተነሣ ፡ እቅፍ ፡ አድርገህ ፡ «ፍቅሬ ፡ ኢ
ሪና ፡ ሆይ ፡ ስለነበረኝ ፡ መጥፎ ፡ ጠባይ ፡ አዝናለሁ ፡
ይቅር ፡ በይኝ ፡ ዛሬ ፡ ከሥራዬ ፡ በጣም ፡ ስላ
በሳጬኝ ፡ ነው ፡ ያሳዘንሁሽ ፡» ትላለህ ። ከዚ
ህ ፡ በኋላ ፡ አእምሮዬ ፡ እረፍትና ፡ ደስታን ፡
ይጐናጸፍና ፡ በመሃከላችን ፡ እንደገና ፡ ሰላም ፡
ይነግሣል ። ይህስ ፡ ሥራህን ፡ ለመሥራት ፡
ምን ፡ ያህል ፡ እንደሚረዳህ ፡ ታውቀዋለህ ።
ማለዳም ፡ ካልጋዬ ፡ ልክ ፡ እንደተተኮሰ ፡ ጥይ

ት ፡ ወጥቼ ፡ ወደምሠራበት ፡ ፋብሪካ ፡ እበራ ለሁ ። ከዚያም ፡ ምንም ፡ ሥራ ፡ ሳላማርጥ ፡ ያ ገኘሁትን ፡ ሁሉ ፡ አጣድፌዋለሁ ። እንደ ፡ ብልህ ፡ ባልንጀራ ፡ ያለች ፡ ሚስት ፡ ማግኘት ፡ መታደ ል ፡ ነው ።

አንድ ፡ ቀን ፡ በደሞዝ ፡ መቀበያ ፡ ዕለት ፡ ከሥራ ፡ ባልንጀሮቼ ፡ ጋር ፡ መጠጥ ፡ ቤት ፡ ሄጄ ፡ ጠጣሁ ። ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ እየተላጋሁ ና ፡ እየተንገዳገድሁ ፡ እንኳን ፡ የእግርኛው ፡ መንገድ ፡ ይቅርና ፡ ዋንኛው ፡ መንገድ ፡ እስ ኪጠበኝ ፡ ድረስ ፡ በሚያሳዝንና ፡ በሚያስቅቅ ፡ ሁኔታ ፡ እግሮቼ ፡ እየተጠላለፉ ፡ ከወዲያ ፡ ወ ዲህ ፡ እየተላጋሁ ፡ ከቤቴ ፡ ገባሁ ፡ ቢሆንም ፡ በ ዚያን ፡ ጊዜ ፡ ልጅነት ፡ ስለነበረኝ ፡ መጠጥ ፡ ስለማያደክመኝ ፡ ብዙ ፡ ጠጥቼ ፡ ደህና ፡ እገ ባ ፡ ነበር ። ግን ፡ በኋላ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ እን ደ ፡ ሕፃንነቴ ፡ እየወደቅሁና ፡ እየተነሳሁ ፡ አ ንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ እየተንፏቸሁ ፡ እገባ ፡ ጀመር ። እንዲህም ፡ በሚሆንበት ፡ ጊዜ ፡ ወቀሳ ፡ ወይም ፡ ስድብ ፡ ወይም ፡ ጭቅጭቅ ፡ ከባ ለቤቴ ፡ ደርሶብኝ ፡ አያውቅም ። የኔ ፡ ኢሪናዬ ም ፡ ሳቅ ፡ ብላ ፡ ፍቅር ፡ በሞላበት ፡ ጥንቃቄ ፡ እንዳልቆጣ ፡ አድርጋ ፡ ጫማዎቼን ፡ አውልቃ ፡ በሹክሹክታ ፡ ቃል ፡ «አንድሬይ ፡ ለዛሬ ፡ ማ



ታ ፡ በግርግዳው ፡ በኩል ፡ ብትተኛ ፡ ይሻላል ፡ አለበለዚያ ፡ ግን ፡ በእንቅልፍ ፡ ልብህ ፡ ትወ ድቃለህ ፡» ትለኝ ፡ ነበር ። ወዲያውኑ ፡ እህል ፡ እንደሞላበት ፡ ስልቻ ፡ ካልጋዬ ፡ ላይ ፡ ስወድ ቅና ፡ የማየው ፡ ሁሉ ፡ በፊቴ ፡ ሲሽከረከር ፡ እ ንቅልፍ ፡ ሊይዘኝ ፡ ሲል ፡ ካጠገቤ ፡ ጋደም ፡ ብላ ፡ ለኔ ፡ በማዘን ፡ እራሴን ፡ እየዳሰሰች ፡ ቀ ስ ፡ ብላ ፡ በለስላሳ ፡ ቃል ፡ ስትናገር ፡ እሰማት ፡ ነበር ። ...

ጥዋትም ፡ ለመዘጋጀት ፡ እንድችል ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ቀደም ፡ ብላ ፡ ትቀሰቅሰኝና ፡ በስካር ፡ ማግስት ፡ ምንም ፡ ለመብላት ፡ ስለማይቻል ፡ ኮምጠጥ ፡ ያለ ፡ የዱባ ፡ ጭማቂ ፡ ወይም ፡ እሱ ን ፡ የመሰለ ፡ ነገር ፡ አዘጋጅታ ፡ ደግሞ ፡ መጠ ጥ ፡ የገደለውን ፡ መጠጥ ፡ ያነሳዋል ፡ እንደ ሚባለው ፡ ቮድካ ፡ በብርጭቆ ፡ አድርጋ ፡ «ይ ኸውልህ ፡ አንድሬይ ፡ ግን ፡ ሌላ ፡ ጊዜ ፡ እባክ ህ ፡ እንዳትጠጣ ፡» ብላ ፡ ትሰጠኝ ፡ ነበር ። ስ ለዚህ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እንዲህ ፡ አድርጐ ፡ ለሚ ያስብለት ፡ እንዴት ፡ የሚያሳዝን ፡ ነገር ፡ ሊመ ልስለት ፡ ይችላል? የሰጠችኝን ፡ ተቀብዬ ፡ ከ ጠጣሁ ፡ በኋላ ፡ በልቤ ፡ አመሰግናትና ፡ ስሚ ያት ፡ ወደ ፡ ሥራዬ ፡ እሄዳለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ ለምን ፡ ጠጣህ ፡ ብላ ፡ ብትጨቅጭቀኝና ፡ ብ

ትቆጣኝ ፡ ኑሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሚያውቀው ፡
እንደገና ፡ እየጠጣሁ ፡ ነበር ፡ የምገባው ። ባን
ዳንድ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ሴትዮዋ ፡ ጅል ፡ ሁና ፡ በመ
ጨቃጨቋ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ወንዶቹ ፡ እየሰከሩ ፡
ሲገቡ ፡ አይቻለሁ ፡ ደግሞም ፡ አውቃለሁ ።

ብዙም ፡ ሳንቆይ ፡ ልጆች ፡ ለመውለድ ፡
ጀመርን ። በመጀመሪያ ፡ አንድ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡
ከዚያ ፡ ቀጥለን ፡ ሁለት ፡ ሴት ፡ ልጆች ፡ ወለ
ድን ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ከባልንጀሮቼ ፡ ተለያየ
ሁ ። ቤተ ፡ ሰባችንም ፡ በመጠኑ ፡ ስላደገ ፡ ደ
ሞዜን ፡ በሙሉ ፡ ለባለቤቴ ፡ እሰጥ ፡ ጀመር ።
በእረፍት ፡ ቀኔም ፡ አንድ ፡ ብርጭቆ ፡ ቢራ ፡
ብቻ ፡ ነበር ፡ የምጠጣው ፡ እንጅ ፡ ከዚያ ፡ አላ
ልፍም ፡ ነበር ።

በ፲፱፻፳፱ ዓ፡ም፡እ፡አ፡አ፡ ስለመኪና ፡ ማወቅ ፡
ከፍ ፡ ያለ ፡ ስሜት ፡ ስላደረብኝ ፡ መንዳት ፡ ተማርሁ
ና ፡ አንድ ፡ ካሚዎን ፡ እነዳ ፡ ጀመር ። ከዚህ ፡
በኋላም ፡ ወደ ፡ ፋብሪካው ፡ ሥራ ፡ ለመመለ
ስ ፡ አልፈለግሁም ። መንዳቱንም ፡ ይበልጥ ፡
እየወደድሁት ፡ ስለሄድሁ ፡ ይሄውልህ ፡ አስር ፡
ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ሳይሰማኝ ፡ በፍጥነት ፡ አለፈ ።
ልክ ፡ እንደ ፡ ሕልም ፡ ሁኖ ፡ ነው ፡ የሚሰማኝ ።
የአስር ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ምንድር ፡ ነች? እስቲ ፡
ከአርባ ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ያሳለ



ፈው ፡ ጊዜ ፡ ይሰማው ፡ እንደሆን ፡ ጠይቀው!
ያለፈው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እዚያ ፡ ማዶ ፡ ከሜዳ
ው ፡ ላይ ፡ እንዳለው ፡ ጭጋግ ፡ ሁኖ ፡ ነው ፡ የ
ሚታየው ። ዛሬ ፡ ጥዋት ፡ ሳቋርጠው ፡ አካባ
ቢው ፡ ሁሉ ፡ ግልጽ ፡ ሁኖ ፡ ይታይ ፡ ነበር ፡ ግ
ን ፡ አሁን ፡ ሃያ ፡ ኪሎሜትር ፡ ብቻ ፡ እስከመ
ጣ ፡ ድረስ ፡ ጭጋግ ፡ ስለሸፈነው ፡ ዛፎችን ፡
ከሳሩ ፡ ወይም ፡ እርሻውን ፡ ከግጦሹ ፡ ሜዳ ፡ ለመ
ለየት ፡ አትችልም ።

በነዚህ ፡ ባለፉት ፡ አስር ፡ ዓመታት ፡ ውስ
ጥ ፡ ቀን ፡ ከሌት ፡ ነው ፡ የሠራሁት ። ስለዚህ ፡
ደህና ፡ ደሞዝ ፡ አገኝ ፡ ስለነበረ ፡ ከሌሎች ፡ የ
ከፋ ፡ ኑሮ ፡ አልነበረም ፡ የምንኖረው ። በልጆ
ቻችንም ፡ በጣም ፡ ነበር ፡ የምንደሰተው ። ሶ
ስቱም ፡ በትምህርታቸው ፡ በጣም ፡ ጐበዞች ፡
ነበሩ ፡ በተለየም ፡ ትልቁ ፡ ልጃችን ፡ አናቶሊ ፡
በሂሳብ ፡ (በቁጥር ፡) ትምህርት ፡ በጣም ፡ ጐበ
ዝና ፡ ብሩህ ፡ የሆነ ፡ አእምሮ ፡ ስላለው ፡ ስሙ ፡
በሞስኮው ፡ ጋዜጣ ፡ ተገልጿል ። ይህን ፡ ዓይ
ነት ፡ ታላቅ ፡ ስጦታ ፡ ከማን ፡ እንደወረሰው ፡
አላውቅም ፡ ልነግርህም ፡ አልችልም ። ከፍ ፡
ያለ ፡ ደስታና ፡ ኩራትም ፡ ተሰማኝ ።

ባስር ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ገንዘብ ፡ አጠራቅ
መን ፡ ከጦርነቱ ፡ በፊት ፡ ሁለት ፡ ክፍልና ፡ ብ

ራንዳ ፡ ያላት ፡ ጐጆ ፡ እንዲሁም ፡ አንድ ፡ ማረ
ፊያ ፡ ጐጆ ፡ ሠርተን ፡ ነበር ። ኢሪናም ፡ ሁለ
ት ፡ ፍየሎች ፡ ገዛች ። ከዚህ ፡ የበለጠስ ፡ ምን ፡
ያስፈልገን ፡ ነበር? ለልጆቹ ፡ ቅንጨና ፡ ወተ
ት ፤ እራሳችንን ፡ የምናስጠጋበት ፡ ቤት ፤ ሰው
ነታችንን ፡ የምንከልልበት ፡ ልብስ ፤ የምንጫ
ማበት ፡ ጫማ ፡ ስለነበረን ፡ ምንም ፡ የሚያሳ
ስበን ፡ አልነበረም ። ስህተቱ ፡ ብቻ ፡ ጥሩ ፡ ቦ
ታ ፡ ሳልመርጥ ፡ ቀርቼ ፡ ከአይሮፕላኑ ፡ ፋብሪ
ካ ፡ አጠገብ ፡ መሬት ፡ ሰጡኝ ። ምናልባት ፡
ቦታዬ ፡ ከዚህ ፡ ሳብ ፡ ያለ ፡ ሆኖ ፡ ቢሆን ፡ ይህ
ን ፡ ጊዜ ፡ ኑሮዬ ፡ የተሻለ ፡ በሆነ ፡ ነበር ።
ጦርነት ፡ ተነሳ ። ቀጥሎ ፡ ባለውም ፡ ቀን ፡
ለወታደርነት ፡ የተጠራሁበት ፡ ወረቀት ፡ ደረ
ሰኝ ፡ የሚለውም ፡ «በደረሰህ ፡ ማግስት ፡ ከወ
ታደሩ ፡ ሠፈር ፡ እንድትቀርብ ፡ ትለመናለህ ፡»
ነው ። ኢሪና ፤ አናቶሊና ፡ ሁለቱ ፡ ሴት ፡ ልጆ
ቼ ፡ ናስቴኝካና ፡ አሊኡሽካ ፡ አራቱ ፤ አንድ ፡
ላይ ፡ ሁነው ፡ ሸኙኝ ። ሁለቱ ፡ ሴት ፡ ልጆቼ ፡
ትንሽ ፡ ሲያለቅሱ ፡ አስራ ፡ ሰባተኛውን ፡ ዓመ
ቱን ፡ የያዘው ፡ አናቶሊ ፡ ግን ፡ ብርድ ፡ እንዳ
ንቀጠቀጠው ፡ ሁሉ ፡ ይንቀጥቀጥ ፡ ነበር ። አ
ስራ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ አብረን ፡ ስንኖር ፡ ኢሪ
ና ፡ እንደዚያንለት ፡ ስትሆን ፡ አይቻት ፡ አላ



ውቅም ። ሌሊቱን ፡ ደረቴና ፡ ትከሻዬ ፡ ላይ ፡
ያለው ፡ ሸሚዜ ፡ በኢሪና ፡ እንባ ፡ ታጥቦ ፡ አ
ደረ ። ጥዋትም ፡ እንደዚሁ ፡ ነበር ። ወደ ፡ ባቡ
ር ፡ ጣቢያም ፡ አብረን ፡ ሄድን ። ፊቷንም ፡ ለ
ማየት ፡ አልቻልሁም ። ከእንባዋ ፡ ብዛት ፡ የተ
ነሳ ፡ ከንፈሮቿ ፡ አብጠው ፡ ነበር ። ጸጉሯም ፡
ከራሷ ፡ መሸፈኛ ፡ ሾልኮ ፡ ወጥቶ ፡ ይታያል ።
አይኖቿም ፡ ፈዘው ፡ አእምሮው ፡ እንደዞረ ፡
ሰው ፡ ፍጥጥ ፡ ብለው ፡ ያዩ ፡ ነበር ። መኰንኖ
ቹ ፡ ባቡር ፡ ላይ ፡ እንድንሳፈር ፡ ባዘዙ ፡ ጊዜ ፡
ከቆመችበት ፡ ዘላ ፡ አንገቴ ፡ ላይ ፡ ተጠምጥማ ፡
ወንዝ ፡ ዳር ፡ እንዳለ ፡ ቄጤማ ፡ ትንዘፈዘፍ ፡
ነበር ።... ልጆች ፡ ሆኑ ፡ እኔም ፡ ልናናግራት ፡
ብንሞክር ፡ ሳይቻለን ፡ ቀረ ። የተቀሩት ፡ ሴቶ
ች ፡ ከባሎቻቸውና ፡ ከልጆቻቸው ፡ ጋር ፡ ይጫ
ወታሉ ፡ የኔዋ ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ቅርንጫፍ ፡ ላይ ፡
እንደተጣበቀች ፡ ቅጠል ፡ እኔ ፡ ላይ ፡ ተንጠል
ጥላ ፡ ከመንቀጥቀጥ ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ ለመና
ገር ፡ አልቻለችም ። «ፍቅሬ ፡ ኢሪና ፡ ሆይ ፡
እባክሽ ፡ በርታ ፡ በይ ፡» አልኋት ፡ «ከመሄዴ
ም ፡ በፊት ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ እንኳ ፡ ተናገሪ ።»
እየተንሰቀሰቀች ፡ እንዲህ ፡ አለች ፡ «አንድሬ
ይ ፡ ፍቅሬ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ እኔና ፡ አንተ ፡
ከቶ ፡ አንተያይም ።»

እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ስትናገር ፡ በሰማሁ ፡ ጊዜ ፡ ልቤ ፡ ስለሷ ፡ በኃዘን ፡ ሊፈነዳ ፡ ደረሰ ። በዚህን ፡ ጊዜም ፡ ከሷ ፡ ተነጥዬ ፡ የምሄደው ፡ ወደ ፡ ጦርነት ፡ እንጅ ፡ ወደ ፡ ግብገ ፡ ቤት ፡ አለመሆኑን ፡ ልትረዳው ፡ በተገባት ፡ ነበር ። እዚህ ፡ ላይ ፡ በቁጣ ፡ ደሜ ፡ ፈላና ፡ እጆቿን ፡ ፈልቀቄ ፡ ካስለቀቅኋት ፡ በኋላ ፡ ገፋ ፡ አደረግ ኋት ። ለኔ ፡ በቀላል ፡ ገፋ ፡ ያደረግኋት ፡ መስ ሎ ፡ ነበር ፡ የተሰማኝ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እንደ ፡ በሬ ፡ ጠንካራ ፡ ስለነበርሁ ፡ አንድ ፡ ሶስት ፡ እርምጃ ፡ እየተንገደገደች ፡ ወደኋላዋ ፡ ሄደች ። እንደ ገና ፡ እጅዋን ፡ ዘርግታ ፡ ወደኔ ፡ ትንሽ ፡ እን ደተመለሰች ፡ «ደህና ፡ ስንብት ፡ ብሎ ፡ መሸ ኘት ፡ እንደዚህ ፡ ነው ፡ ወይ? ከጊዜዬ ፡ በፊት ም ፡ ልትገይኝ ፡ ነው ፡ ወይ ፡ የምትፈልጊው? » ብዬ ፡ ጮሁባት ። ግን ፡ በኋላ ፡ ሁኔታዋ ፡ ስላ ሳዘነኝ ፡ እንደገና ፡ እቅፍ ፡ አድርጌ ፡ ያዝኋት ።

በድንገትም ፡ ንግግሩን ፡ አቋርጦ ፡ ለትን ሽ ፡ ጊዜ ፡ ዝም ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ የመንሰቅሰቅ ፡ ድምጽ ፡ ሰማሁ ። ኃዘኑም ፡ ተሰማኝ ። ሰረቅ ፡ አድርጌ ፡ ብመለከተውም ፡ በኃዘን ፡ ከፈዘዙ ፡ አይኖቹ ፡ አንድ ፡ ጠብታ ፡ እንባ ፡ አልወረደም ። እራሱን ፡ ወደ ፡ መሬት ፡ ደፍቶ ፡ የዛሉት ፡ ትላልቅ ፡ እጆቹና ፡ አገጩ ፡ ደግሞ ፡ ግጥም ፡ አድርገው ፡ የዘ ጋቸው ፡ ከንፈሮቹ ፡ በቀላሉ ፡ ይንቀጠቀጡ ፡ ነበር ።

በዝግታ ፡ «ወዳጄ ፡ ሆይ ፡ ተው ፡ ምርር ፡ ብለህ ፡ አትዘን ፡ እየመላለስህም ፡ አታስበው ፡» አልሁት ፡ ንግግሬን ፡ የሰማው ፡ አልመሰለኝ ም ። በታላቅ ፡ ትግል ፡ ስሜቱን ፡ ካሸነፈ ፡ በ ኋላ ፡ በድንገት ፡ በወፈረና ፡ በተለወጠ ፡ ድም ጽ ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

«እስከ ፡ እለተ ፡ ሞቴና ፡ የመጨረሻዋም ፡ እስትንፋስ ፡ ጥላኝ ፡ እስክትሄድ ፡ ድረስ ፡ እን ዲህ ፡ አድርጌ ፡ ስለገፋኋት ፡ ለራሴ ፡ ምንም ፡ ይቅርታ ፡ አላደርግለትም!»

ለብዙ ፡ ጊዜም ፡ ምንም ፡ ሳይናገር ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ተቀመጠ ። ሲጋራም ፡ ለማጤስ ፡ ትም ባሆውን ፡ በወረቀት ፡ ላይ ፡ አፍሶ ፡ ለመጠቅ ለል ፡ ቢሞክር ፡ አቅቶት ፡ ወረቀቱ ፡ በጣቶቹ ፡ መሃከል ፡ ተበጣጠሱ ፡ ትምባሆውም ፡ ጉልበ ቶቹ ፡ ላይ ፡ ተበታትኖ ፡ ፈሰሰ ። በመጨረሻው ም ፡ እንደምንም ፡ ተጣጥሮ ፡ የተዛነፈና ፡ የተ ዝረከረከ ፡ ጥቅል ፡ ጠቀለለና ፡ ጥሙን ፡ ለማ ርካትም ፡ ደጋግሞ ፡ ከሳበ ፡ በኋላ ፡ ወሬውን ፡ ቀጠለ ።

«እራሴን ፡ ከኢሪና ፡ ካላቀቅሁ ፡ በኋላ ፡ ጉን ጭና ፡ ጉንጭዋን ፡ በእጆቼ ፡ ይዤ ፡ ሳምኋት ።

ከንፈሮችዋ ፡ ግን ፡ ልክ ፡ እንደበረዶ ፡ ቀዝቅዘው ፡ ነበር ። ከዚያ ፡ በኋላም ፡ ልጆቼን ፡ ደህና ፡ ሰንብቱ ፡ ብዬ ፡ ጉዞውን ፡ በጀመረው ፡ ባቡር ፡ ዘልዬ ፡ ደረጃው ፡ ላይ ፡ ለመቆም ፡ ቻልሁ ። ባቡሩም ፡ ሲነሳ ፡ እያዘገመ ፡ በመሄዱ ፡ ቤተሰቦቼን ፡ እንደገና ፡ ላያቸው ፡ ቻልሁ ። ልጆቼም ፡ ወላጆች ፡ እንደሌሏቸው ፡ ልጆች ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ችፍግ ፡ ብለው ፡ ቁመው ፡ እጃቸውን ፡ ሲያርገበግቡ ፡ ፈገግ ፡ ለማለት ፡ ቢሞክሩም ፡ ግን ፡ አልቻሉም ፡ ነበር ። ኢሪና ፡ ግን ፡ እጆቿ ፡ ከደረቷ ፡ ላይ ፡ ነበሩ ፡ ከንፈሮቿም ፡ እንደ ፡ ኖራ ፡ ነጽተዋል ፡ በሹክሹክታ ፡ ትናገር ፡ ነበር ፡ ዓይኖቿም ፡ ወደኔ ፡ አተኩረው ፡ ይመለከታሉ ፡ ኃይለኛ ፡ ንፋስ ፡ እየተጋፋ ፡ እንደሚሄድ ፡ ሰውም ፡ ሰውነቷ ፡ ጭብጥብጥ ፡ ብሎ ፡ ነበር ። ሁልጊዜ ፡ በሃሳቤም ፡ የሚታዩኝ ፡ እጆቿ ፡ ከደረቷ ፡ ላይ ፡ ሁነው ፡ ከንፈሮቿ ፡ ነጥተው ፡ እንባ ፡ ያዘሉት ፡ ዓይኖቿም ፡ አተኩረው ፡ ወደኔ ፡ ሲመለከቱ ፡ ነው ። ይበልጠውን ፡ ጊዜም ፡ በሕልሜ ፡ የሚታዩኝ ፡ ይሄው ፡ ነው ። ለምንስ ፡ ነው ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ የገፋኋት? አሁን ፡ እንኳ ፡ ይህን ፡ ሳስበው ፡ አንድ ፡ የጐለደፈ ፡ ሰንጢ ፡ ልቤ ፡ ላይ ፡ ተተክሎ ፡ የተጠመዘዘ ፡ መስሎ ፡ ነው ፡ የሚሰማኝ ።



በኡክራይና ፡ ውስጥ ፡ ቤላያ ፡ ጼርኮቭ ፡ ወደሚገኘው ፡ የጦር ፡ ክፍላችን ፡ ተወሰድን ። ሶስት ፡ ቶን ፡ ክብደት ፡ የሚችል ፡ መኪና ፡ ተሰጥቶኝ ፡ በዚሁ ፡ ነው ፡ ወደ ፡ ጦሩ ፡ ግንባር ፡ የሄድሁት ። በጦርነቱ ፡ መጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ እንዴት ፡ እንደነበረ ፡ ልተርክልህ ፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም ፡ አንተው ፡ እራስህ ፡ እንዴት ፡ እንደነበረ ፡ ስላየኸው ፡ ታውቀዋለህና ። ከቤተሰብህም ፡ ብዙ ፡ ደብዳቤዎች ፡ ይደርስሃል ፡ ግን ፡ አንተ ፡ መልስ ፡ ብዙ ፡ አትጽፍም ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ እኔ ፡ ደህና ፡ ነኝ ፡ ወደ ፡ ውጊያ ፡ የምሄደውም ፡ ትንሽ ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ብለህ ፡ ነበር ፡ የምትጽፈው ። ምናልባት ፤ አሁን ፡ ወደኋላ ፡ አፈግፍገን ፡ ኃይላችንን ፡ ካጠራቀምን ፡ በኋላ ፡ ፍሪትዞች ፡ (ጀርመኖች ፡) እንዳይረሱት ፡ የሚያስቡትን ፡ ነገር ፡ እንሰጣቸዋለን ። ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ ትጽፋለህ? ይልቁንም ፡ አሰቃቂ ፡ ጊዜ ፡ ስለሆነ ፡ የመጻፍ ፡ ፍላጐትህ ፡ ሁሉ ፡ ይሞታል ። እኔ ፡ ሰው ፡ እንዲያዝንልኝ ፡ በማለት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ የደረሰብኝን ፡ ችግር ፡ ጽፌ ፡ አላውቅም ። ነገር ፡ ግን ፡ አንዳንድ ፡ ለሃጫም ፡ ፍጥረቶች ፡ አሉልህ ፡ እንጂ ። ሚስቶቻቸውና ፡ ልጆቻቸው ፡ የኛውን ፡ ያህል ፡ የችግር ፡ ጊዜ ፡ እንዳለባቸው ፡ ሳይገነዘቡት ፡ እን

ዲያዝኑላቸው ፡ ብቻ ፡ በማሰብ ፡ እንዴት ፡ ባለ ፡
ችግር ፡ ነው ፡ የምኖረው ፤ ምናልባት ፡ እዚሁ ፡
ሙቼ ፡ እቀር ፡ ይሆናል ፡ እያሉ ፡ አንድም ፡
ሳያስቀሩ ፡ የቆጡን ፡ የባጡን ፡ እየቀባጠሩ ፡
የሚጽፉ ፡ አሉ ። ለምንስ ፡ ነው ፡ ሙሉውን ፡
አገር ፡ በትክሻቸው ፡ እንዲሸከሙት ፡ የሚያ
ደርጓቸው ። ሚስቶቻችንና ፡ ልጆቻችን ፡ እን
ዲህ ፡ ከፍ ፡ ያለውን ፡ ክብደት ፡ ለመሸከም ፡
ምን ፡ ዓይነት ፡ ትክሻና ፡ ጉልበት ፡ ሊኖራቸ
ው ፡ ያስፈልጋል! ሆኖም ፡ በትእግሥት ፡ ቻሉት ፡
አልሰባበራቸውም! ከነዚህም ፡ ዓይነት ፡ ፍጥረ
ቶች ፡ አንዱ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ አሰቃቂ ፡ ደብ
ዳቤ ፡ ለሚስቱ ፡ ስለጻፈላት ፡ በደረሳትና ፡ ባየ
ችው ፡ ጊዜ ፡ አዕምሮዋን ፡ በጠበጠው ። የዚህ ፡
ዓይነት ፡ ደብዳቤ ፡ ካገኘች ፡ በኋላ ፡ ስለራሷ ፡
ሆነ ፡ ስለ ፡ሥራዋ ፡ ምንም ፡ ለማድረግ ፡ አል
ቻለችም ። ይህስ ፡ ሊሆን ፡ አይገባም! ወንድ ፡
የተፈጠረው ፡ ለዚህ ፡ አይደለምን ? አንተስ ፡
ወታደር ፡ የሆንከው ፡ ሁሉን ፡ ነገር ፡ አንተው ፡
እራስህ ፡ ብቻ ፡ በትእግሥት ፡ እንድትችለው ፡
አይደለምን ? በፍርሃት ፡ ተውጠህ ፡ እንደሴት ፡
የምትንበደበድ ፡ የሆነ ፡ እንደሆን ፡ የሴት ፡ ቀ
ሚስ ፡ ለብሰህ ፡ አረም ፡ ስታርምና ፡ ላሞችን ፡
ስታልብ ፡ እዚያው ፡ ከመንደር ፡ ብትቀር ፡ የተ



ሻለ ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ ከጦር ፡ ግንባር ፡ የምትፈ
ለግ ፡ አይደለም ፡ ምክንያቱም ፡ የዚህ ፡ ዓይነት ፡
ሰዎች ፡በቂ ፡ የሆኑ ፡ ስላሉ ፡ ነው!

እኔ ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እጄ ፡ ላይ ፡ አን
ድ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ እግሬ ፡ ላይ ፡ ስለቆሰልሁ ፡
ዓመት ፡ የሞላ ፡ እንኳ ፡ አልተዋጋሁም ፡... የመ
ጀመሪያውን ፡ ከአየር ፡ የተተኮሰ ፡ ጥይት ፡ ሲ
ያቆስለኝ ፡ የሁለተኛውን ፡ ግን ፡ የቦምብ ፡ ፍ
ንጣሪ ፡ ነው ። ጀርመኖች ፡ ካሚዎኔን ፡ ከላይ
ና ፡ ከጐን ፡ ሲበሳሱት ፡ እድለኛ ፡ በመሆኔ ፡ አ
መለጥሁ ። ሁሉጊዜ ፡ እድል ፡ ነበረኝ ። አንድ ፡
ቀን ፡ ግን ፡ እድሌ ፡ ጥሎኝ ፡ ሸሸ ። በግንቦት ፡
ወር ፡ ፲፱፻፵፪ ዓ ፡ ም ፡ እ ፡ አ ፡ አ ፡ ሎዞቬ
ንኪ ፡ ተማረክሁ ። ጀርመኖች ፡ በብርቱው ፡
የማጥቃት ፡ ውጊያ ፡ አደረጉብን ። አንደኛው ፡
የኛ ፡ ባለ ፡ ፲፰ ፡ ሚሊሜትር ፡ መድፍ ፡ ጥይት ፡
ሊያልቅበት ፡ ስለተቃረበ ፡ ለማቀበል ፡ ካሚዎኔን ፡
እስክትሞላ ፡ ድረስ ፡ ጥይት ፡ መጫን ፡ ጀመርን ።
እራሴም ፡ ሸሚዜ ፡ በላቤ ፡ ከሰውነቴ ፡ ጋር ፡
እስኪጣበቅ ፡ ድረስ ፡ ጠንክሬ ፡ ጫንሁ ። ቶሎ ፡
ብለን ፡ ሥፍራውን ፡ ከለቀቅን ፡ ጀርመኖች ፡
ሊቆርጡን ፡ እንደተቃረቡ ፡ ተሰማን ። ምክን
ያቱም ፡ ከግራ ፡ በኩል ፡ የታንኮች ፡ መንኳኳት ፡
በስተቀኝና ፡ በግንባር ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ተኩ

ሱ ፡ ቅርብ ፡ መሆኑ ፡ ስለተሰማን ፡ ሁኔታው ፡
ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ አልነበረም ።
«ሶኮሎቭ ፡ በዚህ ፡ መሃከል ፡ ልታልፍ ፡ ት
ችላለህ ፡ ወይ?» ሲል ፡ አዛዣችን ፡ ጠየቀኝ ። መጠ
የቅ ፡ ባላስፈለገም ፡ ነበር ። ባልንጀሮቼ ፡ ሲገዱሉ ፡
እጄን ፡ አጣምሬ ፡ ቁጭ ፡ ብዬ ፡ ላይ ፡ ነውን?
«ምንድር ፡ ነው ፡ የምትናገረው ፡ በማንኛውም
መንገድ ፡ ማለፍ ፡ አለብኝ ፡» አልሁት ።
«እንግዲያው ፡ ምን ፡ ትጠብቃለህ ፡» አለኝ ። ወ
ዲያውኑ ፡ ካሚዎኔ ፡ ላይ ፡ ቁጭ ፡ ብዬ ፡ መን
ገዴን ፡ ጀመርሁ ። በሕይወቴ ፡ ሙሉም ፡
እንዲህ ፡ ባለ ፡ ፍጥነት ፡ ነድቼ ፡ አላውቅም ፡
ካሚዎኔ ፡ ላይ ፡ የተጫነውም ፡ የሚፈነዳ ፡ ነ
ገር ፡ ስለሆነ ፡ በመጠንቀቅ ፡ መንዳት ፡ እንደ
ሚገባኝ ፡ ባውቀውም ፡ ባልንጀሮቼ ፡ ባዶ ፡ እ
ጃቸውን ፡ ሊዋጉ ፡ እንደማይችሉ ፡ ስለተረዳ
ሁት ፤ ምንም ፡ እንኳ ፡ መንገዱ ፡ ሁሉ ፡ በመ
ድፎች ፡ ጥይት ፡ ምሕረት ፡ ውስጥ ፡ ቢሆን
ም ፤ በዝግታ ፡ ለመሄድ ፡ አልቻልሁም ። ስድ
ስት ፡ ኪሎሜትር ፡ ተጉዤ ፡ ከሥፍራው ፡ እን
ደተቃረበሁ ፡ መድፉ ፡ ወዳለበት ፡ ቦታ ፡ ለመ
ሄድ ፡ ተዳፋቱን ፡ ለመያዝ ፡ ስጀምር ፡ ምን ፡
አየሁ? የኛ ፡ እግረኛ ፡ ጦር ፡ በመንገዱ ፡
ግራና ፡ ቀኝ ፡ ሜዳውን ፡ አቋርጠው ፡ ወደኋላ ፡



ሲሸሹና ፡ የጠላትም ፡ የመድፍ ፡ ጥይት ፡ በዙ
ሪያቸው ፡ ሲፈነዳ ፡ አየሁ ። ምን ፡ ማድረግ ፡
አለብኝ ? አልሁ ፡ ወደኋላ ፡ ለመመለስ ፡ አልቻ
ልሁም ፡ እንዴትስ ፡ አድርጌ? መድፉ ፡ ካለበ
ት ፡ ቦታ ፡ ለመድረስ ፡ የቀረኝ ፡ አንድ ፡ ኪሎ
ሜትር ፡ ብቻ ፡ ነበር ፡ መንገዱንም ፡ ተጠምዝ
ዤ ፡ ባለኝ ፡ ፍጥነት ፡ ሁሉ ፡ መሄድ ፡ ጀምሬ ፡
ነበር ፡ ግን ፡ ለመድረስ ፡ አልቻልሁም ። በሩ
ቅ ፡ አሻግሮ ፡ የሚመታ ፡ የመድፍ ፡ ጥይት ፡ ከ
ካሚዎኑ ፡ አጠገብ ፡ ፈነዳ ። ድምጹንም ፡ ወይ
ም ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ አልሰማሁም ፡ ነገር ፡ ግን ፡
ራሴ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ሲፈነዳ ፡ ተሰማ
ኝ ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ምኑንም ፡ ላውቀው ፡ አል
ቻልሁም ። እንዴት ፡ እንደተረፍሁና ፡ ከጉር
ጓዱም ፡ ውስጥ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ወድቄ ፡
እንደቆየሁ ፡ ለማወቅ ፡ ፍጹም ፡ አዳገተኝ ። አ
እምሮዬን ፡ እንዳወቅሁ ፡ ዓይኔን ፡ ገለጽሁት ፡
ለመነሳትም ፡ ብሞክር ፡ ጨርሶ ፡ አቃተኝ ፡ ወ
ባ ፡ እንደያዘውም ፡ ሰው ፡ እንዘፈዘፍ ፡ ነበር ፡
እራሴም ፡ ከመንጨዋለሉ ፡ ስላልተመለሰ ፡
በዙሪያዬ ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ ጨለማ ፡ መስሎ ፡
ነበር ፡ የሚታየኝ ። በግራ ፡ ትከሻዬም ፡ በኩል ፡
መሮውን ፡ ይዞ ፡ እንደሚጠርብ ፡ ጠራቢ ፡ ይ
ገተግተኝ ፡ ነበር ። ሁለት ፡ ቀን ፡ ሙሉ ፡ በጹ

ላ ፡ እያባረሩ ፡ እንደደበደቡት ፡ ሰው ፡ ሰውነቴን ፡ ሁሉ ፡ ያመኝም ፡ ጀመር ። በሆዴም ፡ ተምበልብዬ ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ስገላበጥ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ሳስብ ፡ ተቆየሁ ፡ በኋላ ፡ ተነስቼ ፡ ለመቆም ፡ ቻልሁ ። ወዴት ፡ እንደነበርሁና ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ደረሰብኝም ፡ ለማሰብ ፡ አልቻልሁም ። የነገር ፡ ማስታወስ ፡ ችሎታዬም ፡ ለጊዜው ፡ ጠፋብኝ ። ተመልሼ ፡ ለመተኛትም ፡ ፈራሁ ። የተኛሁ ፡ እንደሆነ ፡ እንደገና ፡ ለመነሳት ፡ ያቅተኛል ፡ በማለት ፡ ስለፈራሁ ፡ ቁሜ ፡ ንፋስ ፡ ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ እንደሚያወዛውዘው ፡ ዛፍ ፡ እወዛወዝ ፡ ነበር ።

ራሴን ፡ ካወቅሁ ፡ በኋላ ፡ በዙሪያዬ ፡ ያለውን ፡ ተመለከትሁ ፡ ልቤም ፡ በጉጠት ፡ ተይዞ ፡ እንደተወጠረ ፡ ሁኖ ፡ ተሰማኝ ። ጭኜው ፡ የነበረውም ፡ የመድፍ ፡ ጥይት ፡ በዙሪያዬ ፡ ተበታትኖ ፡ ወድቋል ፡ ሳብ ፡ ብሎም ፡ ከሚዎኔ ፡ ተሰባብሮ ፡ አራት ፡ እግሮቹም ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ተንጨፍርረው ፡ ወድቆ ፡ አየሁት ፤ ጦርነቱም ፡ እኔን ፡ ወደኋላ ፡ ጥሎ ፡ አልፎኝ ፡ እንደሄደ ፡ አወቅሁ ፡ … አዎን ፡ ከጦሩ ፡ ሜዳ ፡ በኋላ ፡ ቀርቻለሁ!

ይህንንም ፡ ከተረዳሁት ፡ በኋላ ፤ ለመናገርም ፡ አላፍርበትም ፤ እግሮቼ ፡ በመጥረቢያ ፡ እ



ንደተቀረጠ ፡ ግንድ ፡ ስለታጠፉ ፡ በቁመቴ ፡ ሙሉ ፡ ወደቅሁ ። ከጠላትም ፡ የጦር ፡ ግንባር ፡ መስመር ፡ በኋላ ፡ ተቀርጬ ፡ መቅረቴን ፡ ተገነዘብሁት ፡ በትክክል ፡ አነጋገርም ፡ የፋሽስቶች ፡ ምርኮኛ ፡ መሆኔን ፡ ተረዳሁት ። ይህ ፡ ጦርነት ፡ ይመስልሃልን ።

አይደለም ፡ ለመረዳትም ፡ ቀላል ፡ አይሆንም ፡ ያለራስህ ፡ ፈቃድ ፡ ምርኮኛ ፡ መሆንህን ፡ ለመረዳት ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ አይደለም ። በራሱ ፡ ላይ ፡ የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ነገር ፡ ካልደረሰበት ፡ በስተቀር ፡ ለማስረዳት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይጠይቃል ።

ስለዚህ ፡ እዚያው ፡ ዝም ፡ ብዬ ፡ ተኛሁ ፡ ወዲያውኑም ፡ የታንኮችን ፡ መንኳኳት ፡ ሰማሁ ። የመድፍ ፡ ጥይት ፡ ጭኜ ፡ ወደ ፡ መጣሁበት ፡ አቅጣጫም ፡ አራት ፡ የጀርመን ፡ መሃከለኛ ፡ ታንኮች ፡ በሙሉ ፡ ፍጥነት ፡ ባጠገቤ ፡ አልፈው ፡ ሄዱ ። ይህስ ፡ እንዴት ፡ ሁኖ ፡ ነው ፡ የሚሰማህ? ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ትራክተሮች ፡ መድፎችንና ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ወጥ ፡ ቤት ፡ እየጐተቱ ፡ መጡ ፡ ከዚያም ፡ ቀጥሎ ፡ ቁጥራቸው ፡ ብዙ ፡ ያልሆነ ፡ ካንድ ፡ ጓድ ፡ የማይበልጥ ፡ እግረኛ ፡ ጦር ፡ መጣ ። ሰረቅ ፡ አድርጌ ፡ ከተመለከትኋቸው ፡ በኋላ ፡ ለማየት ፡ ነፍሴ ፡ ስለጠላ

ቸው ፡ ፊቴን ፡ ከመሬቱ ፡ ጋር ፡ አጣብቄ ፡ ተ
ኛሁ ።

ሁሉም ፡ ሄደዋል ፡ ብዬ ፡ ለማየት ፡ ራሴን ፡
ቀና ፡ ባደርገው ፡ መቶ ፡ እርምጃ ፡ ከኔ ፡ ሳብ ፡
ብሎ ፡ ስድስት ፡ መትረየስ ፡ ተኳሾች ፡ ሲሄዱ ፡
አየሁ ። ወዲያውኑ ፡ መንገዱን ፡ እጥፍ ፡ ብለ
ው ፡ ወደኔ ፡ አቅጣጫ ፡ ሲያመሩ ፡ አየሁ ፡ እነ
ሱም ፡ አይነጋገሩም ፡ ነበር ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡
ተኝቼ ፡ መሞት ፡ ስላልፈለግሁ ፡ አስቀድሜ ፡
ቁጭ ፡ አልሁ ፡ በኋላም ፡ ቆምሁ ። ከነሱ ፡ አን
ደኛው ፡ ከኔ ፡ ጥቂት፡ እርምጃዎች ፡ ሳብ ፡ ብሎ ፡
ቁሞ ፡ ጠበንጃውን ፡ ከትከሻው ፡ አወረደ ።
በዚህም ፡ ጊዜ ፡ አልፈራሁም ፡ ልቤም ፡ አል
ባባም ፡ የሰውም ፡ አፈጣጠር ፡ ገረመኝ ። እሱ
ንም ፡ ከተመለከትሁት ፡ በኋላ ፡ ሊተኩስብኝ ፡
ነው ፤ የሚመታኝስ ፡ ከምን ፡ ላይ ፡ ነው? ብዬ ፡
አስብ ፡ ነበር ። «ራሴ ፡ ላይ ፡ ነው ፡ ወይስ ፡
ደረቴን ፡ ነው? ከማንኛው ፡ አካላቴ ፡ ላይስ ፡
ቢመታኝ ፡ ምን ፡ ቸገረኝ ፡» አልሁ ።

ወጣት ፤ አቋቋሙ ፡ መልካም ፤ ጸጉሩ ፡ ጥቁ
ር ፤ ከንፈሩ ፡ ስስና ፡ አይኖቹም ፡ ተንኰልና ፡
ክፋት ፡ የተሞላባቸው ፡ አስተያየት ፡ ያሉት ፡
ነበር ። ይህ ፤ ሰው ፡ ለመግደል ፡ ካሰበ ፡ የማያ
መነታ ፡ መሆኑ ፡ በሃሳቤ ፡ ተሰማኝ ። በእር



ግጥም ፡ ጠበንጃውን ፡ ደገነ ። እኔም ፡ ምንም ፡
ሳልናገር ፡ ዓይኑን ፡ አተኩሬ ፡ ተመለከትሁት ።
በዚህን ፡ ጊዜም ፤ ሲመለከቱት ፡ በእድሜ ፡ ከ
ሱ ፡ ከፍ ፡ የሚል ፡ ምናልባት ፡ ያስር ፡ አለቃ ፡
ይሆናል ፤ አንድ ፡ ነገር ፡ በከፍተኛ ፡ ቃል ፡ ተ
ናገረና ፡ እሱን ፡ ወደ ፡ ጐን ፡ ገፋ ፡ አድርጐ ፡
ወደኔ ፡ ቀረበ ፡ በቋንቋው ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ለፈ
ለፈና ፡ ጉልበቴን ፡ ለመሞከር ፡ በማሰብ ፡ የቀ
ኝ ፡ እጄን ፡ ለማጠፍ ፡ ሞከረ ። ከተረዳውም ፡ በ
ኋላ ፡ «አሃ!» አለና ፡ ወደ ፡ ጸሐይ ፡ መግቢያ ፡
ያለውን ፡ መንገድ ፡ በጣቱ ፡ ጠንቁሎ ፡ አሳየ
ኝ ፡ እንደገባኝም ፡ «ወደዚያ ፡ ሂድ ፤ ለኛ ፡ ራ
ይህ ፡ ትሠራለህ ፡» ያለ ፡ መሰለኝ ። ቆጣቢ ፡
ይመስላል!

ግን ፡ ጠጉረ ፡ ጥቁሩ ፡ ወጣት ፡ ያደረግኋ
ቸውን ፡ ቡት ፡ ጫማዎች ፡ ስለፈለጋቸው ፤ ምክ
ንያቱም ፡ አዲስና ፡ ጥሩ ፡ ስለነበሩ ፡ ነው ፤ «አ
ውልቃቸው!» የሚል ፡ ትእዛዝ ፡ በጣት ፡
ምልክት ፡ አሳየኝ ፡ እኔም ፡ ለማውለቅ ፡ ቁጭ ፡
አልሁ ፡ እንዳወለቅኋቸውም ፡ ሰጠሁት ። ከጄ
ም ፡ ነጥቆ ፡ ወሰዳቸው ። በዚህን ፡ ጊዜም ፡ የ
እግር ፡ ሹራቦቼንም ፡ አውጥቼ ፡ ለመስጠት ፡
እጄን ፡ ዘረጋሁለት ። እየማለ ፡ ጮኸ ፡ ጠበንጃ
ውንም ፡ እንደገና ፡ ደገነብኝ ። የተቀሩት ፡ ግን ፡

እየሳቁ ፡ ጮሁበት ። ተነስተውም ፡ ተጓዙ ። ይህ ፡ ጠጉረ ፡ ጥቁር ፡ ግን ፡ ከመንገዱ ፡ እስኪገባ ፡ ድረስ ፡ ሶስት ፡ ጊዜ ፡ እየተገላመጠ ፡ አየኝ ። ዓይኖቹም ፡ እንደተቆጣ ፡ የተኩላ ፡ ቡችላ ፡ ያንጸባርቁ ፡ ነበር ። ምናልባት ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ እኔ ፡ የሱን ፡ ጫማ ፡ የወሰድሁበት ፡ እንጅ ፡ እሱ ፡ የኔን ፡ ጫማ ፡ የወሰደብኝ ፡ መስሎ ፡ አይታየውም ፡ ይሆናል ።

እንዲህ ፡ ግን ፡ አልሆነም ። ኃይለኛ ፡ በሆነ ፡ በቮሮኔዥ ፡ ስድብ ፡ ሰድቤያቸው ፡ ወደምዕራብ ፡ ለመሔድ ፡ መንገዴን ፡ ቀጠልሁ ። በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ በሰዓት ፡ ከአንድ ፡ ኪሎሜትር ፡ ይበልጥ ፡ ለመሄድ ፡ አልቻልሁም ፡ በቀጥታ ፡ ለመሄድ ፡ ስትሞክር ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ከመንገዱ ፡ ዳር ፡ ወደሌላው ፡ ዳር ፡ ስለሚገፋህ ፡ የሰከርህ ፡ ያስመስልህ ፡ ነበር ። ትንሽም ፡ እንደተጓዝሁ ፡ እኔ ፡ ከነበርሁበት ፡ የጦር ፡ ክፍል ፡ እንደኔው ፡ ተማርከው ፡ ከሚነዱት ፡ እስረኞች ፡ ዘንድ ፡ ደረስሁ ። ምናልባት ፡ አስር ፡ የጀርመን ፡ መትረየስ ፡ ተኳሾች ፡ ብቻ ፡ ነበሩ ፡ የሚጠብቋቸው ። ከምርኮኞቹ ፡ ግንባር ፡ ይሄድ ፡ የነበረው ፡ ወደኔ ፡ መጥቶ ፡ ምንም ፡ ሳይናገር ፡ እራሴ ፡ ላይ ፡ በሰደፍ ፡ መታኝ ። ያን ፡ ጊዜ ፡ ብወድቅ ፡ ኑሮ ፡ በጥይት ፡



እዚያው ፡ ከመሬት ፡ ጋር ፡ እንዳያጣብቀኝ ፡ በማለቱ ፡ ወዲያውኑ ፡ የኛዎቹ ፡ ደጋግፈው ፡ አንስተው ፡ ወደ ፡ መሃል ፡ አገቡኝ ፡ ግማሾቹም ፡ ለትንሽ ፡ ጊዜ ፡ ደግፈው ፡ አንደያዙኝ ፡ ነበር ። አእምሮዬ ፡ ሲመለስ ፡ አንደኛው ፡ በሹክሹክታ ፡ ቃል ፡ ስለእግዚአብሔር ፡ ብለህ ፡ እንዳትወድቅ! አለኝ ። እስኪደክምህ ፡ ድረስ ፡ ጠንክረህ ፡ መሄድ ፡ አለብህ ፡ አለበለዚያ ፡ ግን ፡ ይገሉሃል ፡ ብሎ ፡ አስጠነቀቀኝ ። እኔም ፡ መንገዴን ፡ ቀጠልሁ ።

ጸሐይም ፡ ልትጠልቅ ፡ስትል ፡ አንድ ፡ ሃያ ፡ የሚሆኑ ፡ መትረየስ ፡ ተኳሽ ፡ ተጨማሪ ፡ ዘበኞች ፡ በካሚዎን ፡ አመጥዋቸውና ፡ በፍጥነት ፡ እርምጃ ፡ ይነዱን ፡ ጀመር ። በጣም ፡ የቆሰሉት ፡ ከጤነኞች ፡ ጋር ፡ እኩል ፡ ለመራመድ ፡ ባለመቻላቸው ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ተገደሉ ። አንድ ፡ ሁለቱም ፡ ለማምለጥ ፡ ሞከሩ ፡ ግን ፡ የጨረቃ ፡ ብርሃን ፡ ባለበት ፡ ጊዜ ፡ ካንድ ፡ ማይልስ ፡ ርቀት ፡ በላይ ፡ ለመታየት ፡ መቻሉን ፡ ዘንግተው ፡ ኑሮ ፡ እነሱም ፡ ተገደሉ ። በእኩለ ፡ ሌሊት ፡ ግማሹ ፡ ከተቃጠለ ፡ መንደር ፡ ደረስን ። ክቡ ፡ ጣራ ፡ ከፈረሰው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥም ፡ አገቡን ፡ ለጐናችን ፡ የምናነጥፈው ፡ ሳር ፡ ከላይም ፡ የምንደርበው ፡ የወታደር ፡ ካፖርት ፡ እን

ኳ ፡ ሳይኖረን ፡ የወታደር ፡ ልብስ ፡ ብቻ ፡ እን ደለበስን ፡ ከድንጋዩ ፡ ወለል ፡ ላይ ፡ ተኝተን ፡ አደርን ። አንዳንዳችንም ፡ ከጥጥ ፡ የተሠራ ፡ ሸሚዝ ፡ ብቻ ፡ እንጅ ፡ ኮት ፡ እንኳ ፡ ያልደረ ብን ፡ ነበርን ። ከነሱም ፡ አብዛኛዎቹ ፡ ዝቅተ ኛ ፡ መኮንኖች ፡ ነበሩ ። ኮታቸውንም ፡ ያወለ ቁበት ፡ ምክንያት ፡ መኮንኖች ፡ ወይም ፡ ተራ ዎች ፡ መሆናቸው ፡ እንዳይታወቅ ፡ ነበር ። እ ንዲሁም ፡ ከመድፈኛ ፡ ክፍል ፡ የነበሩት ፡ ኮታ ቸውን ፡ አውልቀው ፡ ሲታኮሱ ፡ ስለተማረኩ ፡ ኮታቸውን ፡ አልለበሱም ፡ ነበር ።

ያንለት ፡ ማታ ፡ ዝናብ ፡ ስለጣለ ፡ ሁላችን ም ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ በስብሰን ፡ ነበር ። የጣ ራውም ፡ አጋማሽ ፡ በቦምብ ፡ ወይም ፡ በከባ ድ ፡ መድፍ ፡ ጥይት ፡ ሲፈርስ ፡ የቀረው ፡ ደግ ሞ ፡ በፍንጣሪው ፡ ፈራርሶ ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ከቤት ፡ ክርስቲያኑ ፡ ውስጥ ፡ ምንም ፡ ደረቅ ፡ ቦታ ፡ አልነበረም ። በጐች ፡ በጨለማ ፡ ጉሮኖ ዋቸው ፡ ሌሊቱን ፡ እንደሚያሳልፉት ፡ እኛም ፡ ሌሊቱን ፡ ሙሉ ፡ በዚኸው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያ ን ፡ ውስጥ ፡ አሳለፍነው ። በእኩለ ፡ ሌሊትም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እጄን ፡ ሲነካኝ ፡ ተሰማኝ ። እ ሱም ፡ «ከምን ፡ ላይ ፡ ነው ፡ የቆሰልኸው ፡ ኮ ምሬድ ፡ (ባልንጀራዬ ፡)?» ብሎ ፡ ጠየቀኝ ፡



«ለምንድር ፡ ነው ፡ የምትጠይቀኝ ፡ ጓዴ?» አል ሁት ። «እኔ ፡ ሐኪም ፡ ነኝና ፡ ምናልባት ፡ ል ረዳህ ፡ እችል ፡ ይሆናል ፡» አለኝ ። ያን ፡ ጊዜ ፡ ግራ ፡ ትከሻዬ ፡ አብጦ ፡ በጣም ፡ ያሰቃየኛል ፡ አልሁት ። «ኮትህንና ፡ ሸሚዝህን ፡ አውልቅ ፡» አለኝ ። እንደነገረኝ ፡ ካወለቅሁ ፡ በኋላ ፡ በቀ ጭን ፡ እጣቱ ፡ ትከሻዬን ፡ እየዳሰሰ ፡ «ያምሃ ል!» አለ ። ጥርሴን ፡ እያፋጨሁ ፡ «አንተ ፡ የ ከብት ፡ እንጅ ፡ የሰው ፡ ሐኪም ፡ አይደለህም ፡ የሚያመኝን ፡ ቦታ ፡ ለምን ፡ ነው ፡ የምትጫ ነው ፡ አንተ ፡ ርጎራጌ ፡ ቢስ?» አልሁት ። እሱ ም ፡ መልሶ ፡ በንዴት ፡ ቃል ፡ «አንተ ፡ ያለብ ህ ፡ አፍህን ፡ መዝጋት ፡ ብቻ ፡ ነው! እንዲህ ፡ እየተናገርኸኝ! ትንሽ ፡ ቆይ ፡ ብቻ ፡ ባንድ ፡ ደቂቃ ፡ ውስጥ ፡ ይበልጥ ፡ ነው ፡ የሚያምህ ፡» ብሎ ፡ በኃይል ፡ እጄን ፡ አንዝሮ ፡ ቢስበው ፡ ከዓይኔ ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ፍንጥርጣሪ ፡ የመሰሉ ፡ ነገሮች ፡ ብልጭ ፡ አሉብኝ ።

ነፍሴ ፡ መለስ ፡ እንዳለልኝ ፡ «ምንድር ፡ ነው ፡ ያደረግኸው ፡ አንተ ፡ ፋሽስት ፡ ክንዴ ፡ ተሰባብሮ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ትስበዋለህ ፡» ብዬ ፡ ጠየቅሁት ። እሱም ፡ ሳቅ ፡ ብሎ ፡ «እጅህን ፡ ስስበው ፡ በቀኙ ፡ ትመታኛለህ ፡ ብዬ ፡ ሰግቼ ፡ ነበር ፡ አንተ ፡ ግን ፡ ጠባየ ፡ መልካም ፡ ሰው ፡

ትመስላለህ ፡» አለኝ ። «ውልቃት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡
እንጅ ፡ ክንድህ ፡ አልተሰበረም ፡ አሁን ፡ ግን ፡
ከቦታው ፡ ተመልሶ ፡ ገብቷል ። ትንሽ ፡ ተሻ
ለህ?» ሥቃዩ ፡ ለቀቅ ፡ ስላለልኝ ፡ ከሙሉ ፡ ልቤ ፡ አ
መሰገንሁት ። እሱም ፡ በቀስታ ፡ «የቆሰለ ፡
አለን?» እያለ ፡ በጨለማው ፡ ሄደ ። እውነተኛ ፡
ሐኪም ፡ ነው ። ጥቅጥቅ ፡ ባለው ፡ ጨለማ ፡
ከቦታ ፡ ወደ ፡ ቦታ ፡ እየዞረ ፡ ታላቅ ፡ ሥራው
ን ፡ ከመሥራት ፡ አላጓደለም ።

ጸጥታ ፡ ቢስ ፡ ሌሊት ፡ ነበር ። ወደ ፡ ጓሮ ፡
እንኳ ፡ እንድንወጣ ፡ አልፈቀዱልንም ፡ ይህ
ንንም ፤ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ውስጥ ፡ ጥን
ድ ፡ በጥንድ ፡ ሲያስገቡን ፡ የዘበኞች ፡ አላፊ ፡
ነግሮናል ። ከክርስቲያኖች ፡ መሃከል ፡ አንዱ ፡
ወገቡን ፡ ስለተሰማው ፡ ወደውጭ ፡ ለመውጣ
ት ፡ ተገደደ ። ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሲጣጣር ፡ ከቆየ ፡
በኋላም ፡ ያለቅስ ፡ ጀመር ። «ክርስቲያን ፡ ነኝ ፡
አማኝም ፡ ነኝ ፡ ስለዚህ ፡ የተቀደሰውን ፡ ቦታ ፡
ላረክሰው ፡ አልፈቅድም! ምን ፡ ላድርግ ፡ እ
ባካችሁ?» አለ ። ምን ፡ ዓይነት ፡ ሰዎች ፡ እን
ደ ፡ ነበርን ፡ ታውቀዋለህ ። ጥቂቶቹ ፡ ሳቁ ፡ ጥ
ቂቶቹ ፡ ተራገሙ ፡ የተቀሩት ፡ ደግሞ ፡ በመቀ
ልድ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ ምክር ፡ ሰጡት ።
ለጊዜው ፡ እንኳ ፡ ቢያስደስተንም ፡ መጨረሻ



ው ፡ የሚያሳዝን ፡ ነገር ፡ ሆነ ። በሩን ፡ እየደበ
ደበ ፡ እንዲያስወጡትም ፡ ጠየቀ ። በዚህን ፡ ጊ
ዜ ፡ አንዱ ፡ ፋሽስት ፡ መትረየስ ፡ ጠበንጃውን ፡
ተኰሰ ። ክርስቲያኑንና ፡ ሌሎች ፡ ሶስት ፡ ሰዎ
ች ፡ ሲገድል ፡ አንዱን ፡ ክፉኛ ፡ አቆሰለው ፡
እሱም ፡ ሲነጋ ፡ ሞተ ።

የሞቱትን ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ጥግ ፡ ጐተትንና ፡
አጀማመሩ ፡ የሚያሳዝን ፡ በመሆኑ ፡ በጸጥታ ፡
ቁጭ ፡ ብለን ፡ ለራሳችን ፡ እናስብ ፡ ጀመር ።
ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላም ፡ ከወዴት ፡ እንደመጣ
ንና ፡ እንዴትስ ፡ እንደተማረክን ፡ በሹክሹክ
ታ ፡ እንጠያየቅ ፡ ጀመርን ። ባንድ ፡ ጓድ ፡ ወ
ይም ፡ ባንድ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ የነበሩ ፡ ሰዎች ፡
በዝግታ ፡ በጨለማው ፡ ውስጥ ፡ ይጠራሩ ፡ ጀ
መር ። ካጠገቤ ፡ ደግሞ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ሲነ
ጋገሩ ፡ ሰማሁ ። «ነገ ፡ ወደ ፡ እሩቅ ፡ ቦታ ፡ ከ
መውሰዳቸው ፡ በፊት ፡ አስልፈውን ፡ የፖሊ
ቲካ ፡ መሪዎችን ፤ ኮሙኒስቶችንና ፡ አይሁዶ
ችን ፡ የጠሩ ፡ እንደሆን ፡ ራስህን ፡ ለመደበቅ ፡
አትሞክር ፡ ጓድ ፡ አዛዦችን ፡ ሆይ ። ምንም ፡
ቢሆን ፡ 'አታመልጥም ። ኮትህን ፡ በማውለቅ
ህ ፡ ተራ ፡ ወታደር ፡ መስለህ ፡ ልታመልጥ ፡
ነውን? ይህ ፡ አይምሰልህ ! ባንተ ፡ ምክንያት ፡
እኔ ፡ አልሰቃይም ። ከሁሉ ፡ በፊት ፡ አስቀድ

ሜ ፡ የማጋልጥህ ፡ እኔ ፡ ነኝ ። አንተ ፡ ኮሙኒስ
ት ፡ እንደሆንህ ፡ አውቃለሁ ። በፓርቲው ፡ ው
ስጥ ፡ እንድገባ ፡ እንዴት ፡ ትጣጣር ፡ እንደነ
በረ ፡ አስታውሳለሁ ፡ ስለዚህ ፡ አሁን ፡ መል
ሱን ፡ መስጠት ፡ አለብህ ።» ይህን ፡ የሚናገ
ረው ፡ በስተግራ ፡ በኩል ፡ ከአጠገቤ ፡
ተቀምጦ ፡ የነበረው ፡ ነው ፡ ከሱ ፡ ቀጥሎ ፡
አንድ ፡ ድምጽ ፡ ቀጭን ፡ ሰው ፡ መልስ ፡ ሰጠ ።
«ክሪዥኔቭ ፡ ድሮውንም ፡ አንተ ፡ የማትረባ ፡
እንደሆንህ ፡ እጠረጥር ፡ ነበር ። በተለይም ፡
ያልተማርህ ፡ መስለህ ፡ ከፓርቲው ፡ አልገባ
ም ፡ ያልህ ፡ ጊዜ ። ግን ፡ ቢሆንም ፡ እንደዚህ ፡
ከዳተኛ ፡ ትሆናለህ ፡ ብዬ ፡ ከቶ ፡ አላሰብሁም ።
አስራ ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ እስኪሞላህ ፡ ድረስ ፡
ስትማር ፡ አልነበረም?» «አዎን ፡ ተምሬያለሁ ፡
ታዲያስ?» ለብዙ ፡ ጊዜም ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ቆ
ዩ ። የጓድ ፡ አዛዡም ፡ በዝግታ ፡ «ኮምሬድ ፡
(ባልንጀራ ፡) ክሪዥኔቭ ፡ አሳልፈህ ፡ አትስጠኝ ።»
ብሎ ፡ ሲናገር ፡ በድምጹ ፡ ልለየው ፡ ቻልሁ ።
ያኛው ፡ ግን ፡ በዝግታ ፡ ሳቀና ፡ «ባልንጀሮች
ህን ፡ ከወዲያ ፡ ማዶው ፡ መስመር ፡ ጥለሃቸው ፡
መጥተሃል ፡ እኔ ፡ ባልንጀራህ ፡ አይደለሁምና ፡
ከቶ ፡ አትለምነኝ ፡ በማንኛውም ፡ መንገድ ፡
እንደማጋልጥህ ፡ እወቅ ፡ አለው ። እኔ ፡ የማም



ነው ፡ ከሁሉ ፡ በፊት ፡ እራሴን ፡ ማዳን ፡ ብቻ ፡
ነው ፡» አለ ።

ንግግራቸውን ፡ አቋረጡ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡
ዝቅተኛና ፡ የተዋረደ ፡ ተግባር ፡ ለመፈጸም ፡
በማሰቡ ፡ሙሉ ፡ ሰውነቴን ፡ ቀፈፈኝና ፡ አን
ቀጠቀጠኝ ። «አይሆንም ፡ አለቃህን ፡ አሳል
ፈህ ፡ እንድትሰጠው ፡ አልፈቅድም ፡ ብዬ ፡ አ
ሰብሁ ። ከዚህ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ተጕት
ተህ ፡ ትወጣለህ ፡ እንጅ ፡ በሕይወት ፡ አትወ
ጣም!» አልሁ ። ብርሃን ፡ ወገግ ፡ ሲልም ፡ ብ
መለከት ፡ አንድ ፡ ወፈር ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ እጆቹ
ን ፡ ተንተርሶ ፡ በጀርባው ፡ ተንጋሎ ፡ ተኝቷል ፡
ከአጠገቡም ፡ አፍንጫ ፡ አሻዳና ፡ ቀና ፡ ያለ ፡
የገረጣ ፡ ወጣት ፡ ሸሚዝ ፡ ብቻ ፡ ለብሶ ፡ ጉል
በቱን ፡ ታቅፎ ፡ ቁጭ ፡ ብሏል ። «ይህ ፡ ወጣ
ት ፡ ብቻውን ፡ ይህን ፡ ዘረጦ ፡ ሊያጠቃው ፡
አይችልምና ፡ እኔው ፡ እራሴ ፡ መጨረስ ፡ አለ
ብኝ ፡ » ብዬ ፡ አሰብሁ ።

ወጣቱንም ፡ ነካ ፡ አደረግሁና ፡ የጓዱ ፡ አዛ
ዥ ፡ አንተ ፡ ነህን? ብዬ ፡ በሹክሹክታ ፡ ጠየ
ቅሁት ። ምንም ፡ ሳይናገር ፡ እራሱን ፡ በማነ
ቃነቅ ፡ መለሰልኝ ። «ያ ፡ እዚያ ፡ በጀርባው ፡
ተንጋሎ ፡ ያለው ፡ ነው ፡ ወይ ፡ አሳልፎ ፡ ሊሰ
ጥህ ፡ የፈለገው?» አልሁት ። እንደገና ፡ እራሱ

ን ፡ በማነቃነቅ ፡ አዎን ፡ አለኝ ። ግድየለም ፡
እንዳይፈራገጥ ፡ እግሩን ፡ አጠንክረህ ፡ ያዝ!
ፈጠን ፡ በል ! አልሁት ። ዘልዬም ፡ ጉሮሮው
ን ፡ በጣቶቼ ፡ አንቄ ፡ ይዝሁት ። ለመጮህ ፡
እንኳ ፡ ጊዜ ፡ አልሰጠሁትም ። ለትንሽ ፡ ደቂቃ
ዎችም ፡ ይዤው ፡ ቁጭ ፡ ብዬ ፡ ቆየሁና ፡ ለቀ
ቅሁት ። ምላሱም፡ ተጐልጉሎ ፡ ወጥቶ ፡ ነበር ።
ሆኖም፡ አንድ ፡ ከሃዲ ፡ ተቀነሰ ።

እንደ ፡ እባብ ፡ የመሰለ ፡ አስጸያፊ ፡ አው
ሬ ፡ እንጅ ፡ ሰው ፡ የገደልሁ ፡ ስላልመሰለኝና ፡
አሳቤም ፡ ስለተሳቀቀ ፡ እጄንም ፡ ለመታጠብ ፡
ፈለግሁ ። በሕይወቴ ፡ ሙሉ ፡ ሰው ፡ ስገድል ፡
ይህ ፡ የመጀመሪያዬ ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ወዲያውም ፡
የሃገራችንን ፡ ልጅ ፤ የሃገራችን ፡ ልጅ? ግን ፡ እ
ሱ ፡ የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ሰው ፡ አልነበረም ። እሱ
ም ፡ ከሃዲ ፡ በመሆኑ ፡ ከጠላት ፡ የባሰ ፡ ሰው ፡
ነበር ። ከዚያም ፡ ተነስቼ ፡ የጓድ ፡ አዛዡን ፡
«ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ሰፊ ፡ ነውና ፡ ይህን ፡ ቦታ ፡
ለቀን ፡ እንሂድ ፡» አልሁት ።

ክሪኘርኔቭ ፡ እንዳለውም ፡ በጥዋት ፡ ከቤተ ፡
ክርስቲያኑ ፡ አስወጥተውን ፡ በሰልፍ ፡ ካቆሙ
ን ፡ በኋላ ፡ በባለመትረይስ ፡ ወታደሮች ፡ ተከ
በብን ። ሶስት ፡ የኤስ ፡ ኤስ ፡ መኮንኖችም ፡ ከ
መሃከላችን ፡ አደገኞች ፡ መስለው ፡ የተሰሙዋ



ቸውን ፡ ለመምረጥ ፡ ጀመሩ ። ኮሙኒስት ፡ ማ
ን ፡ ነው ፡ መኮንንስ ፡ ማን ፡ ነው ፡ የፖሊቲካ ፡
መሪስ ፡ ማን ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ቢጠይቁም ፡ ማንን
ም ፡ ሊያገኙ ፡ አልቻሉም ። ምክንያቱም ፡ ቅር
ብ ፡ ግማሽ ፡ የምንሆንዎች ፡ ኮሙኒስት ፡ ስለ
ነበርን ፡ መኮንኖችና ፡ የፖሊቲካ ፡ መሪዎችም ፡
ስለነበሩ ፡ ከመሃከላችን ፡ የተልከሰከሰ ፡ ጠባ
ይ ፡ ኑሮት ፡ አጋልጦ ፡ የሚሰጥ ፡ አልተገኘም ።
ከሁለት ፡ መቶ ፡ በላይ ፡ ከነበርነውም ፡ ውስ
ጥ ፡ አራት ፡ ብቻ ፡ አውጥተው ፡ ወሰዱ ። ይሄ
ውም ፡ ከተራ ፡ ወታደሮች ፡ ውስጥ ፡ ሲሆን ፡
አንድ ፡ አይሁድና ፡ ሶስት ፡ ሩሲያዎች ፡ ናቸው ።
ሩሲያዎችም ፡ እንዲህ ፡ ካለ ፡ መከራ ፡ ላይ ፡
የወደቁት ፡ ጥቁርና ፡ የተጥመዛመዘ ፡ ጠጉር ፡
ስለነበራቸው ፡ የኤስ ፡ ኤስ ፡ ሰዎች ፡ ወደነሱ ፡
ተጠግተው ፡ አንዱን ፡ «ይሁዲ ፡ ነህ ?» ብለው ፡
ጠየቁት ። ሩሲያዊ ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ መለሰላቸው ፡
ሊሰሙትም ፡ አልፈቀዱም ። ዝም ፡ ብለው ፡
ብቻ ፡ «ውጣ!» ፡ አሉት ።

እነዚህን ፡ ምስኪን ፡ ሰዎች ፡ ተገደሉዋቸ
ው ፡ በኋላ ፡ እኛን ፡ ወደፊት ፡ ነዱን ። እስከ ፡
ፖዝናን ፡ ድረስም ፤ ከሃዲውን ፡ ለማነቅ ፡ የረ
ዳኝ ፡ የጓድ ፡ አዛዥ ፡ ከአጠገቤ ፡ አልተለየም ፡
ነበር ። በመጀመሪያው ፡ የጉዞ ፡ ቀን ፡ አልፎ ፡

አልፎ ፡ እጄንም ፡ ይጨብጠው ፡ ነበር ። ፖዝ
ናን ፡ ስንደርስ ፡ ግን ፡ ነጣጠሉን ።

ከተያዝሁበት ፡ ቀን ፡ አንስቶ ፡ ሁሉ ፡ ጊዜ ፡
ለማምለጥ ፡ እንዳሰብሁ ፡ ነበር ። ከመሞከሬ ፡
በፊት ፡ ግን ፡ ሙከራዬ ፡ እንዳይከሽፍ ፡ እፈልግ ፡ ነበ
ር ። እስከ ፡ ፖዝናን ፡ ድረስ ፡ የምናድረው ፡ በደ
ንበኛ ፡ ሠፈር ፡ ስለሆነ ፡ ተፈላጊ ፡ የሆነው ፡
እድል ፡ ሊገጥመኝ ፡ አልቻለም ። ፖዝናን ፡ ከተ
ባለው ፡ ሠፈር ፡ ግን ፡ ስጠባበቀው ፡ ለነበረው ፡
እድል ፡ ተስማሚ ፡ ሁኖ ፡ አገኘሁት ። በግን
ቦት ፡ ወር ፡ መጨረሻም ፡ ከኛዎቹ ፡ ብዙዎች ፡
በተቅማጥ ፡ በሽታ ፡ ይሞቱ ፡ ስለነበረ ፡ ለሞቱ
ት ፡ እስረኞች ፡ መቃብር ፡ ለመቆፈር ፡ ከሠፈ
ሩ ፡ አጠገብ ፡ ከሚገኘው ፡ ሜዳ ፡ ወሰዱን ። የ
ፖዝናንን ፡ ሸክላማ ፡ አፈር ፡ ስቆፍር ፡ ዘወር ፡
ብዬ ፡ ብመለከት ፡ ሁለቱ ፡ ዘበኞች ፡ ቁጭ ፡ ብ
ለው ፡ ይበላሉ ፡ ሶስተኛው ፡ ቁጭ ፡ ብሎ ፡
ፀሐይ ፡ ሲሞቅ ፡ ሰመመን ፡ (ቀላል ፡ እንቅል
ፍ ፡) እንደያዘው ፡ ስላየሁ ፡ የምቆፍርበትን ፡ አ
ካፋ ፡ አስቀምጬ ፡ ቀስ ፡ ብዬ ፡ ካንድ ፡ ቁጥቋ
ጦ ፡ በኋላ ፡ ተደበቅሁ ። ከዚያ ፡ በኋላም ፡ ወደ ፡
ጸሐይ ፡ መውጫ ፡ አቅጣጫ ፡ ሮጥሁ ።

እነዚህም ፡ ዘበኞች ፡ ለጊዜው ፡ ልብ ፡ አላ
ደረጉኝም ፡ ነበር ። በጣም ፡ ከስቼ ፡ ስለነበረ ፡



በቀን ፡ ውስጥ ፡ አርባ ፡ ኪሎሜትር ፡ ለመሄ
ድ ፡ ጉልበት ፡ ከወዴት ፡ ላግኝ ፤ እራሴንም ፡
ላውቀው ፡ አልቻልሁም ። ቢሆንም ፡ አልተሳ
ካልኝም ። ከዚህ ፡ ከተረገመው ፡ ሠፈር ፡ ብዙ ፡
ከራቅሁ ፡ በኋላ ፡ በአራተኛው ፡ ቀን ፡ ያዙኝ ።
ዳና ፡ በሚያሸቱ ፡ ውሻዎች ፡ አድነው ፡ ካልታ
ጨደ ፡ አጃ ፡ አዝመራ ፡ ውስጥ ፡ አገኙኝ ።

ማለዳም ፡ ቢያንስ ፡ ሶስት ፡ ኪሎሜትር ፡
ከሚሆነው ፡ መስክ ፡ አጠገብ ፡ ስለደረስሁና ፡
በጸሐይ ፡ ብርሃንም ፡ ለማቋረጥ ፡ ስለፈራሁ ፡
እስኪመሽ ፡ ድረስ ፡ በአጃው ፡ አዝመራ ፡ ውስ
ጥ ፡ ተኛሁ ። አጃውንም ፡ እያሸሁ ፡ ስንቅ ፡ እ
ንዲሆነኝ ፡ በኪሴ ፡ ስከት ፡ የውሻ ፡ ጩኸትና ፡
የሞተር ፡ ቢሲክሌት ፡ ድምጽ ፡ ሰማሁ ። ውሾ
ችም ፡ ስለተቃረቡኝ ፡ ልቤ ፡ ከዳኝ ። ፊቴንም ፡
እንዳይነክሱት ፡ እጆቼን ፡ በአንገቴ ፡ ላይ ፡ አ
ድርጌ ፡ ተንበልብዬ ፡ ተኛሁ ። ለብሸው ፡ የነ
በረውንም ፡ ቡትት ፡ ለመቦጫጨቅ ፡ አንድ ፡
ደቂቃ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የወሰደባቸው ። እ
ንደ ፡ ተወለድሁም ፡ እራቁቴን ፡ ቀረሁ ። በአ
ጃው ፡ አዝመራ ፡ ውስጥም ፡ እንደፈቀዱት ፡
ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ጐተቱኝ ። በመጨረሻም ፡
አንድ ፡ ትልቅ ፡ ውሻ ፡ የፊት ፡ እግሮቹን ፡ ከደ
ረቴ ፡ ላይ ፡ አሳርፎ ፡ በጥርሶቹ ፡ ጉሮሮዬን ፡ ለ

መያዝ ፡ ተዘጋጀ ፡ ግን ፡ ወዲያውኑ ፡ አልነከ
ሰኝም ።

ሁለት ፡ ጀርመኖች ፡ በሞተር ፡ ቢሲክሌት ፡
ደረሱ ። አስቀድመው ፡ እስኪበቃቸው ፡ ድረስ ፡
ደህና ፡ አድርገው ፡ ከደበደቡኝ ፡ በኋላ ፡ ውሾ
ችን ፡ እንደገና ፡ ለቀቁብኝ ፡ ሙዳ ፡ ሥጋም ፡ ከ
ሰውነቴ ፡ እየተነጨ ፡ ወደቀ ። በደም ፡ እንደ
ተለወስሁና ፡ እራቁቴን ፡ እንደሆንሁ ፡ ወደ ፡
ሠፈር ፡ መልሰው ፡ ወሰዱኝ ። ለማምለጥ ፡ በመ
ሞከሬም ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ብቻዬን ፡ በተለየ ፡ ሥ
ፍራ ፡ እንድታሰር ፡ ቢደረግም ፡ ገና ፡ በሕይወት ፡
ነበርሁ ። በማንኛውም ፡ መንገድ ፡ ነፍሴን ፡ ለ
ማዳን ፡ ታገልሁ!

እስረኛ ፡ በነበርሁበት ፡ ጊዜ ፡ የደረሰብኝ
ን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ማሰብ ፡ በጣም ፡ አሰቃቂ ፡
ነው ። እዚያና ፡ ጀርመን ፡ አገር ፡ በነበርንበት ፡
ጊዜ ፡ ሰብዓዊ ፡ ርኅራኄ ፡ በሌላቸው ፡ ፍጥረቶ
ች ፡ የደረሰብንን ፡ ሥቃይ ፡ ማሰብና ፡ በነዚህ
ም ፡ ሠፈሮች ፡ በመደብደብ ፡ የሞቱትን ፡ ባል
ንጀሮቻችንን ፡ ባሰብህ ፡ ጊዜ ፡ እንባ ፡ ጉሮሮ
ህን ፡ ያንቀውና ፡ ለመተንፈስም ፡ ያቅትሃል ።

ለሁለት ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ እስረኛ ፡ በነበር
ሁበት ፡ ወቅት ፡ እንዴት ፡ ባለ ፡ አሳዛኝ ፡ መን
ገድ ፡ ይጠብቁንና ፡ ይመግቡን ፡ ነበር! ካንድ ፡



ሠፈር ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ በመዘዋወር ፡ የጀርመን
ን ፡ አገር ፡ አጋማሹን ፡ እንዳደረስሁት ፡ ትዝ ፡
ይለኛል ። ሳክሶኒ ፡ ባለው ፡ የኬሚካል ፡ (መቀ
መሚያ ፡) ፋብሪካ ፡ ስሠራና ፡ በሩህር ፡ የከሰ
ል ፡ ማዕደን ፡ ከሰል ፡ ስቆፍር ፡ ነበር ። በባቫ
ሪያ ፡ ደግሞ ፡ አካፋ ፡ ይዤ ፡ በመሥራት ፡ ወዜ
ን ፡ አንጠፍጥፌያለሁ ። በቱይሪንገንም ፡ እን
ዲሁ ፡ ደክሜያለሁ ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ ያልረ
ገጥሁት ፡ የጀርመን ፡ አፈር ፡ ያለ ፡ አይመስለ
ኝም ። ያገሩ ፡ አቀማመጥ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሲሆን ፡
ግን ፡ ባልንጀሮቻችንን ፡ የሚገድሉበትና ፡ የሚ
ደበድቡበት ፡ መንገድ ፡ የተለየ ፡ አይደለም ።
እነዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ የረገማቸው ፤ የሚሳ
ቡና ፡ በሰውም ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ መዠገር ፡ ተጣ
ብቀው ፡ የሰውን ፡ ደም ፡ መምጠጥ ፡ የለመዱ ፡
አውሬ ፡ ፍጥረቶች ፡ ባገራችን ፡ ማንም ፡ ሰው ፡
አውሬን ፡ እንኳ ፡ በማይመታበት ፡ መንገድ ፡
ነበር ፡ የሚደበድቡን ። በቡጢ ፡ በእርግጫ ፡
በጐማ ፡ ዱላ ፡ ወይም ፡ እንዳጋጣሚ ፡ በእጃቸ
ው ፡ ባገኙት ፡ የብረት ፡ ቁራጭ ፡ ይደበድቡን ፡
ነበር ። በከዘራና ፡ በሰደፍ ፡ የሚደበድቡንን ፡
አታንሳው ።

ሩሲያዊ ፡ በመሆንህ ፤ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ውስ
ጥ ፡ ገና ፡ በሕይወት ፡ በመኖርህና ፡ ለነሱ ፡ በ

መሥራትህ ፡ ምክንያት ፡ ብቻ ፡ ይመቱህ ፡ ነ
በር ። በክፉ ፡ ዓይን ፡ ስለተመለከትሃቸው ፡ ሃ
ሳባቸውን ፡ ስላልተቀበልሃቸው ፡ ትንሽ ፡ የተ
ዛነፈ ፡ ነገር ፡ ስላደረግህም ፡ ይመቱሃል ፡...
ነፍስህ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እንድትወጣ ፡ በመፈ
ለግ ፡ ይደበድቡሃል ፡ የገዛ ፡ ደምህም ፡ ትን ፡
ብሎህ ፡ እስክትሞት ፡ ድረስ ፡ ይቀጠቅጡሃል ።
እንደሚመስለኝ ፡ በሞላው ፡ ጀርመን ፡ ውስ
ጥ ፡ በቂ ፡ ምድጃዎች ፡ ባይኖሩ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡
ሁላችንንም ፡ ባቃጠሉን ፡ ነበር ።

በሄድንበት ፡ ሁሉ ፡ የሚሰጡን ፡ ምግብ ፡
ከእንጨት ፡ ዱቄትና ፡ ከትንሽ ፡ የእህል ፡ ዱ
ቄት ፡ ጋር ፡ ተቀላቅሎ ፡ የተጋገረ ፡ ዳቦ ፡ አን
ድ ፡ ጉንጭ ፡ ውኃና ፡ ለከብቶች ፡ ምግብ ፡ የሚሰ
ጠውን ፡ አታክልት ፡ ነበር ። ባንዳንድ ፡ ቦታ ፡
ደግሞ ፡ የምንጠጣው ፡ ሙቅ ፡ ውኃ ፡ ሲሰጡን ፡
አንዳንድ ፡ ቦታ ፡ ጭራሽ ፡ አይሰጡንም ፡ ነበር ።
ይህን ፡ ሁሉ ፡ መዘርዘር ፡ ምን ፡ ያስፈልጋል ፡
አንተው ፡ እራስህ ፡ ገምተህ ፡ ፍረድ ። ጦርነ
ቱ ፡ ከመጀመሩ ፡ በፊት ፡ ሰማንያ ፡ ስድስት ፡
ኪሎ ፡ እመዝን ፡ ነበርሁ ፡ የበልጉ ፡ ወራት ፡
ሲደርስ ፡ ግን ፡ ሃምሳ ፡ ኪሎ ፡ እንኳን ፡ ልደፍ
ን ፡ አልቻልሁም ። ቆዳዬ ፡ አጥንቶቼን ፡ በየ
ቦታቸው ፡ ሰብስቦ ፡ ከመያዙም ፡ በላይ ፡ እነ



ሱን ፡ እንኳ ፡ ለመሸከም ፡ ያዳግተኝ ፡ ነበር ።
ይሁን ፡ እንጂ ፡ ከመሥራት ፡ በቀር ፡ አንድ ፡
ነገር ፡ ለመናገር ፡ አትችልም ፡ የምንሠራውም ፡
ሥራ ፡ በጣም ፡ ብዙ ፡ ስለነበረ ፡ እንኳን ፡
ለኛ ፡ ለጋሪ ፡ ጐታች ፡ ፈረስም ፡ እንደሚበዛ
በት ፡ ይሰማኛል ።

በመስከረም ፡ ወር ፡ መጀመሪያ ፡ አንድ ፡
መቶ ፡ አርባ ፡ ሁለት ፡ የምንሆነው ፡ የሶቪዬት ፡
የጦር ፡ ምርኮኞች ፡ ኩይስትሪን ፡ አጠገብ ፡ ከ
ሚገኘው ፡ ሠፈር ፡ ቢ-፲፬ ወደሚባለው ፡ ከድ
ሬስዴን ፡ አቅራቢያ ፡ ወደሚገኘው ፡ ሠፈር ፡
አዛወሩን ። በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ሁለት ፡ ሺ ፡ የሚ
ያህሉ ፡ እስረኞች ፡ በሠፈሩ ፡ ነበሩ ። ሁላችንም ፡
የጀርመንን ፡ ድንጋይ ፡ እንቆፍርና ፡ እንሰብር ፡
ነበርን ። እስቲ ፡ ልብ ፡ አድርገው ፡ ሰውነቱን
ና ፡ ነፍሱን ፡ በጣር ፡ ለማቆየት ፡ የቻለው ፡
ሰው ፡ ሁሉ ፡ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ በቀን ፡ ውስ
ጥ ፡ አራት ፡ ሜትር ፡ ኩብ ፡ እንዲሠራ ፡ ተወስ
ኖበት ፡ ነበር ። ከዚህም ፡ ይበልጥ ፡ የሚያስቅ
ቀው ፡ ባንድ ፡ ክፍል ፡ ከነበርነው ፡ ከመ
ቶ ፡ አርባ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ውስጥ ፡ በሁለ
ት ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ሃምሳ ፡ ሰባት ፡ ብቻ ፡ ቀ
ረን ። ስለዚህስ ፡ ምን ፡ ይመስልሃል ፡ ወዳ
ጄ? እየባሰም ፡ ሄደ ። ባልንጀሮቻችንን ፡ እ

4*

ንኳ ፡ ለመቅበር ፡ ጊዜ ፡ አልነበረንም ። ከዚህ
ም ፡ በላይ ፡ ጀርመኖች ፡ ቮልጎግራድን ፡ እን
ደያዙና ፡ ወደሳይቤሪያም ፡ እንደሚገሰግሱ ፡
በሠፈሩ ፡ ይወራ ፡ ጀመር ። አንዱም ፡ ከሌላው ፡
የባሰና ፡ የሚያሳዝን ፡ ሆነ ፡ በባዕድ ፡ አገር ፡
እንድንሞት ፡ የጠየቅናቸው ፡ ይመስል ፡ በሚ
ደርስብን ፡ ሥቃይ ፡ ብዛት ፡ ዓይናችንን ፡ እንኳ ፡
ከመሬት ፡ እንዳናነሳ ፡ ይጨቁኑን ፡ ጀመር ።
የሠፈሩ ፡ ጠባቂ ፡ ዘበኞችም ፡ ሁሉጊዜ ፡ እየ
ጠጡ ፡ ዘፈናቸውንም ፡ እያቀለጡ ፡ ጠቃሚ ፡
በመሰላቸው ፡ ሁሉ ፡ ይደሰቱ ፡ ነበር ።

አንድ ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ምሽት ፡ ከሥራ ፡ ወደ ፡
ጐጆዋችን ፡ ስንመለስ ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ሲዘንብ ፡
በመዋሉ ፡ ቡቱቶዋችን ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ በ
ስብሶ ፡ ነበር ። ከብርዳሙም ፡ ንፋስ ፡ የተነሳ ፡
እንንቀጠቀጥ ፡ ጀመር ። የሚፋጨውንም ፡ ጥ
ርሳችንን ፡ ለማቆም ፡ አቅቶን ፡ ነበር ። የበሰበ
ሰውን ፡ ልብሳችንን ፡ ለማድረቅ ፡ ወይም ፡ ሰ
ውነታችንን ፡ ለማሞቅ ፡ አንድ ፡ ቦታ ፡ አላገ
ኘንም ፡ ከዚህም ፡ በላይ ፡ ያለመጠን ፡ እርቦን ፡
ነበር ። እንደገባንም ፡ ምንም ፡ ምግብ ፡ አልሰ
ጡንም ።

ቡቱቶዬንም ፡ ከላዬ ፡ ላይ ፡ አውልቄ ፡ ወደ
ምተኛበት ፡ ቦታ ፡ ወረወርሁና ፡ «በቀን ፡ አ



ራት ፡ ሜትር ፡ ኩብ ፡ እንድትሠራ ፡ ያዘሃል ፡
አንዱ ፡ ሜትር ፡ ኩብ ፡ እንኳ ፡ ለአንዳችን ፡ መ
ቃብር ፡ ይበዛል ።» ይህን ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የተ
ናገርሁት ። ነገር ፡ ግን ፡ ከመሃከላችን ፡ አንድ ፡
ውሻ ፡ ፍጥረት ፡ ስለነበረ ፡ ይህን ፡ በመመረር ፡
የተናገርሁትን ፡ ወስዶ ፡ ለሠፈሩ ፡ ሹም ፡ አሳ
በቀ ።

የሠፈሩ ፡ አዛዥ ፡ ወይም ፡ እነሱ ፡ እንደሚ
ጠሩት ፡ ላገርፉህረር ፡ ሚዩለር ፡ የሚባል ፡ ቁ
መቱ ፡ ድልድል ፡ ጠጉሩ ፡ ችፍግ ፡ ያለና ፡ የወ
የበ ፡ ጀርመን ፡ ነበር ። ጠጉሩ ፡ ቅንድቡና ፡ ሽ
ፋሽፍቱ ፡ ወይባ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ ዓይነ ፡
ትንንሽ ፡ ነበር ። የሩሲያ ፡ ቋንቋም ፡ እንዳንተ
ና ፡ እንደኔ ፡ ጥሩ ፡ አድርጎ ፡ ይናገራል ፡ ብቻ ፡
የቃል ፡ አጠራሮቹ ፡ ቮልጋ ፡ ተወልዶ ፡ እንዳደ
ገ ፡ ይመስላል ። ስድብ ፡ ሲችል ፡ አያድርስ
ብህ! መዓተኛ ፡ ነበር ። ይህን ፡ ሁሉ ፡ ከወዴት ፡
እንዳወቀው ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ይገርመኝ ፡ ነ
በር ። ከጐጆው ፡ ፊት ፡ አሰልፈው ፡ ያቆሙን
ና ፡ ቀኝ ፡ እጁን ፡ ጀርባው ፡ ላይ ፡ አድርጎ ፡
በኤስ ፡ ኤስ ፡ ሰዎቹ ፡ ተከቦ ፡ በፊታችን ፡ ወዲያ
ና ፡ ወዲህ ፡ ይንጐራደዳል ። እጁንም ፡ እንዳ
ያመው ፡ ከቆዳ ፡ የእጅ ፡ ሹራቡ ፡ ውስጥ ፡ እር

ሳስ ፡ አድርጐ ፡ የያንዳንዱን ፡ ሰው ፡ አፍንጫ ፡
በቡጢ ፡ እያቀመሰ ፡ «የኢንፍሉኤንሳ ፡ ክትባ
ት ፡ ነው ፡» ይል ፡ ነበር ። ይህም ፡ የቀን ፡ ተግ
ባር ፡ ሁኖ ፡ ተለምዷል ። በጠቅላላው ፡ አራት ፡
በተራ ፡ የተሠሩ ፡ ቤቶች ፡ ነበሩ ። አንድ ፡ ቀን ፡
በመጀመሪያው ፡ ቤት ፡ ይጀምራል ፡ በማግስ
ቱ ፡ ደግሞ ፡ የሁለተኛው ፡ ቤት ፡ ተራ ፡ የተቀ
ሩትም ፡ እንዲሁ ፡ ተራቸው ፡ ይደርሳቸዋል ።
የተረገመ ፡ ፍጥረት ፡ ነበር ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እን
ኳ ፡ አስታጉሎ ፡ አያውቅም ። ይህ ፡ ጅል ፡ ያ
ልተረዳው ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ነበር ፡ ተግ
ባሩን ፡ ከመጀመሩ ፡ በፊት ፡ ከፊታችን ፡
ሳብ ፡ ብሎ ፡ ቁሞ ፡ ለመሳደብና ፡ ለመራገም ፡ ይ
ጀምራል ። የሚያውቀውን ፡ ስድብና ፡ እርግማን፡
ሲያወርድብን ፡ ትንሽ ፡ ቀለል ፡ ይለን ፡ ነበር ።
ካፉ ፡ የሚወጡት ፡ ቃሎች ፡ የራሳችን ፡ መስ
ለው ፡ ስለሚሰሙን ፡ ያገራችን ፡ ንፋስ ፡ ይታ
ወሰን ፡ ነበር ። ይህም ፡ የስድብና ፡ የርግማን ፡
ቃል ፡ እንደሚያስደስተን ፡ ቢያውቀው ፡ ኑ
ሮ ፡ ሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ በሩሲያ ፡ ቋንቋ ፡ ሳይናገ
ር ፡ በዚያው ፡ በራሱ ፡ ቋንቋ ፡ ብቻ ፡ ይናገ
ር ፡ ነበር ። ከመሃከላችንም ፡ የኔ ፡ ባልንጀራ ፡
የሆነ ፡ አንድ ፡ መስኮባዊ ፡ ወጣት ፡ ብቻ ፡
ከፉኛ ፡ ይበሳጭ ፡ ነበር ። «እንዲህ ፡ ሲሰድበ



ንና ፡ ሲረግመን ፡ ዓይኔን ፡ ጨፍኜ ፡ ሞስኮ ፡
ከተማ ፡ ካንደኛው ፡ መጠጥ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡
ያለሁና ፡ አንድ ፡ ብርጭቆ ፡ ቢራ ፡ ለመጠጣ
ት ፡ የምፈልግ ፡ መስሎ ፡ ነበር ፡ የሚሰማኝ ፡»
ይላል ።

ስለ ፡ ሜትር ፡ ኩቡ ፡ በተናገርሁ ፡ ማግስ
ት ፡ አዛገፍ ፡ ወጥመድ ፡ ውስጥ ፡ ገባሁ ። ወደ ፡
አመሻሽም ፡ አንድ ፡ አስተርጓሚና ፡ ሁለት ፡
ዘበኞች ፡ ወዳለንበት ፡ ጐጆ ፡ መጡ ። «ሶኮሎ
ቭ ፡ አንድሬይ?» ሲሉ ፤ መልስ ፡ ሰጠሁ ። በፍጥ
ነት ፡ እርምጃ ፡ ተከተለን ፡ ሄር ፡ ላገርፉህረር ፡
ሊያነጋግሩህ ፡ ይፈልጋሉ ፡ አለኝ ። ሊጨርሱ
ኝ ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ አሰብሁ ። ጓደኞቼንም ፡ ደህና ፡
ሰንብቱ ፡ አልኋቸው ። ሁሉም ፡ ወደ ፡ ሞት ፡
እንደምሄድ ፡ ተረዱት ፡ እኔም ፡ ትንፋሼን ፡ ከ
መለስሁ ፡ በኋላ ፡ ዘበኞችን ፡ ተከተልኋቸው ።
የሠፈሩንም ፡ ሜዳ ፡ ሳቋርጥ ፡ ቀና ፡ ብዬ ፡ ኮከ
ቦችን ፡ አየሁና ፡ ደህና ፡ ሰንብቱ ፡ አልኋቸው ፡
በኋላም ፡ ለራሴ ፡ በማሰብ ፡ አንድሬይ ፡ ሶኮሎ
ቭ ፡ ቁጥር ፡ ፲፱፻፴፩ ሙሉ ፡ ሥቃይህን ፡ አሁን ፡ ል
ተቀበል ፡ ነው ፡ አልሁት ። ለትንሽ ፡ ጊዜም ፡
ስለኢሪናና ፡ ልጆቼ ፡ አዘንሁ ፡ ከዚያም ፡ ወታ
ደር ፡ ሊያደርገው ፡ እንደሚገባው ፡ ሁሉ ፡ በመ
ጨረሻዋ ፡ ደቂቃ ፡ ነፍሴ ፡ ከሥጋዬ ፡ ስትለያይ ፡

ብርጭቆውንና ፡ ዳቦውን ፡ ልቀበለው ፡ ስል ፡ የተናገራቸው ፡ ቃሎች ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ፈጁኝ ። እኔ ፡ የሩሲያ ፡ ወታደር ፡ የሆንሁት ፡ ስለጀርመን ፡ ጦር ፡ አሸናፊነት ፡ ልጠጣ ፡ ነው? ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ «ምንድር ፡ ነው ፡ የሚፈልገው ፡ ሄር ፡ ኮማንዳንት? ከሸናፕሱ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ገሃነም ፡ ለምን ፡ አይወርድም!» የሚል ፡ ሃሳብ ፡ ተሰማኝ ።

ብርጭቆውን ፡ ከነዳቦው ፡ ጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ አስቀምጬ ፡ «ብዙ ፡ አመሰግናለሁ ፡ ስለ ፡ ግብዣዎ ፡ ግን ፡ አልጠጣውም ፡» አልሁ ። ፈገግ ፡ አለና ፡ «ታዲያስ ፡ ስለአሸናፊነታችን ፡ ለመጠጣት ፡ አትፈልግም? እንግዲያስ ፡ ስለራስህ ፡ ሞት ፡ ጠጣ ።» «ብሞት ፡ ከሥቃይ ፡ ነው ፡ የምገላገለው ፡ የሚጐድልብኝስ ፡ ምንድር ፡ ነው?» አልሁና ፡ ብርጭቆውን ፡ አንስቼ ፡ በሁለት ፡ ጉንጭ ፡ ጨለጥሁት ። ግን ፡ ዳቦውን ፡ አልነካሁትም ። አፌንም ፡ በእጄ ፡ ከጠረግሁ ፡ በኋላ ፡ «ስለግብዣዎ ፡ አመሰግንዎታለሁ ፡ አሁን ፡ ተዘጋጅቻለሁና ፡ ሄር ፡ ኮማንዳንት ፡ በኢላማዎ ፡ ላይ ፡ ሊተኩሱ ፡ ይችላሉ ፡» አልሁ ።

አተኩሮ ፡ ከተመለከተኝ ፡ በኋላ ፡ «ከመሞትህ ፡ በፊት ፡ ብላ ፡» አለኝ ። እኔም ፡ መልሼ ፡ «አንድ ፡ ብርጭቆ ፡ ከጠጣሁ ፡ በኋላ ፡ ከቶ ፡ በልቼ ፡ አላውቅም ።» ከዚያ ፡ በኋላ ፡ እንደገና ፡ ቀድቶ ፡ ለሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ ብርጭቆውን ፡ ሰጠኝ ። እኔም ፡ ሁለተኛውን ፡ ብርጭቆ ፡ ተቀብዬ ፡ ጠጣሁ ፡ ዳቦውን ፡ ግን ፡ አልነካሁትም ። ሁሉንም ፡ በድፍረት ፡ እሰበስብ ፡ ነበር ። በኋላም ፡ ለመሞት ፡ ወደ ፡ ሜዳው ፡ ከመውጣቴ ፡ በፊት ፡ እሰክር ፡ ይሆናል ፡ ብዬ ፡ አሰብሁ ። ከዚህ ፡ ቀጥሎም ፡ የአዛዡ ፡ ቅንድቦች ፡ ወለል ፡ ብለው ፡ ተከፈቱና ፡ «የሩሲያው ፡ ኢቫን ፡ ለምን ፡ አትበላም? አትፈር!» እኔ ፡ ግን ፡ እምቢታዬን ፡ አጥብቄ ፡ ያዝሁ ። «ይቅርታ ፡ ያድርጉልኝ ፡ ሄር ፡ ኮማንዳንት ፡ ከሁለተኛው ፡ ብርጭቆ ፡ መጠጥ ፡ በኋላም ፡ አልበላም ፡» ሳቁን ፡ ለመያዝ ፡ አቃተውና ፡ ከልቡ ፡ በሙሉ ፡ ኃይሉ ፡ እየሳቀ ፡ በጀርመን ፡ ቋንቋ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ተናገረ ። እኔ ፡ የተናገርሁትን ፡ ለባልንጀሮቹ ፡ የተረጐመላቸው ፡ መሰለኝ ። ከዚህ ፡ በኋላም ፡ ወንበራቸውን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ እየገፉ ፡ እኔንም ፡ ለማየት ፡ ዘወር ፡ ብለው ፡ ይስቁ ፡ ጀመር ፡ ባስተያየታቸውም ፡ ነገሩ ፡ ቀዝቀዝ ፡ እንዳለ ፡ ገባኝ ።

አዛዡም ፡ ሶስተኛውን ፡ ብርጭቆ ፡ ቀድቶ ፡ ሊሰጠኝ ፡ ሲል ፡ ከሳቁ ፡ ብዛት ፡ የተነሳ ፡ እጁ ፡ ይንቀጠቀጥ ፡ ነበር ። ይህንንም ፡ ተቀብዬ ፡ በቀስታ ፡

ስጠጣ ፡ ከዳቦውም ፡ ትንሽ ፡ ቆርሼ ፡ በላሁና ፡ የቀረውን ፡ ጠረጴዛ ፡ ላይ ፡ አስቀመጥሁት ። ምንም ፡ እንኳ ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ቢርበኝም ፡ እነሱ ፡ እንዳሰቡት ፡ የጣሉልኝን ፡ ፍርፋሪ ፡ እንደ ፡ እንስሳ ፡ በመንገብገብ ፡ ልበላው ፡ አልፈለግሁም ፡ ምክንያቱም ፡ ያለኝን ፡ የሩሲያዊ ፡ ክብር ፡ ላሳያቸው ፡ ፈለግሁ ፡ እንጂ ።

ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ በኋላ ፡ በአዛዡ ፡ ፊት ፡ የቁም ፡ ነገረኛነት ፡ መልክ ፡ ታየበት ፡ በደረቱ ፡ ላይ ፡ የተንጠለጠሉትን ፡ ሁለት ፡ የብረት ፡ መስቀል ፡ ኒሻኖች ፡ አስተካከለና ፡ ሽጉጡን ፡ ጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ አስቀምጦ ፡ «ስማ ፡ ሶኮሎቭ ፡ እውነተኛው ፡ የሩሲያ ፡ ወታደር ፡ ነህ ፡ ጥሩ ፡ ወታደር ፡ ነህ ። እኔም ፡ እንዳንተ ፡ ወታደር ፡ ነኝ ፡ ጠላትም ፡ ቢሆን ፡ ጀግናውን ፡ ሰው ፡ አከብራለሁ ፡ ስለዚህ ፡ አልገድልህም ። ከዚህስ ፡ የበለጠ ፡ ምን ፡ አለ ፡ የኛ ፡ ጀግኖች ፡ ወታደሮች ፡ ቮልጋ ፡ ደርሰዋል ፡ ቮልጎግራድንም ፡ በሙሉ ፡ ይዘዋታል ፡ ስለዚህ ፡ ለኛ ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ ስለሆነ ፡ በሩኅሩኅነቴ ፡ ነፍስህን ፡ ምሬያታለሁ ። ስለደፋርነትህ ፡ ይህንን ፡ ይዘህ ፡ ወደቤትህ ፡ ሂድ ፡» ብሎ ፡ ከጠረጴዛውም ፡ ላይ ፡ ትንሽ ፡ ዳቦና ፡ አንድ ፡ ጉማጅ ፡ ጮማ ፡ ሰጠኝ ።



ዳቦውን ፡ በቀኝ ፡ እጄ ፡ ከደረቴ ፡ ጋር ፡ ባለኝ ፡ ጉልበት ፡ ሁሉ ፡ አጣብቄ ፡ ያዝሁና ፡ ጮማውን ፡ ደግሞ ፡ በግራ ፡ እጄ ፡ ይዤ ፡ አመሰግናለሁ ፡ ሳልል ፡ እንኳ ፡ ግማሽ ፡ ዙር ፡ ብቻ ፡ ዞሬ ፡ እንዲህ ፡ ባለ ፡ ባልታሰበ ፡ ሁኔታ ፡ ወደ ፡ በሩ ፡ ሄድሁ ። ብቻ ፡ ቢሆንም ፡ ካሁን ፡ አሁን ፡ በትከሻዬ ፡ ላይ ፡ አፈላብኝ ፡ ይህን ፡ የያዝሁትንም ፡ ለባልንጀሮቼ ፡ ሳላደርስላቸው ፡ ልቀር ፡ ነው ፡ በሚል ፡ ጥርጣሬ ፡ ተውጬና ፡ እንደ ፡ ብርድ ፡ የሚያንቀጠቅጠው ፡ የሞት ፡ ጥላ ፡ ተሰምቶኝ ፡ ሳለ ፡ ምንም ፡ ሳይደርስብኝ ፡ በደህና ፡ እንደገና ፡ ከሞት ፡ አመለጥሁ ።

ከአዛዡ ፡ ቢሮ ፡ ሳልንገዳገድ ፡ ወጣሁ ፡ ውጭ ፡ ግን ፡ ቦታውን ፡ ሁሉ ፡ እያደረስሁ ፡ ነው ፡ የሄድሁት ። ከጐጆውም ፡ ውስጥ ፡ እየተንገዳገድሁ ፡ ገብቼ ፡ በሲሚንቶው ፡ ወለል ፡ ላይ ፡ ተዘርሬ ፡ ወደቅሁ ። ባልንጀሮቼም ፡ ገና ፡ ሳይነጋ ፡ ቀስቅሰው ፡ «የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ ንገረን !» አሉኝ ። በአዛዡ ፡ ቢሮ ፡ ውስጥ ፡ የሆነውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አስታወስሁና ፡ ነገርኋቸው ። ከኔ ፡ አልጋ ፡ አጠገብ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ በሚንቀጠቀጥ ፡ ድምጽ ፡ «ይህን ፡ ምግብ ፡ እንዴት ፡ አድርገን ፡ ነው ፡ የምንካፈለው?» ሲል ፡ ጠየቀ ። «ሁላችንም ፡ እኩል ፡ ነው ፡ የምንካፈለው ፡» አል

ሁት ። እስኪነጋ ፡ ድረስ ፡ ጠብቀን ፡ ዳቦውንና ፡ ጮማውን ፡ በክር ፡ ከሸነሸንነው ፡ በኋላ ፡ ከዳቦው ፡ ለያንዳንዳችን ፡ የክብሪት ፡ ቤት ፡ የሚያህል ፡ ቁራጭ ፡ ሲደርሰን ፡ ከጮማው ፡ ግን ፡ ከንፈራችንን ፡ ለማውዛት ፡ ያህል ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የደረሰን ። ቢሆንም ፡ በትክክል ፡ ነው ፡ የተካፈልነው ።

ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ከመሃከላችን ፡ ጠንከር ፡ ያሉትን ፡ መርጠው ፡ አንድ ፡ ሶስት ፡ መቶዎችን ፡ እረግረጋሙን ፡ ቦታ ፡ ቦይ ፡ እየቆፈረን ፡ እንድናደርቀው ፡ ወሰዱን ። እሱንም ፡ ስንጨርስ ፡ በሩህር ፡ ማዕደን ፡ እንድንቆፍር ፡ አስተላለፉን ። ከዚያም ፡ እስከ ፡ ፲፱፻፴፩ ዓ ፡ ም ፡ ድረስ ፡ (እ ፡ አ ፡ አ፡) ቆየሁ ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ አገራችን ፡ ውስጥ ፡ የነበረው ፡ የጀርመን ፡ ጦር ፡ የወታደሮቻችን ፡ እጅ ፡ ጥሩ ፡ አድርጐ ፡ ስለቀመሰው ፡ ፋሽስቶች ፡ እኛን ፡ እስረኞችን ፡ ዝቅ ፡ አድርገው ፡ ከመመልከት ፡ ታገሱን ። ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ሁላችንንም ፡ አሰለፉን ፡ አንድ ፡ ለመጐብኘት ፡ የመጣ ፡ አበርሌውተናንት ፡ በአስተርጓሚ ፡ አማካይነት ፡ «ወታደር ፡ በነበራችሁበት ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ በመኪና ፡ ነጅነት ፡ ስትሠሩ ፡ የነበራችሁ ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ እርምጃ ፡ ወደፊት ፡ ሂዱ ፡» ብሎ ፡ ተናገረ ። አንድ ፡ ሰ



ባት ፡ የምንሆን ፡ ካሁን ፡ ቀደም ፡ በመኪና ፡ ነጅነት ፡ ስንሠራ ፡ የቆየን ፡ ከመስመሩ ፡ ቀደም ፡ ብለን ፡ ወጣን ። ያረጀ ፡ ከላይ ፡ የሚደረብ ፡ ልብስ ፡ ሰጥተው ፡ በዘበኛ ፡ ወደ ፡ ፖትስዳም ፡ ወሰዱን ። እዚያም ፡ እንደደረስን ፡ በየቦታው ፡ በታተኑን ። እኔ ፡ ቶድት ፡ እንድሠራ ፡ ተነገረኝ ። ይህም ፡ ጀርመኖች ፡ እንደሚጠሩት ፡ የመንገዶችና ፡ የመከላከያ ፡ ሥራ ፡ ማደራጃ ፡ ክፍል ፡ ነው ።

ለአንድ ፡ የጀርመን ፡ የመኃንዲስ ፡ ክፍል ፡ ሻለቃ ፡ አፔል ፡ አድሚራል ፡ ኦቶሞቢል ፡ እነዳ ፡ ነበር ። እሱም ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ሰው ፡ እንደነበረ ፡ ለማወቅ ፡ የፈለግህ ፡ እንደሆን ፡ ልክ ፡ እርያ ፡ የመሰለ ፡ ፍጥረት ፡ ነው ። አጠር ፡ ያለ ፡ ሆዱ ፡ ወደፊት ፡ የገፋ ፡ ዳሌው ፡ የሰፋ ፡ በቁመቱ ፡ ልክ ፡ የወፈረ ፡ ሰው ፡ ነበር ። እንደ ፡ ወፍራም ፡ ሴት ፡ ከአገጩም ፡ ግርጌ ፡ ሶስት ፡ የተንጠለጠለ ፡ ኩልኩልት ፡ ሲኖረው ፡ ከማጅራቱም ፡ ላይ ፡ ሻኛ ፡ ይመስል ፡ የተደራረበ ፡ ግድ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነበር ፡ እንደማስበው ፡ ሃምሳ ፡ ኪሎ ፡ ሞራ ፡ የተሸከመ ፡ ይመስለኛል ። ሲሄድ ፡ ትንፋሹ ፡ ልክ ፡ በእንፉዋለት ፡ እንደሚሠራ ፡ መኪና ፡ ሲተነፍስ ፡ ይሰማል ። ለመብላት ፡ በሚቀመጥበትም ፡ ጊዜ ፡ በቀላሉ ፡ አ

ይመለስም! ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ሲያመነዝህና ፡ ኮ
ኛኩን ፡ ሲጐነጭ ፡ ነበር ፡ የሚውለው ። አል
ፎ ፡ አልፎ ፡ ለኔም ፡ ትንሽ ፡ ቁራጭ ፡ ያቀምሰኛ
ል ፡ መንገዳችንን ፡ አቋርጠን ፡ እንቆማለን ፡ የ
አሳማ ፡ ቋሊማና ፡ አይብ ፡ ቆራርጦ ፡ ከበላና ፡
ከጠጣ ፡ በኋላ ፡ ደስ ፡ ባለው ፡ ቀን ፡ ትራፊውን ፡
እንደ ፡ ውሻ ፡ ገፋ ፡ ያደርግልኛል ። ምን ፡ ጊዜም ፡
ቢሆን ፡ አንስቶ ፡ ሰጥቶኝ ፡ አያውቅም ። ምክን
ያቱም ፡ ከሱ ፡ ዝቅ ፡ አድርጐ ፡ ስለቆጠረኝ ፡
ነው ። የሆነውም ፡ ቢሆን ፡ ከሠፈሩ ፡ ጋር ፡ ሊ
ወዳድር ፡ አይችልም ፡ እኔም ፡ ትንሽ ፡ በትን
ሽ ፡ ጐልመስ ፡ እያልሁና ፡ ሰው ፡ እየመሰልሁ ፡
ሄድሁ ፡ ክብደትም ፡ ልጨምር ፡ ጀመርሁ ።
ለሁለት ፡ ሳምንትም ፡ ሻለቃውን ፡ ከፖት
ስዳም ፡ ወደ ፡ በርሊን ፡ ሳመላልሰው ፡ እን
ደቆየሁ ፡ ወደ ፡ ጦር ፡ ግንባር ፡ ሂዶ ፡ ወታደሮ
ቻችንን ፡ የሚያግድ ፡ ምሽግ ፡ እንዲሠራ ፡ ታ
ዘዘ ። ከዚያ ፡ በኋላማ ፡ ሌሊቱን ፡ እንቅልፍ ፡
ሊወስደኝ ፡ ነው! በየማታውም ፡ እንዴት ፡ አ
ምልጬ ፡ ከባልንጀሮቼ ፡ ጋር ፡ እንደምቀላቀል ፡
ሌሊቱን ፡ ሙሉ ፡ ሳስብ ፡ አድር ፡ ጀመር ።
ፖሎትስክ ፡ ወደ ፡ ተባለው ፡ ከተማ ፡ ሄድ
ን ። ሲነጋም ፡ በሁለት ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡



የኛን ፡ የመድፍ ፡ ድምጽ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡
ስሰማ ፡ ልቤ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ በኃይል ፡ እንደመ
ታ ፡ ገምተህ ፡ ልትረዳው ፡ ትችላለህ ። ምን ፡
ማለትህ ፡ ነው ? በመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ከኢሪና ፡
ጋር ፡ አብሬ ፡ በምሄድበት ፡ ወቅት ፡ እንኳ ፡ ይ
ህን ፡ ያህል ፡ አልመታም! ጦርነቱ ፡ ከፖሎት
ስክ ፡ አስራ ፡ ስምንት ፡ ኪሎሜትር ፡ ያህል ፡
እራቅ ፡ ብሎ ፡ በስተ ፡ ምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ነበር ።
በከተማው ፡ ውስጥ ፡ የነበሩት ፡ ጀርመኖች ፡
ከፍርሃት ፡ የተነሳ ፡ ይባንኑ ፡ ነበር ። የኔውም ፡
ጉዝር ፡ ሆድ ፡ ይበልጥ ፡ ይጠጣ ፡ ጀመር ። ቀ
ኑን ፡ ሁሉ ፡ ከቦታ ፡ ወደ ፡ ቦታ ፡ እየዞረ ፡ ም
ሽጉን ፡ እንዴት ፡ አድርገው ፡ እንደሚሠሩት ፡
ትእዛዝ ፡ ሲሰጥ ፡ ውሎ ፡ ማታ ፡ ወደ ፡ መጠጡ ፡
ይመለስ ፡ ነበር ። ትንፋሹም ፡ ይበልጥ ፡ እየ
ቀጠለ ፡ ሄደ ። ያይኑ ፡ ቆብም ፡ እንደ ፡ ከረጢ
ት ፡ የተንጠለጠለ ፡ ሆነ ።
የምፈልገው ፡ ጊዜ ፡ ደረሰ ፤ ተንግዴህ ፡ ወ
ዲህ ፡ የምጠብቀው ፡ ነገር ፡ ምንም ፡ የለም ፡
ብዬ ፡ አሰብሁ ። አሁንስ ፡ ብቻዬን ፡ አላመል
ጥም ፡ እዚያ ፡ ብዙ ፡ ይጠቅማልና ፡ ይህን ፡ ጉ
ዝር ፡ ሆድ ፡ ይገፔ ፡ መሄድ ፡ አለብኝ ፡ አልሁ።
ከፈረሱት ፡ ቤቶች ፡ መሃከል ፡ አንድ ፡ ከበ
ድ ፡ ያለ ፡ ብረት ፡ አገኘሁ ። እራሱን ፡ ስመታ

በት ፡ እንዳይደማ ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ ጫፉን ፡
በጨርቅ ፡ ጠመጠምሁት ። ከመንገድ ፡ ላይም ፡
የተበጠሰ ፡ የስልክ ፡ ሽቦ ፡ ረዘም ፡ ያለውን ፡
ወስጄ ፤ የሚያስፈልገኝን ፡ ሁሉ ፡ ስላገኘሁ ፡
ሁሉንም ፡ ከፊተኛው ፡ መቀመጫ ፡ ሥር ፡ ደበ
ቅሁት ። ጀርመኖችን ፡ ደህና ፡ ሰንብቱ ፡ ብዬ ፡
ከመሄዴ ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ አስቀድሞ ፡ ከቤንዚ
ን ፡ ማደያ ፡ ጣቢያ ፡ ስመለስ ፡ አንድ ፡ የጀርመ
ን ፡ ተራ ፡ ወታደር ፡ ሙትት ፡ ብሎ ፡ ሰክሮ ፡ ግ
ርግዳ ፡ ተደግፎ ፡ ሲንገዳገድ ፡ አገኘሁት ። እ
ሱንም ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ ወደ ፡ ፈረስ ፡ ቤት ፡ ጐት
ቼ ፡ ካገባሁት ፡ በኋላ ፡ ልብሱንና ፡ መለዮን ፡ ጭ
ምር ፡ ገፈፍሁት ። ሁሉንም ፡ ከመጀመሪያው ፡
ወንበር ፡ ሥር ፡ ደብቄ ፡ ተዘጋጀሁ ።

በ፳፱ኛው ፡ ሰኔ ፡ ጥዋት ፡ በትሮስኪጻ ፡ አቅ
ጣጫ ፡ ከከተማ ፡ ውጭ ፡ ይዤው ፡ እንድሄድ ፡
ሻለቃው ፡ አዘዘኝ ። እዚያም ፡ ስለሚሠራው ፡
መከላከያ ፡ ምሽግ ፡ አላፊ ፡ ነበር ። መንገዳች
ንን ፡ ቀጠልን ። ሻለቃው ፡ ኋላ ፡ ተቀም
ጦ ፡ እንቅልፍ ፡ ሽልብ ፡ አድርጐት ፡ ስለነበር ፡
ልቤ ፡ ፈንድቶ ፡ ባፌ ፡ ሊወጣ ፡ ምንም ፡ አል
ቀረውም ፡ ነበር ። ተከተማ ፡ እስክንወጣ ፡ ድ
ረስ ፡ በፍጥነት ፡ ነዳሁ ፡ ተከተማ ፡ እንደወጣ
ሁ ፡ ግን ፡ የመኪናውን ፡ ፍጥነት ፡ አቀዝቅ



ዤ ፡ ትንሽ ፡ ስሄድ ፡ እንደቆየሁ ፡ መኪናውን ፡
አቁሜ ፡ ለመመልከት ፡ ወጣሁ ፡ ከኋላችንም ፡
በጣም ፡ ራቅ ፡ ብለው ፡ ሁለት ፡ ካሚዮኖች ፡
የኛን ፡ አቅጣጫ ፡ ይዘው ፡ በዝግታ ፡ ሲመጡ ፡
አየሁ ። የደበቅሁትንም ፡ ከባድ ፡ ብረት ፡ አው
ጥቼ ፡ የአቶሞቢሉን ፡ በር ፡ በሰፊው ፡ ከፈትሁ
ት ። ሻለቃውም ፡ ከኋለኛው ፡ ወንበር ፡ ተቀም
ጦ ፡ እንቅልፍ ፡ ወስዶታል ፡ ባለቤቱም ፡ ካጠ
ገቡ ፡ ያለች ፡ ይመስል ፡ ያንኳርፍ ፡ ነበር ። በ
ያዝሁትም ፡ ብረት ፡ በግራ ፡ በኩል ፡ ጆሮ ፡ ግ
ንዱን ፡ ሳቀምሰው ፡ ራሱን ፡ ደፋው ። ለማ
ረጋገጥም ፡ ሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ ደገምሁት ። ግ
ን ፡ ልገድለው ፡ አልፈለግሁም ። ከነነፍሱ ፡
ማርኬ ፡ ይዤው ፡ እንድሄድና ፡ እዚያ ፡ ብዙ ፡
የሚጠቅም ፡ ነገር ፡ እንዲናገር ፡ ነበር ፡ የፈለ
ግሁት ። ሽጉጡንም ፡ ከማህደሩ ፡ አውጥቼ ፡ እ
ኪሴ ፡ ውስጥ ፡ አገባሁት ። በፍጥነት ፡ ስነዳም ፡
ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ እንዳይወድቅ ፡ የሻለቃውን ፡
አንገት ፡ በስልኩ ፡ ሽቦ ፡ ከመኪናው ፡ ጣራ ፡
ማገር ፡ ጋር ፡ አሰርሁት ። የገፈፍሁትን ፡ የጀ
ርመን ፡ ወታደር ፡ ልብስ ፡ ለበስሁና ፡ ሰማይ
ና ፡ መሬት ፡ ወደሚያልፍበት ፡ ወደጦርነቱ ፡ ቦታ ፡
ቀጥታውን ፡ ሄድሁ ።

የጀርመኖችን ፡ የጦር ፡ መስመር ፡ አቋርጬ ፡ አልፌ ፡ ስሄድ ፡ ጠርቀም ፡ ያሉ ፡ መትረየስ ፡ ተኳሾች ፡ ከእርዳቸው ፡ እየዘለሉ ፡ ሲወጡ ፡ በማየቴ ፡ አንድ ፡ ሻለቃ ፡ አብሮኝ ፡ እንዳለ ፡ እንዲያዩ ፡ ፍጥነቱን ፡ ቀነስ ፡ አደረግሁ ። መንገዴን ፡ እንዳልቀጥል ፡ ለማስረዳት ፡ እጃቸውን ፡ እያወዛወዙ ፡ ቢጮሁ ፡ እንዳልሰማኋቸው ፡ መስዬ ፡ ፍጥነቴ ፡ ሰማንያ ፡ ኪሎሜትር ፡ እስኪደርስ ፡ ድረስ ፡ ነዳሁት ። እነሱም ፡ የሆነውን ፡ ለይተው ፡ አውቀው ፡ ሳይተኩሱብኝ ፡ ማንም ፡ ካልያዘው ፡ ቦታ ፡ ደረስሁ ፡ የመድፍ ፡ ጥይት ፡ የቆፈረውንም ፡ ጉድጓድ ፡ ለመሸሽ ፡ እንደ ፡ ጥንቸል ፡ ሩጫ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ እየተጠማዘዝሁ ፡ ነበር ፡ የምሄደው ።

ጀርመኖች ፡ ከኋላዬ ፡ የኛዎች ፡ ደግሞ ፡ ከፊቴ ፡ ይተኩሱብኝ ፡ ጀመር ። መስኮቱ ፡ በአራት ፡ ጥይት ፡ ሲመታ ፡ ራዲያቶሩ ፡ ደግሞ ፡ በአንድ ፡ ጥይት ፡ ተመታ ። ከአንድ ፡ ሐይቅ ፡ አጠገብ ፡ ያለውን ፡ ጫካ ፡ ተመልክቼ ፡ ወደዚያ ፡ ስሄድ ፡ የኛዎቹ ፡ ወታደሮች ፡ ወደ ፡ አቶሞቢሉ ፡ ይሮጡ ፡ ነበር ፡ ከጫካው ፡ ውስጥም ፡ እንደገባሁ ፡ ቶሎ ፡ ብዬ ፡ በሩን ፡ ከፍቼ ፡ ወጥቼ ፡ መሬቱን ፡ ሳምሁት ። ከደስታም ፡ ብዛት ፡ የተነሳ ፡ በመጣጣር ፡ ነበር ፡ የምተነፍሰው ።



አንድ ፡ ወጣት ፡ ካሁን ፡ ቀደም ፡ ያላየሁት ፡ ካኪ ፡ የመሰለ ፡ ጥብጣቦች ፡ ትከሻው ፡ ላይ ፡ ያደረገ ፡ ከሁሉም ፡ አስቀድሞ ፡ እንደደረሰ ፡ በቁጣ ፡ ቃል ፡ «አንተ ፡ ሰይጣን ፡ ፍሪትዝ ፡ መንገድህ ፡ ጠፍቶሃል ፡ ወይ?» አለ ። የለበስሁትንም ፡ የጀርመን ፡ ወታደር ፡ ልብስ ፡ ቦጫጭቄ ፡ ከነቆቡ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ጥዬ ፡ «አንተ ፡ ያማርህ ፡ ወጣት ፡ ወጣቱ ፡ ልጄ! ቮሮኔዥ ፡ ተወልጄ ፡ ያደግሁት ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ፍሪትዝ! ተማርኬ ፡ እስረኛ ፡ ነበርሁ ፡ ተመልከት!» አልሁት ። «አሁን ፡ መኪና ፡ ውስጥ ፡ የታሰረውን ፡ እርያ ፡ ከእስራቱ ፡ ፍታና ፡ ቦርሳውንም ፡ ከእጁ ፡ ተቀብለህ ፡ ወደ ፡ አዛዥህ ፡ ውሰደው ።» አልሁ ። ሽጉጤንም ፡ ሰጠሁት ። ቀኑንም ፡ ካንዱ ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ ስተላለፍ ፡ ውዬ ፡ ወደ ፡ ምሽት ፡ ከዲቪዚዮኑ ፡ አዛዥ ፡ ኮሎኔል ፡ ፊት ፡ ቀረብሁ ። ወደ ፡ ኮሎኔሉ ፡ ከመቅረቤ ፡ በፊት ፡ ሰውነቴን ፡ ስታጠብና ፡ ደህና ፡ ምግብ ፡ ስመገብ ፡ እንዲሁም ፡ ስጠየቅ ፡ ውዬ ፡ አዲስ ፡ የወታደር ፡ ልብስ ፡ ተሰጥቶኝ ፡ በደንብ ፡ ከለበስሁና ፡ በሚገባም ፡ ንጹህ ፡ ከሆንሁ ፡ በኋላ ፡ ኮሎኔሉ ፡ ወደሚገኝበት ፡ እርድ ፡ ሄድሁ ። እንደደረስሁም ፡ ኮሎኔሉ ፡ ከተቀመጠበት ፡ ተነስቶ ፡ እኔ ፡ እቆምሁበት ፡ ቦታ ፡ ድረስ ፡ መጥቶ ፡ እዚያ ፡ በነበሩት ፡

መኮንኖች ፡ ሁሉ ፡ ፊት ፡ እቅፍ ፡ አድርጎ ፡ «ስላመጣህልን ፡ ያማረ ፡ ስጦታህ ፡ እናመሰግንሃለን ። ያንተ ፡ ሻለቃና ፡ ቦርሳውም ፡ ከጦር ፡ ግንባር ፡ ከምንማርካቸው ፡ ሃያ ፡ ጀርመኖች ፡ ይበልጥ ፡ የሚጠቅም ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ያስረዱን ። ሽልማት ፡ እንድታገኝ ፡ እጽፍልሃለሁ ።» ያሳየኝ ፡ ፍቅርና ፡ የተናገራቸው ፡ ቃሎች ፡ በደስታ ፡ ማዕበል ፡ ስላሰጠሙኝ ፡ የምናገረው ፡ በማጣት ፡ የሚነቃነቁ ፡ ከንፈሮቼን ፡ ላስታግሳቸው ፡ አልቻልሁም ። ልናገረውም ፡ የቻልሁት ፡ «ከምሬድ ፡ (ባልንጀራዬ፡) ኮሎኔል ፡ በእግረኛ ፡ ጦር ፡ ክፍል ፡ ለመቀጠር ፡ እጠይቃለሁ ፡» የሚል ፡ ብቻ ፡ ነበር ።

ኮሎኔሉም ፡ ሳቀና ፡ ትከሻዬን ፡ ይዞ ፡ «ለመቆም ፡ የቻልኸው ፡ በችግር ፡ ሲሆን ፡ ታዲያ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ወታደር ፡ ነው ፡ የምትሆነው ። አሁኑኑ ፡ ወደ ፡ ሐኪም ፡ ቤት ፡ ነው ፡ የምሰድህ ። ከዚያም ፡ ደህና ፡ አድርገው ፡ ከጠገኑህና ፡ ከመገቡህ ፡ በኋላ ፡ ያንድ ፡ ወር ፡ ፈቃድ ፡ አግኝተህ ፡ ቤተ ፡ ሰብህን ፡ ከጐበኘህ ፡ በኋላ ፡ ስትመለስ ፤ የምትገባበትን ፡ ክፍል ፡ እናስባለን ፡» አለኝ ።

ኮሎኔሉና ፡ አብረውት ፡ የነበሩት ፡ መኮንኖች ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ፍጥረት ፡ አክብረው ፡ እጄን ፡ እየጨበጡ ፡ ሰላምታ ፡ በመስጠት ፡ ደህና ፡ ሰንብት ፡ ባሉኝ ፡ ጊዜ ፡ ከደስታው ፡ ብዛት ፡ የተነሳ ፡ እራሴ ፡ ዞረ ። ምክንያቱም ፡ ባለፉት ፡ ሁለት ፡ ዓመቶች ፡ ውስጥ ፡ ይህን ፡ ዓይነት ፡ ስሜት ፡ ተነፍጌ ፡ ስለነበረ ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ አከባበር ፡ እንዴት ፡ እንደሆነ ፡ ረስቼው ፡ ነበር ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ ከከፍተኛ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ስትነጋገር ፡ ራስህን ፡ ደፍተህ ፡ ነው ፡ የተባለውን ፡ ልምድ ፡ እስክረሳው ፡ ድረስ ፡ ጊዜ ፡ የሚጠይቅ ፡ ስለነበረ ፤ እዚያው ፡ ያለሁ ፡ መስሎኝ ፡ እንዳልመታ ፡ በፍርሃት ፡ ተውጬ ፡ ነበር ። በነዚያ ፡ የፋሽስት ፡ እስር ፡ ቤት ፡ ሠፈሮች ፡ ይህን ፡ ዓይነት ፡ ትምህርት ፡ ነበር ፡ የሚያስተምሩን ።

ሆስፒታልም ፡ እንደገባሁ ፡ ለኢሪና ፡ ደብዳቤ ፡ ጻፍሁላት ። ሐተታ ፡ ሳላበዛም ፡ እንዴት ፡ ተማርኬ ፡ እስረኛ ፡ እንደነበርሁና ፡ አንድ ፡ የጀርመን ፡ ሻለቃም ፡ ይዤ ፡ አምልጬ ፡ እንደወጣሁ ፡ ነበር ፡ የጻፍሁላት ። የዚህ ፡ ዓይነት ፡ የፋከራ ፡ መንፈስ ፡ ከወዴት ፡ እንዳገኘሁት ፡ አላውቅምና ፡ ስለዚህ ፡ ልነግርህ ፡ አልችልም ። የኒሻን ፡ ሽልማት ፡ እንዳገኝ ፡ ኮሎኔሉ ፡ እጽፍልሃለሁ ፡ ብሎ ፡ ተስፋ ፡ ሰጥቶኛል ፡ ብዬስ ፡ ለምንድር ፡ ነው ፡ የጻፍሁላት!..

ለሁለት ፡ ሳምንት ፡ ዝም ፡ ብዬ ፡ ተኝቼ ፡
ነበር ፡ የምቀለበው ። የፈለግሁትን ፡ ምግብ ፡
ሁሉ ፡ ሰጥተውኝ ፡ ሁሉንም ፡ ባግበሰብሰው ፡
አደገኛ ፡ እንደሚሆንብኝ ፡ ሐኪሙ ፡ ስለገለ
ጠልኝ ፡ አነስተኛ ፡ ምግብ ፡ እየሰጡኝ ፡ በቀን ፡
ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እንድበላ ፡ ነበር ፡ የታዘዘ
ው ። ሁለት ፡ ሳምንት ፡ ካለፈ ፡ በኋላም ፡
ስመኘው ፡ የነበረውን ፡ እህል ፡ ዘወር ፡
ብዬ ፡ ልመለከተው ፡ አልቻልሁም ። ከቤቴም ፡
መልስ ፡ ስላጣሁ ፡ መንፈሴ ፡ ተሰቃየ ። እራቤ ፡
ተቆረጠ ፤ እንቅልፌም ፡ ጠፋ ፤ በመጥፎ ፡ ሃሳ
ብ ፡ ማዕበልም ፡ ተዋጥሁ ። ከሶስት ፡ ሳምንት ፡
በኋላም ፡ ከቮሮኔዥ ፡ አንድ ፡ ደብዳቤ ፡ አገኘ
ሁ ። ግን ፡ ከኢሪና ፡ አይደለም ፡ ጐረቤቴ ፡ ከ
ነበረ ፡ ኢቫን ፡ ቲሞፌየቪች ፡ ከሚባለው ፡ ካ
ንድ ፡ አናጢ ፡ ነው ። የዚህ ፡ ዓይነትም ፡ ደብ
ዳቤ ፡ ለማንም ፡ እንዲደርሰው ፡ አልመኝለት
ም ። በደብዳቤውም ፡ ውስጥ ፡ ጀርመኖች ፡ በ
ሰኔ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፴፪ ዓ ፡ ም ፡ እ ፡ አ ፡ አ ፡ የአይሮፕላኑን ፡
ፋብሪካ ፡ በቦምብ ፡ እንደደበደቡትና ፡ አንድ ፡ ከ
ባድ ፡ ቦምብም ፡ በቀጥታ ፡ ከቤቴ ፡ ላይ ፡ እን
ደወደቀ ፡ የሚገልጽ ፡ ነበር ። ቦምቡ ፡ በወደ
ቀበትም ፡ ሰዓት ፡ ኢሪናና ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡
ከቤት ፡ ውስጥ ፡ ነበሩ ። ልናገኛቸውም ፡ አል



ቻልንም ፡ ቤትህ ፡ በነበረበት ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡
አንድ ፡ ትልቅ ፡ ጉርጓድ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ያገ
ኘነው ፡ ሲል ፡ ነበር ፡ የጻፈልኝ ። በመጀመ
ሪያ ፡ ጊዜ ፡ ደብዳቤውን ፡ አንብቤ ፡ ልዘልቀ
ው ፡ አልፈቀድሁም ። ነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ጨለመብ
ኝ ፡ ልቤም ፡ ኩምትርትር ፡ ብሎ ፡ አረረ ። በጀ
ርባዬም ፡ ተንጋልዬ ፡ ትንሽ ፡ እንደቆየሁ ፡ ጀ
ምሬ ፡ የተውሁትን ፡ ደብዳቤ ፡ ለመዝለቅ ፡ ኃ
ይል ፡ አገኘሁ ። ቦምቡ ፡ በተጣለበት ፡ ጊዜም ፡
አናቶሊ ፡ ከተማ ፡ እንደነበረና ፡ ወዳመሻሽም ፡
ወደ ፡ ቤቱ ፡ መጥቶ ፡ ቦምቡ ፡ የቆፈረውን ፡ ጉ
ርጓድ ፡ ካየ ፡ በኋላ ፡ ወዲያውኑ ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡
ተመልሶ ፡ ከመሄዱ ፡ በፊት ፡ በፈቃዱ ፡ ለመ
ዝመት ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ መሄዱን ፡ ለጐረቤ
ቶች ፡ መናገሩን ፡ ብቻ ፡ ነበር ፡ የጻፈል
ኝ ።

«ሃሳቤ ፡ ትንሽ ፡ መለስ ፡ እንዳለልኝ ፡ ከባ
ቡሩ ፡ ጣቢያ ፡ ኢሪና ፡ እንዴት ፡ አድርጋ ፡ ተ
ጠምጥማብኝ ፡ እንደነበረና ፡ እኔም ፡ እንዴት ፡
አድርጌ ፡ እንደገፋኋት ፡ ትዝ ፡ አለኝ ። የሴት
ነት ፡ ልቧም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ውስጥ ፡ ሁለተ
ኛ ፡ እንደማንገናኝ ፡ ነግሯት ፡ ነበረ ። አንድ ፡
ጊዜ ፡ ቤተሰብና ፡ የራሴ ፡ ቤት ፡ እንደነበረኝ ፤
ለመሥራትም ፡ ብዙ ፡ ዓመት ፡ እንደወሰደብ

ኙና ፡ ይህም ፡ ሁሉ ፡ በቅጽበት ፡ ጠፍቶ ፡ ብቻ
ዬን ፡ እንደቀረሁ ፡ ተሰማኝ ። ይህ ፡ የኔን ፡ ሕይ
ወት ፡ ለማበላሸት ፡ የመጣው ፡ ነገር ፡ ሕልም ፡
መሆን ፡ አለበት ፡ ብዬ ፡ አሰብሁ ። እስር ፡ ቤት ፡
በነበርሁበትም ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ በየማታው ፡
በሕልሜ ፡ ከኢሪናና ፡ ከልጆቼ ፡ ጋር ፡ ስነጋ
ገር ፤ ወደ ፡ ቤቴ ፡ ተመልሼ ፡ መጣሁ ፡ ልታዝ
ኑ ፡ አይገባችሁም ፡ እኔ ፡ ጠንካራ ፡ ነኝ ፡ ሁሉ
ንም ፡ ታግሼ ፡ ችዬ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ሁ
ላችን ፡ ተሰብስበን ፡ አንድላይ ፡ እንሆናለን ፡
የሚል ፡ ቃል ፡ በሃሳቤ ፡ እየነገርኋቸው ፡ ላስ
ደስታቸው ፡ እሞክር ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ሁለ
ት ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ከሬሳ ፡ ጋር ፡ ነው ፡ ስ
ነጋገር ፡ የነበርሁት?»

ላንድ ፡ ደቂቃም ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ እንደቆየ ፡
ፍጹም ፡ በተለዋወጠ ፡ ድምጽ ፡ «የታነቅሁ ፡
መስሎ ፡ ስለተሰማኝ ፡ እስቲ ፡ ሲጋራ ፡ እናጢ
ስ ፡» አለኝ ።

ሲጋራችንንም ፡ አቀጣጠልን ። በዛፍ ፡ የ
ተወረረውንም ፡ ቦታ ፡ አንድ ፡ ግንደቆርቁር ፡
ያለማቋረጥ ፡ ትቆረቁር ፡ ነበር ። ሞቃቱም ፡
ንፋስ ፡ ባበቡት ፡ ዛፎች ፡ ላይ ፡ ሽው ፡ ሽው ፡ እ
ያለ ፡ ሲነፍስባቸው ፡ ደመናዎች ፡ ደግሞ ፡ በ
ንፋስ ፡ እየተመሩ ፡ እንደሚሄዱ ፡ መርከቦች ፡



ካንዱ ፡ ወዳንዱ ፡ ይሮጡ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ በ
ነዚህ ፡ ፍጹም ፡ ዝምታ ፡ ነገሥ ፡ በነበሩባቸውም ፡
ደቂቃዎች ፤ ዳር ፡ ድንበሩ ፡ የማይታወቀው ፡
ዓለም ፤ የጸደይን ፡ የምሥራች ፡ አብሳሪ ፡ ቃል ፡ ተ
ቀብሎ ፡ ዘለዓለማዊ ፡ የሆነውን ፡ ለምለማዊ ፡ ሕይ
ወት ፡ ለመጐናጸፍ ፡ በሚዘጋጅበት ፡ ወቅት ፤ ልዩ ፡
ሁኖ ፡ ተሰማኝ ።

ዝም ፡ ብሎ ፡ መቀመጥ ፡ የሚያስለች ፡ ስ
ለነበረ ፡ እንዲህ ፡ ስል ፡ ጠየቅሁ ።

«ከዚህ ፡ በኋላስ ፡ ምን ፡ ሆነ?»

ወሬውን ፡ ተራቹ ፡ ፈቃዱ ፡ ሳይሆን ፡ «ከ
ዚህ ፡ በኋላስ ፡ ምን ፡ ሆነ?» ሲል ፡ ጥያቄዬን ፡
መልሶ ፡ ደገመና ፡ ከዚህ ፡ በኋላማ ፡ ኮሎኔሉ ፡
የወር ፡ ፈቃድ ፡ ስለሰጠኝ ፡ ካንድ ፡ ሳምንት ፡
በኋላ ፡ ወደ ፡ ቮሮኔዥ ፡ ሄድሁ ። ካሁን ፡ ቀደም ፡
ከቤተ ፡ ሰቤ ፡ ጋር ፡ ወደምኖርበት ፡ ቦታ ፡ ድረ
ስ ፡ በእግሬ ፡ ሂጄ ፡ ብመለከት ፡ እርግጥ ፡ ጉር
ጓዱ ፡ ጠለቅ ፡ ያለና ፡ በቆሸሸ ፡ ውኃ ፡ የሞላ ፡
በዙሪያውም ፡ የበቀለው ፡ አረም ፡ ወገብ ፡ ድረ
ስ ፡ የደረሰ ፡ ሆኖ ፡ አገኘሁት ። አካባቢውም ፡
ጸጥ ፡ በማለቱ ፡ ልክ ፡ የመቃብር ፡ ቦታ ፡
ነበር ፡ የሚመስለው ። ያን ፡ ጊዜ ፡ ክፉኛ ፡
ነው ፡ የተሰማኝ! እዚያም ፡ ትንሽ ፡ ቁሜ ፡ የ
መረረ ፡ ኀዘን ፡ ካዘንሁ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ባቡር ፡

ጣቢያ ፡ ተመልሼ ፡ ሄድሁ ። ከዚያም ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ እንኳ ፡ ለመቆየት ፡ ስላቃተኝ ፡ ወዲያውኑ ፡ ወደ ፡ ዲቪዥኑ ፡ ተመልሼ ፡ ሄድሁ ።

ጥቅጥቅ ፡ ካለው ፡ ደመና ፡ መሃከል ፡ ጸሐይ ፡ ብቅ ፡ ስትል ፡ ማንንም ፡ ደስ ፡ እንደሚለው ፡ ያለ ፡ ደስታ ፡ ከሶስት ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ ደረሰኝ ። ይሄውም ፡ አናቶሊ ፡ ካለበት ፡ የጦር ፡ ግንባር ፡ የላከልኝ ፡ ደብዳቤ ፡ ስለደረሰኝ ፡ ነው ። አድራሻዬንም ፡ ያገኘው ፡ ከዚያ ፡ ኢቫን ፡ ቲሞፌየቪች ፡ ከሚባለው ፡ ከጐረቤቴ ፡ ኑሯል ። በሂሳብ ፡ ትምህርት ፡ ስጦታ ፡ ስለነበረው ፡ መጀመሪያ ፡ ወደ ፡ መድፈኛ ፡ ክፍል ፡ ኮሌጅ ፡ ገብቶ ፡ ነበር ። አንድ ፡ ዓመት ፡ ከተማረ ፡ በኋላም ፡ ፈተናውን ፡ ከክብር ፡ ጋር ፡ ያለፈና ፡ ወደ ፡ ጦር ፡ ግንባርም ፡ የተላከ ፤ ከዚያም ፡ የሻምበልነት ፡ ማዕረግ ፡ አግኝቶ ፡ የባለ ፡ ፶፯ ሚ ፡ ሜ ፡ መድፎች ፡ አዛዥነት ፡ እንደተሰጠውና ፡ ስድስት ፡ ኒሻኖችና ፡ ሜዳዮች ፡ እንደተሸለመ ፡ ጽፎልኛል ። በጠቅላላው ፡ ሽማግሌ ፡ አባቱን ፡ ብዙ ፡ አልፎት ፡ ሂዷል ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ቢሆንም ፡ በሱ ፡ እውነተኛ ፡ ኩራት ፡ ተሰምቶኛል ። ምን ፡ ማለትህ ፡ ነው ፡ ልጄ ፡ ሻምበል ፡ ሁኖ ፡ የመድፍ ፡ ጓድ ፡ አዛዥ ፡ ሲሆን ፡ ትንሽ ፡ ነገር ፡ አይደለም! ፡ የተሸለማ



ቸው ፡ ኒሻኖችስ ፡ ሁሉ ፤ አባቱ ፡ በስቱድቤከር ፡ ካሚዎን ፡ የመድፍ ፡ ጥይትና ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ወዲህና ፡ ወዲያ ፡ ቢያመላልስ ፡ ምንም ፡ አይደለም ። ያባቱ ፡ ጊዜ ፡ አልፎአል ፡ ግን ፡ እሱ ፡ አንድ ፡ ሻምበል ፡ ወደፊት ፡ ብዙ ፡ ተስፋ ፡ ያለው ፡ ነው ።

በየሌሊቱም ፡ ወላጆች ፡ እንደሚያስቡት ፡ ሁሉ ፡ አስብ ፡ ጀመር ። ጦርነቱ ፡ ሲያልቅ ፡ ልጄን ፡ ሚስት ፡ አጋባውና ፡ ከነሱ ፡ ጋራ ፡ እኖራለሁ ። የአናጢነት ፡ ሥራ ፡ በቀላሉ ፡ እየሠራሁ ፡ የልጅ ፡ ልጆቼን ፡ እጠብቃለሁ ። ይህ ፡ ሁሉም ፡ እንደ ፡ ሕልም ፡ በኖ ፡ ቀረ ። በክረምቱም ፡ ውስጥ ፡ ያለማቋረጥ ፡ ወደፊት ፡ እንገፋ ፡ ስለነበረ ፡ ወረቀት ፡ ለመጻጻፍ ፡ እንኳ ፡ ጊዜ ፡ አልነበረንም ፡ ከበርሊን ፡ እንደተቃረብን ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ጥዋት ፡ ደብዳቤ ፡ ላክሁለት ፡ የደብዳቤዬንም ፡ መልስ ፡ በማግስቱ ፡ አገኘሁ ። ሁለታችንም ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ መስመር ፡ ከጀርመን ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ ስለተጠጋን ፡ የምንገናኝበትንም ፡ ቀን ፡ በመጓጓት ፡ እጠብቀው ፡ ነበር ። ለካስ ፡ በሰቀቀን ፡ አዘቅት ፡ የምዋጥበት ፡ ቀን ፡ ታቃርቦ ፡ ኑሮ ፤ ድል ፡ ያደረግንበት ፡ ዕለት ፡ ጥዋት ፡ ግንቦት ፡ ዘጠኝ ፡ ቀን ፡ የኔው ፡ አናቶሊ ፡ በጀርመኖች ፡ ተገድሏል ።

ከሰዓት ፡ በኋላም ፡ ከአንድ ፡ ጓድ ፡ አዛዥ ፡
ዘንድ ፡ ተጠራሁ ። እዚያም ፡ እንግዳ ፡ የሆነ ፡
የመድፈኛ ፡ ክፍል ፡ መኮንን ፡ ተቀምጦ ፡ አየ
ሁ ። ስገባም ፡ የበላይ ፡ አዛዥ ፡ እንደመጣ ፡ ሁ
ሉ ፡ ተነስቶ ፡ ቆመ ። የጓድ ፡ አዛዥ ፡ መኮንን
ም ፡ «ሶኮሎቭ ፡ አንተን ፡ ሊገናኝህ ፡ ነው ፡ የ
መጣው ፡» ብሎ ፡ ወደ ፡ መስኮቱ ፡ ዞሮ ፡ ቆመ ።
በዚህን ፡ ጊዜም ፡ አንድ ፡ አስጨናቂ ፡ ነገር ፡
እንደደረሰብኝ ፡ አወቅሁ ። ሰውነቴንም ፡ ሁሉ ፡
እንደ ፡ ኤሌክትሪክ ፡ ኃይል ፡ ሲወረኝ ፡ ተሰማ
ኝ ። ሌተና ፡ ኮሎኔሉ ፡ ወደኔ ፡ ተጠግቶ ፡ «ተ
ጽናና ፡ ልጅህ ፡ ሻምበል ፡ አናቶሊ ፡ ሶኮሎቭ ፡
ዛሬ ፡ ከመድፎቹ ፡ አጠገብ ፡ ተገድሏል ፡ ስለ
ዚህ ፡ አብረን ፡ እንሂድ ፡» አለኝ ።

ለጊዜው ፡ አንገደገደኝ ፡ ግን ፡ እንደምን
ም ፡ ብዬ ፡ ተጽናናሁ ፡ ከሌተና ፡ ኮሎኔሉ ፡ ጋር ፡
በዚያ ፡ ትልቅ ፡ መኪና ፤ የቤቱ ፡ ፍራሽ ፡ ድን
ጋይና ፡ ሸክላ ፡ በተበታተነበት ፡ መንገድ ፡ ላ
ይ ፡ እንዴት ፡ አድርገን ፡ እንደሄድን ፡ አሁን ፡
እንኳን ፡ ሳስበው ፡ እንደ ፡ ሕልም ፡ ሁኖ ፡ ነው ፡
የሚታየኝ ። ተሰልፎ ፡ ስለነበረው ፡ የክብር ፡
ዘብና ፡ አስከሬኑም ፡ ተሸፍኖበት ፡ ስለነበረው ፡
ቀይ ፡ ጨርቅ ፡ ለማስታወስ ፡ ስሞክር ፡ በጭጋ
ግ ፡ የተሸፈነ ፡ ሁኖ ፡ ነው ፡ የሚታየኝ ። ግን ፡



ልጄን ፡ አናቶሊን ፡ አሁን ፡ አንተን ፡ እንደ
ማይህ ፡ ያህል ፡ ወለል ፡ ብሎ ፡ ነው ፡ የማየው ።
ወደ ፡ አስከሬኑም ፡ ተጠጋሁ ። እርግጥ ፡ ነው ፡
እዚያ ፡ ውስጥም፡ የተጋደመው ፡ ልጄ ፡ ነበር ፡
ደግሞም ፡ አልነበረም ። ልጄ ፡ ሁሉጊዜ ፡ ፈገ
ግ ፡ የሚል ፡ ትከሻው ፡ ጠበብ ፡ ያለ ፡ ገና ፡ ያ
ላደገ ፡ ልጅ ፡ ነበር ። እዚህ ፡ ግን ፡ ተጋድሞ ፡
ያየሁት ፡ ትከሻው ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ መልከ ፡ መል
ካም ፤ ዓይኖቹ ፡ በግማሽ ፡ ተዘግተው ፡ ወደማ
ይታወቅ ፡ እሩቅ ፡ ቦታ ፡ አልፎኝ ፡ እንደሄደ ፡
የሚመለከትና ፤ ያደገ ፡ ወጣት ፡ ነበር ። ሁሉ
ጊዜ ፡ እንደሚያደርገውም ፡ ከንፈሮቹ ፡ ከዳርና ፡
ዳር ፡ በፈገግታ ፡ ፈልቀቅ ፡ ብለዋል ። ይህም ፡
አንድ ፡ ጊዜ ፡ የማውቀው ፡ አናቶሊ ፡ ነበር ።
ስሜውም ፡ ወደጐን ፡ ሳብ ፡ ብዬ ፡ ቆምሁ ። ሌ
ተና ፡ ኮሎኔሉም ፡ ንግግር ፡ አደረገ ። የኔ ፡ አና
ቶሊ ፡ ባልንጀሮች ፡ ሁሉ ፡ ሲያለቅሱ ፡ እኔ ፡
ላለቅስ ፡ አልቻልሁም ። እንደሚመስለኝ ፡ በድ
ንጋጭ ፡ እንባዬ ፡ ስለደረቀ ፡ እስካሁን ፡ ድረ
ስ ፡ የሚያሰቃየኝ ፡ እሱ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ።

የመጨረሻ ፡ ደስታዬንና ፡ ተስፋዬን ፡ በ
ባዕድ ፡ አገር ፡ ቀበርሁት ። አዛዦቸው ፡ የሚጓ
ዘውን ፡ ረጅም፡ ጉዞ ፡ ለመሸኘት ፡ መድፎቹ ፡
በሮምታ፡ ተተኮሱ ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ የሚያበ

ቡና ፡ ቤቱ ፡ ሄድሁ ። ከቡና ፡ ቤቱም ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ልጁ ፡ ተቀምጦ ፡ እግሮቹን ፡ ያማታ ፡ ነበረ ። እንደራበውም ፡ ጥሩ ፡ አድርጎ ፡ በፊቱ ፡ ይታያል ። በመስኮቱም ፡ በኩል ፡ አንገቴን ፡ ወጣ ፡ አድርጌ ፡ «ቫንያ! ና ፡ ካሚዎኑ ፡ ላይ ፡ ውጣና ፡ ወደ ፡ እህሉ ፡ ማራገፊያ ፡ ሂደን ፡ ስን መለስ ፡ ምሳችንን ፡ አብረን ፡ እንበላለን ፡» አል ሁት ። በፍጥነትም ፡ ከተቀመጠበት ፡ ተነ ስቶ ፡ በሩጫ ፡ ወደ ፡ መስኮቱ ፡ ተጠጋና ፡ «ስ ሜ ፡ ቫንያ ፡ እንደሆነ ፡ እንዴት ፡ አወቅኸው?» ብሎ ፡ ጠየቀኝ ፡ እንደኮከብ ፡ በሚያበሩ ፡ ዓይ ኖቹ ፡ አተኩሮ ፡ እያየኝ ፡ መልሱን ፡ ይጠባበቅ ፡ ነበር ። «ስለ ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ ከሚያውቁት ፡ ሰዎች ፡ መሃከል ፡ አንዱ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡» አል ሁት ።

ተካሚዎኑ ፡ በስተቀኝ ፡ በኩል ፡ ሲዞር ፡ በ ሩን ፡ ከፈትሁለትና ፡ ገብቶ ፡ ተጎኔ ፡ እንደተ ቀመጠ ፡ ጉዞዋችንን ፡ ቀጠልን ። ደህና ፡ ሲጫ ወት ፡ በድንገት ፡ ዝም ፡ አለ ። ከጊዜ ፡ ወደ ፡ ጊ ዜም ፡ ረጅም ፡ ሽፋሽፍት ፡ በተጎናጸፉ ፡ ዓይ ኖቹ ፡ እየተመለከተኝ ፡ ይተክዝ ፡ ጀመረ ። ይ ህ ፡ ትንሽ ፡ ልጅ ፡ በዚህ ፡ እድሜው ፡ መተከ ዝ ፡ ማወቁ ፡ የሚገርም ፡ ነው ። ይህስ ፡ ለርሱ ፡ ሥራው ፡ ሁኖ ፡ ይሆን? «አባትህ ፡ ወዴት ፡ ነ



ው ፡ ቫንያ?» ብዬ ፡ ጠየቅሁት ። «ጦር ፡ ግን ባር ፡ ተገድሏል ፡» ሲል ፡ በሹክሹክታ ፡ መለ ሰልኝ ። «እናትህስ?» «በባቡር ፡ ስንጓዝ ፡ በቦም ብ ፡ ሙታለች ።» «ከወዴት ፡ ነው ፡ በባቡር ፡ የምትመጡት ፡ የነበር?» «አላውቅም ፡ እረስቼ ዋለሁ ።» «ምንም ፡ ዘመድ ፡ የለህም?» «አዎን ፡ ማንም ፡ የለኝም ።» «ታዲያ ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ የምታድረው?» «ባገኘሁበት ፡ ቦታ ።»

እንደ ፡ ጐርፍ ፡ የሚሄደው ፡ የእንባዬ ፡ ሙ ቀት ፡ ጉሮሮዬ ፡ ላይ ፡ ተሰማኝ ። ወዲያውኑም ፡ ሃሳቤን ፡ ወሰንሁ ። ለምንስ ፡ ነው ፡ ተለያይተ ን ፡ ሁለታችንስ ፡ እንዲህ ፡ የምንሠቃየው ? እ ንደ ፡ ራሴ ፡ ልጅ ፡ አድርጌ ፡ አሳድገዋለሁ ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ የሚሠቃየው ፡ ሃሳቤ ፡ እረ ፍት ፡ አገኘና ፡ ቀለል ፡ አለኝ ። ወደሱም ፡ ጠጋ ፡ ብዬ ፡ በእርጋታ ፡ «ቫንያ ፡ እኔ ፡ ማን ፡ እንደሆንሁ ፡ ታውቃለህ?» አልሁት ። ተንፈስ ፡ አለና ፡ «ማን ፡ ነህ?» አለኝ ። እንደመ ጀመሪያው ፡ በእርጋታ ፡ «አባትህ ፡ ነኝ ፡» አልሁት ።

የእግዚአብሔር ፡ ያለህ! ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ታውቃለህ? አንገቴን ፡ አቅ ፎ ፡ ይዞ ፡ ጉንጩን ፡ ከንፈሬን ፡ ግንባሬን ፡ እ

የሳመ ፡ እንደሚያዜም ፡ ወፍ ፡ ያንጐደጉደው ፡
ጀመር ። «ውዱ ፡ አባቴ ፡ ሆይ! እንደምትፈል
ገኝ ፡ አውቄዋለሁ ፡ አውቄዋለሁ! የሆነው ፡
ቢሆን ፡ ፈልገህ ፡ እንደምታገኘኝ ፡ አውቄዋለ
ሁ! ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ የጠበቅሁህ!» እኔም ፡
ላይ ፡ ተጣብቆ ፡ ንፋስ ፡ እንደሚያተመው ፡ ሳ
ር ፡ ይንቀጠቀጥ ፡ ነበር ። ዓይኖቼም ፡ እንባ ፡ አ
ቀረሩ ፡ እኔም ፡ እንዘፈዘፍ ፡ ጀመር ። እጆቼም ፡
ከመንቀጥቀጥ ፡ ብዛት ፡ የተነሳ ፡ ራዱ ። መ
ሪውንስ ፡ እንዴት ፡ አድርጌ ፡ ልጨብጠው ?
የሆነው ፡ ሁኖ ፡ ወደ ፡ ዳር ፡ ወጣ ፡ አድርጌ ፡
አንድ ፡ ትንሽ ፡ ጉድጓድ ፡ አስደግፌ ፡ አቆምሁ
ና ፡ ሞተሩን ፡ አጠፋሁት ። ዓይኖቼ ፡ እንባ ፡
አቅረው ፡ ሳለ ፡ ብነዳ ፡ ሰው ፡ እንዳልገጭ ፡ ፈ
ራሁ ። ላምስት ፡ ደቂቃዎችም ፡ ያህል ፡ እዚያ
ው ፡ ስንቆም ፡ ልጄ ፡ ምንም ፡ ሳይናገር ፡ እኔ ፡
ላይ ፡ እንደተንጠለጠለና ፡ እንደ ፡ ተንቀጠቀ
ጠ ፡ ነበር ። በቀኝ ፡ እጄ ፡ አቅፌ ፡ ይዤ ፡ ካሚ
ዎኑን ፡ በግራ ፡ እጄ ፡ እየነዳሁ ፡ ወደም
ኖርበት ፡ ጐጆ ፡ ሄድሁ ። ከዚያ ፡ በኋላም ፡
እህል ፡ ወደማቀርብበት ፡ ለመሄድ ፡ አልፈለ
ግሁም ።

ካሚዎኑን ፡ ከበር ፡ ላይ ፡ አቁሜ ፡ አዲሱን ፡
ልጄን ፡ ታቅፌ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ስገባ ፡ በአነስተ



ኛ ፡ እጆቹ ፡ አንገቴን ፡ አጥብቆ ፡ ተጠምጥሞ ፡
ይዞ ፡ ጉንጩን ፡ ካልተላጨው ፡ ጉንጬ ፡ ጋር ፡
አጣብቆ ፡ ነበር ። ባልንጀራዬና ፡ ሚስቱ ፡ ከቤ
ት ፡ ነበሩ ። እንደገባሁም ፡ በዓይኔ ፡ ጠቀስኋ
ቸው ፡ በኩራትና ፡ በደስታም ፡ «ይሄውላችሁ ፡
የኔን ፡ ትንሹን ፡ ቫንያን ፡ አገኘሁት ፤ እነሆ ፡ መ
ጣን ፡ እናንት ፡ ደግ ፡ ሰዎች ፡» አልኋቸው ። እ
ነሱ ፡ ልጅ ፡ ስላልነበራቸው ፤ ሁለቱም ፡ ልጅ ፡
ይፈልጉ ፡ ነበርና ፡ ትንሽ ፡ ሲያመነቱ ፡ ተቆዩ ፡
በኋላ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ይንደፋደፉ ፡ ጀመር ።
እኔም ፡ ልጄ ፡ እንዲለቀኝ ፡ ላስገድደው ፡ አል
ቻልሁም ። ግን ፡ እንደምንም ፡ አባብዬ ፡ እን
ዲለቀኝ ፡ ከአደረግሁ ፡ በኋላ ፡ እጆቹን ፡ በሳሙ
ና ፡ አጠብሁትና ፡ እንዲበላ ፡ ከጠረጴዛው ፡ አ
ጠገብ ፡ አስቀመጥሁት ። የባልንጀራዬ ፡ ሚስት
ም ፡ ሾርባ ፡ በሰሐን ፡ አመጣችለት ፡ እሱም ፡ በ
ፍጥነት ፡ ሲበላ ፡ ባየችው ፡ ጊዜ ፡ ታለቅስ ፡ ጀ
መር ። ከምድጃውም ፡ አጠገብ ፡ ቁማ ፡ እንባ
ዋን ፡ በሽርጧ ፡ ስትጠርገው ፡ ባያት ፡ ጊዜም ፡
ቫንያ ፡ ወደሷ ፡ ሲሮጥ ፡ ሂዶ ፡ ልብሷን ፡ እየሳ
በ ፡ «አክስቴ ፡ ለምን ፡ ታለቅሻለሽ? አባቴ ፡ እ
ኮ ፡ ከቡና ፡ ቤቱ ፡ አጠገብ ፡ ነው ፡ ያገኘኝ ። ስ
ለዚህ ፡ ሁላችንም ፡ ደስ ፡ ሊለን ፡ ሲገባን ፡ አ
ንቺ ፡ ግን ፡ ታለቅሻለሽ ፡» ባላት ፡ ጊዜ ፡

በፊት ፡ አብሮኝ ፡ ይሄድ ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግ
ን ፡ ለኔ ፡ አንድ ፡ ቁራጭ ፡ ዳቦና ፡ አንድ ፡ ሽን
ኩርት ፡ ትንሽ ፡ ጨው ፡ ለቀን ፡ መዋያዬ ፡ ሲ
በቃኝ ፡ ለሱ ፡ ግን ፡ ወተትና ፡ የተቀቀለ ፡ እን
ቁላል ፡ እንዲሁም ፡ አንድ ፡ ሙቅ ፡ ሾርባ ፡ የ
ሚያስፈልገው ፡ መሆኑን ፡ ስለተረዳሁትና ፡ ይ
ህን ፡ ሁሉ ፡ ለማድረግ ፡ ሥራዬን ፡ የሚያጓድ
ልብኝ ፡ ስለሆነ ፡ ከባልንጀራዬ ፡ ሚስት ፡ ጋር ፡
ከቤት ፡ እንዲውል ፡ ቆረጥሁ ። ከቤት ፡ መዋ
ልም ፡ ጀመረ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡
ሲያለቅስና ፡ ወደ ፡ አመሻሽም ፡ እኔን ፡
ለማግኘት ፡ እህሉን ፡ ወደማቀብልበት ፡ እየ
ሮጠ ፡ ይመጣና ፡ እዚያም ፡ ሲጠብቀኝ ፡ ያ
መሽ ፡ ነበር ።

በመጀመሪያው ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ የሚያስ
ቸግር ፡ ነገር ፡ ሁኖብኝ ፡ ነበር ። አንድ ፡ ቀን ፡
እንደአጋጣሚ ፡ ሁኖ ፡ አድካሚ ፡ የሆነ ፡ ሥራ ፡
ስንሠራ ፡ ስለዋልን ፡ ገና ፡ ሳይመሽ ፡ ተኛን ።
ሁሉ ፡ ጊዜም ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ይጫወትና ፡ ይ
ለፈልፍ ፡ ነበር ፡ የዚያንለት ፡ ግን ፡ ዝም ፡ ስላለ ፤
«ምንድር ፡ ነው ፡ የምታስበው ፡ ልጄ?» ብዬ ፡
ጠየቅሁት ። ጣራውን ፡ ሲመለከት ፡ ቆይቶ ፡
«አባባ ፡ የቆዳ ፡ ካፖርትህን ፡ የት ፡ አደረስከው?»
ብሎ ፡ ጠየቀኝ ። በሕይወቴ ፡ ሙሉ ፡ የቆዳ ፡



ካፖርት ፡ አልነበረኝም! ይሁን ፡ እንጅ ፡ አን
ድ ፡ መልስ ፡ መስጠት ፡ ግድ ፡ ሆነብኝ ። «ቮ
ሮኔዥ ፡ ተውሁት!» አልሁት ። ቀጥሎም ፡ «ለ
ምንድር ፡ ነው ፡ እኔን ፡ ፈልገህ ፡ ለማግኘት ፡
እረጅም ፡ ጊዜ ፡ የወሰደብህ?» አለ ። «አንተ ፡
በኡሪኡፒንስክ ፡ ሳለህ ፡ እኔ ፡ አንተን ፡ እፈል
ግህ ፡ የነበረው ፡ በጀርመን ፡ በፖላንድና ፡ በቤ
ሎሩስያ ፡ ነበር ፡» አልሁት ። «ኡሪኡፒንስክ ፡
ከጀርመን ፡ ይቀርባልን? ከቤታችን ፡ ፖላንድ ፡
እሩቅ ፡ ነውን?» ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ስንነጋገር ፡
እንቅልፍ ፡ ይዞን ፡ ተኛን ።

ስለዚያ ፡ የቆዳ ፡ ካፖርት ፡ ሲጠይቅ ፡ አንድ ፡
ምክንያት ፡ የሌለው ፡ ይመስልሃልን? የለም ፡
አንድ ፡ ምክንያት ፡ አለው ። ምናልባት ፡ አ
ንድ ፡ ጊዜ ፡ እውነተኛ ፡ አባቱ ፡ የቆዳ ፡
ካፖርት ፡ ኑሮት ፤ ስለዚህ ፡ እሱ ፡ ትዝ ፡
ብሎት ፡ ይሆናል ። የልጅ ፡ አእምሮ ፡ ልክ ፡ እ
ንደ ፡ በጋ ፡ መብረቅ ፡ ያለ ፡ ነው ። ለጊዜው ፡
ብልጭ ፡ ብሎ ፡ አንዳንድ ፡ ነገሮች ፡ እንዲታ
ወሱት ፡ ያደርግና ፡ ወዲያውኑ ፡ ደግሞ ፡ ይረ
ሳዋል ። አሁንም ፡ ትዝ ፡ ያለው ፡ እንደበጋው ፡
መብረቅ ፡ ለጊዜው ፡ ብልጭ ፡ ስላለበት ፡ ይህ
ንኑ ፡ አሰቦ ፡ ነው ።

ምናልባት ፡ በኅዳር ፡ ወር ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ባ

ይደርስብኝ ፡ ኑሮ ፡ በኡሪኡፒንስክ ፡ አንድ ፡
ዓመት ፡ እንቆይ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ባንድ ፡ መንደ
ር ፡ ውስጥ ፡ ጭቃማ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ እየነዳ
ሁ ፡ ስሄድ ፡ በጣም ፡ ድጥ ፡ ስለነበረ ፡ ከመን
ገዴ ፡ ላይ ፡ የነበረችውን ፡ ላም ፡ ገጨኋት ። እ
ንደምታውቀው ፡ ሴቶች ፡ መንጫጫት ፡ ጀመ
ሩ ፡ የመንደሩ ፡ ሰውም ፡ ከቦታው ፡ ላይ ፡ ተሰ
በሰበ ፡ ወዲያውኑም ፡ አንድ ፡ የትራፊክ ፡ ኢን
ስፔክተር ፡ ደረሰ ። ነገሩን ፡ ቀላል ፡ እንዲያደር
ገው ፡ ብጠይቀው ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ የመንጃ ፡ ፈ
ቃዴን ፡ ወሰደብኝ ። ላሟ ፡ ግን ፡ ተነስታ ፡ ጭ
ራዎን ፡ ለብሳ ፡ በመንገዱ ፡ አቆልቁላ ፡ ፈረጠ
ጠች ፡ እኔም ፡ የመንጃ ፡ ፈቃዴን ፡ አጣሁ ። ክ
ረምቱን ፡ አናጢነት ፡ እየሰራሁ ፡ አሳለፍሁት ፡
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የወታደርነት ፡ ባልንጀራዬን ፡
አገኘሁት ፡ እሱም ፡ በምክትል ፡ ወረዳችን ፡
ውስጥ ፡ በመኪና ፡ ነጅነት ፡ ይሠራ ፡ ስለነበረ ፡
ወደሱ ፡ ዘንድ ፡ ሂጄ ፡ እንድቀመጥ ፡ ጋበዘኝ ።
እዚህም ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ የአናጢነት ፡ ሥራ ፡
ስትሠራ ፡ ተቆየህ ፡ በኋላ ፡ ከወረዳችን ፡ አዲ
ስ ፡ የመንጃ ፡ ፈቃድ ፡ ልታወጣ ፡ ትችላለህ ፡
አለኝ ። ስለዚህ ፡ አሁን ፡ ልጄና ፡ እኔ ፡ ወደካ
ሻሪ ፡ ነው ፡ የምንጓዘው ።



አዳጋውም ፡ ባይደርስብኝ ፡ ኑሮ ፡ ከኡሪኡ
ፒንስክ ፡ ለመሄድ ፡ አስቤ ፡ ነበር ። ከሚሰማኝ
ም ፡ ኃዘን ፡ የተነሳ ፡ አንድ ፡ ቦታ ፡ መኖር ፡ ይ
ሰለቸኛል ። ቫንያ ፡ አድጎ ፡ ወደ ፡ ትምህርት ፡
ቤት ፡ ሲሄድ ፡ ምናልባት ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡
ቦታ ፡ እሠፍር ፡ ይሆናል ። ግን ፡ አሁን ፡ ለጊ
ዜው ፡ የሩሲያን ፡ አገር ፡ አብረን ፡ በእግራች
ን ፡ እናዳርሰዋለን ።

«ይደክመዋልን?» ብዬ ፡ ጠየቅሁት ።

«መቼ ፡ በእግሩ ፡ ሂዶ ፡ ቢያውቅ ፡ ነው ፡
ይበልጠውን ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ እሽኮኮ ፡ ብዬ
ው ፡ የምሄድ ፤ ሲደክመው ፡ ዘሎ ፡ ይወርድና ፡
እንደ ፡ ፍየል ፡ ግልገል ፡ በመንገዱ ፡ ዳር ፡ ዳር ፡
ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ይዘላል ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ ምን
ም ፡ አይደለም ፡ ወንድሜ ፤ እኛ ፡ ተለማምደ
ናል ፤ ብቻ ፡ የሚያሰጋኝ ፤ ልቤ ፡ አንድ ፡ የሆ
ነው ፡ ነገር ፡ አለ ፤ ሊለወጥ ፡ የሚቻል ፡ ቢ
ሆን ፡ ባስለወጥሁት ፡ ነበር ። አንዳንድ ፡ ጊ
ዜም ፡ ክፉኛ ፡ ይወጋኛል ፡ ስለዚህ ፡ አንድ ፡
ቀን ፡ በተኛሁበት ፡ እንዳልቀርና ፡ ትንሹ ፡
ልጄ ፡ ብቻውን ፡ እንዳይሆን ፡ እፈራለታለ
ሁ ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ ደግሞ ፡ የሚያስቸ
ግረኝ ፡ በጣም ፡ የምወዳቸውንና ፡ አሁን ፡ የተ
ለዩኝን ፡ ሰዎቼን ፡ በየማታው ፡ በሕልሜ ፡ አያ

ቸዋለሁ ። ይበልጠውን ፡ ጊዜ ፡ ሲታዩኝ ፡ እኔ ፡ በኩርንቺት ፡ ሽቦ ፡ አጥር ፡ ውስጥ ፡ ያለሁና ፡ እነሱ ፡ ካጥሩ ፡ ውጭ ፡ ነፃ ፡ የሆኑ ፡ ይመስለኛል ። ከኢሪናና ፡ ከልጆቼ ፡ ጋር ፡ ስለማንኛውም ፡ የምንነጋገርና ፡ ኩርንቺቱን ፡ ሽቦም ፡ ለመበጠስ ፡ ስሞክር ፡ ከዓይኔ ፡ ስር ፡ በነው ፡ የሚጠፉ ፡ ይመስለኛል ። በጣም ፡ ደግሞ ፡ የሚገርመው ፡ በቀን ፡ ውስጥ ፡ እንባዬን ፡ አንቄ ፡ ስለምይዘው ፡ ኃዘኔን ፡ በፊቴ ፡ ላይ ፡ ሊያየው ፡ አይችልም ፡ ግን ፡ አንዳንድ ፡ ማታ ፡ ከእንቅልፌ ፡ ስነቃ ፡ ትራሴ ፡ በእንባ ፡ እረጥቦ ፡ አገኛዋለሁ ።»

ከወደ ፡ ጫካው ፡ በኩልም ፡ የባልንጀራዬ ፡ ድምጽ ፡ ሲሰማኝ ፡ መቅዘፊያው ፡ ደግሞ ፡ ውኃውን ፡ ሲመታው ፡ ይሰማ ፡ ጀመር ።

አሁን ፡ ቅርብ ፡ ወዳጄ ፡ የሆነው ፡ እንግዳ ፡ ሰውዬ ፡ ሰላምታ ፡ ለመስጠት ፡ እንደ ፡ ብረት ፡ የጠነከረ ፡ እጁን ፡ ዘረጋ ።

«ደህና ፡ ሰንብት ፡ ወንድሜ ፡ መልካም ፡ እድል ፡ ይግጠምህ!»

«ላንተም ፡ መልካም ፡ እድልና ፡ ወደ ፡ ካሻሪም ፡ የምታደርገው ፡ ጉዞ ፡ የተቃናልህ ፡ እንዲሆን ፡ እመኝልሃለሁ !»

«አመሰግንሃለሁ ፡» አለና ፡« ልጄ ፡ ና ፡ ወ



ደ ፡ ጀልባው ፡ እንሂድ ፡» ብሎ ፡ ልጁን ፡ ጠራው ።

ልጁም ፡ ሲሮጥ ፡ ወደ ፡ አባቱ ፡ መሄና ፡ የኮቱን ፡ ጫፍ ፡ በእጁ ፡ ጨብጦ ፡ ጐንጐኑን ፡ ይሄድ ፡ ጀመር ፣

ሁለት ፡ ብቸኞች ፡ እንደ ፡ ሁለት ፡ የእህል ፡ ቅንጣት ፡ በጦርነቱ ፡ ውሽንፍር ፡ ተጠርገው ፡ ከኖሩበት ፡ መንደራቸው ፡ ወደ ፡ እንግዳ ፡ መንደር ፡ ተሰደዱ ። ወደፊትስ ፡ ምን ፡ ይገጥማቸው ፡ ይሆን? ይህ ፡ ጽኑ ፡ ፈቃድ ፡ ያለው ፡ ሩሲያዊ ፡ ልጁ ፡ አድጐ ፤ ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ በትእግሥት ፡ ለመቻልና ፡ እንቅፋቱንም ፡ ሁሉ ፡ ለማሸነፍ ፤ አገሩ ፡ በፈለገችው ፡ ጊዜም ፡ አለሁልሽ ፡ ብሎ ፡ ጥሪዋን ፡ ለመመለስ ፡ እስኪችል ፡ ድረስ ፡ አባቱ ፡ እንዲቆይለት ፡ ለማመን ፡ ፈለግሁ ።

መንገዳቸውን ፡ ሲሄዱ ፡ ቁሜ ፡ ሳይ ፡ ኃዘን ፡ ተሰማኝ ፡ ምናልባትም ፡ መለያየታችን ፡ የተሻለ ፡ ሆነ ። ነገር ፡ ግን ፡ ትንሽ ፡ ከሄዱ ፡ በኋላ ፡ ቫንያ ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ ትንሹን ፡ እጁን ፡ ሲያርገበግብልኝ ፡ ሳይ ፡ በድንገት ፡ የተሰማኝ ፡ ኃዘን ፡ እንደ ፡ አውሬ ፡ መዳፍ ፡ የለሰለሰ ፡ ሁኖ ፡ ሳለ ፡ በጥፍሮቹ ፡ ልቤን ፡ ቦጭቆ ፡ ሊያወጣው ፡ ስለደረሰ ፡ እንዳላያቸው ፡ በፍጥነት ፡ ፊቴን ፡

ዙሬ ፡ ቆምሁ ። በጦርነቱ ፡ ጊዜያት ፡ ጸጉራ
ቸው ፡ የሸበቱት ፡ ሽማግሎች ፡ ተኝተው ፡ ብ
ቻ ፡ አይደለም ፡ የሚያለቅሱት ፤ ሲነቁም ፡
ያለቅሳሉ ። የሚጠቅመውና ፡ ዋናው ፡ ነገር ፡
ኀዘንን ፡ አለማጠንከር ፡ ነው ። ከሁሉም ፡ ይ
በልጥ ፡ ይህን ፡ ደረቅና ፡ የሚያቃጥል ፡ እንባ ፡
በወንድ ፡ ጉንጭ ፡ ሲወርድ ፡ ሕፃን ፡ አይቶት ፡
ልቡ ፡ በኀዘን ፡ እንዳይገረፍ ፡ ማሰብ ፡ ነው ።

## አንባብያን ፡ ሆይ!

የፕሮግሬስ ፡ የመጻሕፍት ፡ ማ
ዘጋጃና ፡ ማሳተሚያ ፡ ቤት ፡ ስለ
ዚች ፡ መጽሐፍ ፡ ትርጉም ፤ ዝ
ግጅትና ፡ እትም ፡ ያላችሁን ፡
አስተያየትና ፡ አሳባችሁን ፡ ብ
ትገልጹለት ፡ በደስታ ፡ ይቀበላል ።
አድራሻው ፤

21, Zubovsky Boulevard,
Moscow, USSR.